## ገርማሜ ንዋይ (፲፱፻፲፮ - ፲፱፻፺ ዓ.ም.)

ገርማሜ ንዋይ የተወለደው፣ የመናገሻ ቅዱስ ጊዮርጊስ ደብር ገበዝ ከነበሩት ከአለቃ ንዋይ ተክለ ሃይማኖትና ከደጃዝማች ገርማሜ የልጅ ልጅ ከወይዘሮ አካሌ ሐሰን በ፲፱፻፲፮ ዓ.ም. በአዲስ አበባ ከተማ ገዳም ሠፈር ነው፡፡ ዕድሜው ለትምህርት ሲደርስ በአካባቢው በነበረው በቅዱስ ዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ ቤተ ክርስቲያን ግቢ መንፈሳዊ ትምህርቱን ተከታትሏል፡፡ ቀጥሎም የአንደኛ ደረጃ ትምህርቱን በተፈሪ መኮንን፣ የ፪ኛ ደረጃን በኮተቤ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ትምህርት ቤት ፈፅሟል፡፡



ገርማሜ ንዋይ



ገርማሜ ንዋይ

ገርማሜ ወላጆቹ ካፈሩዋቸው ሁለት ወንዶችና አንድ ሴት መካከል ሲሆን ለጀኔራል መንግሥቱ የስምንት ዓመት ታናሻቸው ነበር፡፡ የከፍተኛ ትምህርቱን እንዲከታተል ገርማሜን ወደ አሜሪካ የላኩት ልዑል አልጋ ወራሽ አስፋ ወሰን ኃይለ ሥላሴ ናቸው፡፡ ከገርማሜ ጋር ሌሎች አራት ወጣቶችም አብረው ተልከዋል፡፡ እነሱም ሠይፉ ማኅተመ ሥላሴ (በኋላ የትምህርት ሚኒስትር)፣ ሙላቱ ደበበ (በኋላ የገንዘብ ሚኒስትር)፣ ለማ ፍሬሕይወት (የቡና ቦርድ ዋና ሥራ አስፈጻሚ) እና ገርማሜ ወንድአፍራሽ (የሁለት አውላሎ አውራጃ ገዥ) ናቸው፡፡

ገርማሜ በአሜሪካ በዊስኮንሰን ዩኒቨርስቲ በሥነ መንግሥትና በምጣኔ ሀብት የመጀመሪያ ዲግሪውን፤ ከኮሎምቢያ ዩኒቨርሲቲ በዚያው የትምህርት መስክ የማስተርስ ዲግሪውን አግኝቷል፡፡ በአሜሪካ ቆይታው በኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር ውስጥ ም/ፕሬዘዳንት ሆኖ በመመረጥ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አበርክቷል፡፡ የማኅበሩ ልሳን በነበረው መጽሔት ያቀርባቸው በነበሩ ጽሑፎችም ገና ከወዲሁ ዝንባሌውን ግልጽ እያደረገ መጥቶ ነበር፡፡ ለምሳሌ ‹‹ኢትዮጵያ በውስጥም ሆነ በውጭ ጉዳይዋ የወደፊት ዕድሏንና በዓለምም ለሚኖራት ስፍራ አደራዋን የጣለችው፣ በኛ በወጣቶች ላይ እንደሆነ መዘንጋት የለብንም"፣ «አንድነት ኃይል ነው» «... የሰው የሥጋዊና መንፈሳዊ ውሱንነት በተናጠል ጥረቱ ራሱን ለመጥቀምም ሆነ ፍላጎቱን ለማርካት እንዳይችል እንቅፋት ይሆንበታል፡፡ የሰው ልጅ ያስገኛቸው ታላላቅ ክንዋኔዎች ሁሉ ለጋራ ጥቅሙ ሲል ያካሄዳቸው የኅብረት ጥረቱ ወጤቶች ናቸው» የሚሉት ሐሳቦቹ ዝንባሌውን ማሣያ ናቸው፡፡ ገርማሜ የሰውን የግለኝነት ጠባይ የሚገነዘብ ቢሆንም፤ በብዙኃን ኅብረት ፅኑ እምነት ነበረው፡፡ «ሰው በኑሮውና በማኅበራዊ ባሕርዩ አስገዳጅነት በኅብረት መኖር ግድ ይለዋል» ብሎ ያምናል፡፡ «የመንግሥት መኖር ዓላማው የኅብረተሰቡን የተለያዩ ፍላጎቶች ለማርካት፣ አገርን ለማጠንከር መሆን አለበት። መንግሥታዊ ሕጎችና ተቋሞቹም ዘለዓለማዊ ሳይሆኑ ይህንኑ ማኅበራዊ ፍላጎት ለማስገኘት ሲባል ከኅብረተሰቡ ዕድገት ጋር አብረው የሚያድጉና የሚለወጡ መሆን አለባቸው፡፡ ይህ ካልሆነ ድህነት፣ ሰብአዊ ጉስቁልና፣ ሐዘንና ሰላም የለሽነት ይቆራኙውና ለውድቀት ይዳረጋል» የሚል ሐሳብ ነበረው፡፡

ገርማሜ በ፲፱፻፵፮ ዓ.ም. ወደ ኢትዮጵያ እንዲመለስ በመንግሥት ሲጠራ፤ ለፒ.ኤች.ዲ. ዲግሪው በመሥራት ላይ ነበር፡፡ እንደመጣም የወቅቱ የአገር ግዛት ሚኒስትር ከነበሩት ከራስ አበበ አረጋይ ጋር የቆየ ሲሆን፤ በሚኒስትሩ የጉባዔ አመራር፣ የጉዳዮችን ጭብጥ ለይቶ በማውጣትና በጥንቃቄ የመመልከት ተሰጥዎ እንደሚደነቅ ብዙዎች ያስታውሳሉ፡፡ መደበኛ ሥራ የጀመረው ግን ራስ አበበ በራስ መስፍን ስለሺ ከተተኩ በኋላ በመሆኑ የሚያስደስተው አልሆነም፡፡ ምክንያቱ ደግሞ በራስ መስፍን ስለሺ ልዩ ጽሕፈት ቤት ውስጥ መደበኛ የሥራ ድርሻና ኃላፊነት ሳይሰጠው በተደራቢነት ደመወዝ ተቆርጦለት እንዲቀመጥ መደረጉ ነው፡፡ ራስ መስፍን ገርማሜን፣ በቅርብ ለመቆጣጠር አመቺ ነው ብለው ባመኑበት በሚኒስትሩ ልዩ ጽሕፈት ቤት ውስጥ አንድ ቢሮ ሰጥተው ያለሥራ ያስቀመጡት፤ ከውጭ

ከመጣ ጀምሮ "ተራማጅ አስተሳሰብ አለው። ለውጥ ፈላጊ ነው" እየተባለ ከሚወራለትና ከእርሳቸው ሐሳብ ፍጹም ተቃራኒ ከሆነው ከዚህ ወጣት ምሑር ጋር ተግባብቶ ሊያሠራ የሚያስችል ሁኔታ ሊኖር እንደማይችል በማመን ይመስላል።

ገርማሜ ምንም የተወሰነ የሥራ ድርሻ ባይኖረውም በተሰጠው ቢሮ ተቀምጦ፣ በየቢሮው ውስጥና በየክፍሉ በሕዝብ ላይ ይደርስ የነበረውን የአስተዳደር በደልና የሕግ መጓደል ለመታዘብ ችሏል። ይህም ከዕለት ወደዕለት ስሜቱን እየረበሸውና ኅሊናውን እያቆሰለ መምጣቱ አልቀረም። ይህን ችግር ለማስወገድ የሚያስችል በሥራ ድርሻው ተጠቅሞ ለጊዜው ሊያደርግ የሚችለው ነገር ግን አልነበረም። ስለዚህ ለተወሰነ ጊዜ ሁኔታውን ውስጥ ለውስጥ እያብላላ ቆየ። በግሉ እስከ ዕለተ ሞቱ በፀናበት በካኪ ልብስ ተወስኖ፣ ደመወዙን የወር ገቢያቸው ለወር ቀለብ ለማይበቃቸው ለመሥሪያ ቤቱ ተላላኪዎች እያካፈለ በመደጎም ችግራቸውን ይጋራ ነበር ይባላል። በዚህ መካከል ግን ምንም እንኳን የዐፄ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት፣ በነቢትወደድ ነጋሽ በዛብህ የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ደርሶበት ከነበረው ሽብር እፎይ ቢልም፤ ያንዳንድ ለውጥ ፈላጊ ወጣት ምሑራን እንቅስቃሴ ምልክት መታየት በመጀመሩ፤ የገርማሜን ቀልብ ሳበ።

ገርማሜና ሌሎች የወቅቱ ትኩስ ኃይሎች በሦስተኛው ክፍለ ዓለም ውስጥ ፍትሐዊና ዲሞክራሲያዊ አስተዳደር ለማምጣት የትግል ሥልታቸውን ይመሩ የነበሩት ከአሜሪካ ሊበራሊዝምና ከማርክሲስት ሌኒኒስት ፍልስፍና መርሆዎች በተዳቀለ አመለካከት፣ ነበር። በአሜሪካ ኮሎምቢያ ዩኒቨርስቲ ግራ ዘመም (የሶሻሊስት አመለካከት) ሲሆን፤ ገርማሜ ንዋይ ደግሞ ወደአክራሪነት ያደላ ነበር። አብረውት አሜሪካ ከተማሩት ሌሎች ኢትዮጵያውያንም ዶ/ር ዘለቀ በቀለ (በሕክምና ሙያ ያገለገሉ) ሲሆኑ፤ አክራሪ የሚሰኙ ነበሩ። ዶ/ር ምናሴ ኃይሌ (የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር) እና ልጅ ኃይለ ማርያም ከበደ (የጐጃም ጠቅላይ ግዛት ገዥ) ደግሞ ለዘብተኞች እንደነበሩ ይነገር ነበር። በ፲፱፻፵፯ ዓ.ም. በውጭ አገር ተማሪ ሳሉ ያስቡት የነበረውን ከተቻለ በአዝጋሚ ለውጥ በሰላማዊ መንገድ፣ ካልተሳካ በዐመፅ ያለውን ሥርዓት መለወጥ የሚለውን ሐሳብ አጠናከሩ።[1] ገርማሜ ተራማጅ አስተሳሰብ ቢኖረውም፤ ወደአገሩ ተመልሶ የአስተዳደሩን ችግር በቅርበት መመዘን ከመቻሉ በፊት የአገሪቱ አስተዳደር አንዳንድ ማሻሻያ እየተደረገለት ዘውዳዊ ሥርዓቱ እንደ ተጠበቀ ሆኖ ኢትዮጵያ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መሪነትም ቢሆን በሰላም ወደ ዕድገት ልታመራ ትችላለች የሚል እምነት ነበረው። ብዙዎች እንደሚሉት ይህን እምነቱን ተስፋ ቆርጦ እርግፍ አድርጎ እንዲተው ያደረገው፤ ወደ አገሩ ከተመለሰ ግዜ ጀምሮ በአገር ውስጥ በአጠቃላይና በተለይም በተመደበበት መሥሪያ ቤት የሚታየው አሳዛኝ ሁኔታ ነበር።

---

[1] ቢትወደድ ዘውዴ ገብረሕይወት እንደነገሩኝ።

ገርማሜ ዐላማውን ለማሳካት የመጀመሪያ ተግባሩ ያደረገው ልዑል ራስ እምሩ ልዩ ልዩ ዕውቀት ያላቸውን ወጣት ምሑራን እየተገናኙ ያወያዩ ስለነበረ፤ አምባሳደር ሆነው ወደ ሕንድ ሲሔዱ አዲስ አበባ የሚገኘውን የአባታቸውን ቤት ለምሑራን ወጣቶች «የቀጨኔ ክበብ» እንዲሆን እንዲፈቅዱ ማሳሰብ ነበር:: ልዑል ራስ እምሩም ጥያቄውን ተቀብለው በመፍቀዳቸው፤ ለእነ ገርማሜ ቀጣይ እንቅስቃሴ ዓይነተኛ አስተዋጽዖ አበርክተዋል:: በዚህ ተሳትፎ ወቅትም ገርማሜ አበክሮ ያነሳ የነበረው፤ ወጣቱ የለውጥ ፍላጐቱን ከግብ ለማድረስ የሚያስችለው ድርጅት ሊኖር ይገባል የሚል ነበር:: በቀጨኔ ክበብ የተጠነሰሰውን የፖለቲካ እንቅስቃሴ ወደ ጠንካራ የፖለቲካ ድርጅትነት ለመለወጥ የተጀመረው ሙከራ ግን እንደታሰበው አልዘለቀም:: በተለይም ትምህርታቸውን በእንግሊዝ አገርና በአሜሪካ በተከታተሉ ምሑራን መካከል በተፈጠረ የአመለካከት ልዩነትና[21] በውይይቱ መድረክ እምብዛም ልብ ለልብ ሊተማመኑ የማይችሉ የልዩ ልዩ ማኅበረሰብ ክፍል አባላት ተሳትፎ እየጨመረ መምጣቱ በፈጠረው ጥርጣሬ ጭምር፤ ውይይቱ ሐቀኞቹ ወጣቶች በሚፈልጉት መልክ መቀጠል ከማይችልበት ደረጃ ላይ ደረሶ ክበቡን አዳከመው፤ በመጨረሻም አከሰመው::

የቀጨኔ ክበብ መፍረስ ገርማሜን ተስፋ ሳያስቆርጠው፣ ከሐቀኛ ወጣቶች ጋር በመሆን በአገሪቱ የሚታየውን የሥልጣን ብልግና፣ የሕዝብ በደል፣ አለአግባብ ሀብት ማግበስበስና የመሳሰለውን ሕገወጥ ተግባር ለመቃወም እና የአገሩ የወደፊት ዕድገት ሊመራበት ስለሚገባው አቅጣጫ በአንድ ልብ ሁኖ ለመወያየት የሚያስችል ሌላ መድረክ መሻት ጀመረ:: በዚህ መሠረት ገርማሜ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (ኮተቤ) የቀድሞ ተማሪዎች ማኅበር «አሉምናይ» ለዚህ ተግባር እንዲጠቅም አመቻችቶ ለማቋቋም ጥረት ጀመረ:: በዚህ የሙከራ ጥንስስ ተሳታፊዎች ከነበሩት ከእንግሊዝ አገር የተመለሱትና ከብዙ ዓመታት በኋላ ከፍተኛ ሥልጣን የደረሱት ሚካኤል እምሩ (በኋላ ጠቅላይ ሚኒስትር)፣ ዘውዴ ገብረ ሥላሴ (የውጪ ጉዳይ ሚኒስትርና ም/ጠቅላይ ሚኒስትር)፣ እንዳልካቸው መኮንን (ጠቅላይ ሚኒስትር)ና አምሐ አበራ በኋላ (የቤጌምድርና ስሜን ጠቅላይ ግዛት እንደራሴ) ይገኙባቸዋል:: ማኅበሩ ሕጋዊነት እንዲያገኝ ከመንግሥት ፈቃድ ሲጠየቅ ግን ተቀባይነት ሳያገኝ ቀረ::

ገርማሜ ከተናጠል ይልቅ በድርጅት ተሰባስቦ መታገል መሠረታዊ ለውጥ ለማምጣት አማራጭ የሌለው ሥልት መሆኑን ይገነዘብ ስለነበር፤ በ፲፱፻፵፱ ዓ.ም. መጨረሻ ገደማ፣ ለበርካታ ወጣት ምሑራን ጥሪ አስተላለፈ:: ከተጠሩት አርባ ያህል ተገኙ:: እነዚህ ተሰብሳቢዎች የኮተቤ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የቀድሞ ተማሪዎች ሲሆኑ፤ ማህበሩን ያለመንግሥት ፈቃድ በመመሥረት ገርማሜን

---

[21] እንግሊዝ አገር በተማሩት በአብዛኛዎቹ የመኳንንትና የመሳፍንቱ ወገን በሆኑትና በአሜሪካ አገር በተማሩት የመካከለኛ ኑሮ ነዋሪዎች በሆኑት መካል እንዲኖር በሚፈልጉት ለውጥ ዓይነት (አክራሪነትና ለዘብተኛ) መካከል ያለ አለመስማማት ነው::

በፕሬዝዳንትነት መረጡ። ገርማሜ ለለውጥ ሲነሳ የአንድነትን ጥቅም በመረዳትና የሚታዩት ችግሮች በውይይት መፍትሔ ሊያገኙ እንደሚችሉ ተስፋ በማድረግ ነበር። እንደዚህ በመሆኑ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ይህንኑ ማኅበር አንድ እርምጃ ወደፊት ገፋ በማድረግ፣ በኢትዮጵያ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ለውጥ ለማምጣት የሚረዳ ተፅዕኖ የሚያደርግ ቡድን (ፕሬዠር ግሩፕ) እንዲሆን ለማስቻል በኮተቤ ትምህርት ቤት ያልተማሩትን ጭምር በአባልነት ተቀበሉ። በዚሁ ጊዜ ገርማሜ ግልጽ የሆነ የለውጥ ፕሮግራም አይኑረው እንጂ ለውጥ አስፈላጊ መሆኑን ከማሰላሰል ጋር በኢትዮጵያ የመሬት ይዞታ ላይ መሻሻል መደረግ የሚኖርበት ስለመሆኑና ስለመሳሰሉት የለውጥ እርምጃዎች አስፈላጊነት በግልጽ መናገር ጀመረ። ገርማሜ ንዋይ የምኒልክ የትልቁ መኳንንት (ያንካሳው) ገርማሜ የልጅ ልጅ እንደመሆኑ የመሬት ችግር እንደሌለበት ይታወቃል፤ ለሕዝብ ከማሰብ በመነጨ እንጂ።

በዘመኑ የነበረውና ዐፄ ምኒልክ የዘረጉት የመሬት ሥሪት ካገሪቱ ችግሮች ውስጥ እንደ ዋና ችግር ሆኖ የሚታይ ነበር። ይህን ለማስተካከል በኢትዮጵያ ስላለው የመሬት አመዳደብ (ሥሪት) ወይም ይዞታ ጥናት መደረግ እንዳለበት ታመነ። ይህን በተግባር ለማዋል ወርቅነህና ገርማሜ በወርቅነህ የምክትል ኤታ ማጆር ጽሕፈት ቤቱና ከፀጥታ መምሪያ ጽሕፈት ቤቱ እየተገናኙ ይጫዋወቱ ነበር።[22] ከፀጥታ መምሪያ ጽሕፈት ቤቱ ሲገናኙ ገርማሜ ወርቅነህ ቢሮ ሲገባ (ገርማሜ ብርቱ ሲጋራ አጫሽ ስለሆነ) ቡና፣ ሌ/ኮለኔል ወርቅነህ ሻይ አዘው ይወያያሉ። በኋላ እንደተረዳሁት ረዘም ያለ ምሥጢራዊ ጉዳይ ሊያነሱ ሲፈልጉ ደግሞ ይመስላል ውይይታቸውን በስብሰባ አዳራሽ ውስጥ በፈለጉት ቦታ ያደርጋሉ። በኋላ ሳስበው ጭውውታቸው እንዳይቀዳ ያደረጉት ጥንቃቄ ሳይሆን እንደማይቀር ገምቻለሁ።[23]

ከእንዲህ ዓይነት ቀናት በአንዱም እኔ በቅርብ ተገኝቼ ከሁለቱም ጋር ተነጋግሬያለሁ። ጉዳዩ እንዲህ ነው። አንድ ቀን ሁለቱም ከስብሰባው አዳራሽ እንደተቀመጡ ተጠርቼ ገብቼ፤ ለሰላምታ እጅ ነሳሁ። እነሱም የአጸፋ ሰላምታ ከሰጡኝ በኋላ ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ ፈገግ ብሎ «ልብ ትላለህ ብዬ አስባለሁ፤ እስቲ የመሬት ሥሪት ድልድል ወይም ይዞታ በኢትዮጵያ እንዴት እንደሆነ ብጥር[24] አድርገህ አጥንተህ አንድ ማስታወሻ አቅርብ» አለኝ። በዚህ ጊዜ ገርማሜ ሲጃራ በያዘበት እና በሌላው እጁ ግራ ቀኝ አገጩን ደገፍ አድርጎ ይዞ ትኩር ብሎ ያየኝ ነበር። ከነበረው ሁኔታ አንጻር ሌላ ለማለት ስላልተመቸኝ፣ እሺ ብዬ እጅ ነስቼ ወጣሁ። ነገር ግን ከሥራዬ ጋር ግንኙነት የለው፤ በዚህ ላይ ዕውቀቱ የለኝ፤ ገርማሜ ደግሞ "በወላይታ የሚገኘውን የመንግሥት መሬት ያለመንግሥት ፈቃድ ሸንሽኖ

---

[22] ገርማሜና ወርቅነህ የተዋወቁበትና ወደዚህ መተማመን ያደረሳቸውን አጋጣሚ በትክክል አላውቅም። የዓላማ አንድነትና ሁለቱም ያላቸው የቆራጥነት መንፈስ በአንድ ላይ እንዲሠሩ እንደረዳቸው እገምታለሁ።
[23] የኮሎኔል ወርቅነህ ልዩ ጸሐፊ የነበረው አቶ (በኋላ አምባሳደር) ምገስ ኃ/ማርያም እንዳጫወተኝ
[24] ወርቅነህ ይህቺን ቃል ብዙ ጊዜ ይጠቀምባታል

ለሕዝብ ሰጠ" እየተባለ ሲወራ ሰምቼ ስለነበርም፤ እንዴት ይህን ሁኔታ እሱ ባለበት እኔ እንዳጠናው ያዘኛል? ችግር ውስጥ አይከተኝም ወይ? እያልኩ አነመነምኩ።

ለማንኛውም ነገሩ እየከበደኝም ቢሆን፤ ሥራውን ለመጀመር መንደርደሪያ ነጥቦችን ነደፍኩ። በዚህ ጉዳይ ዝርዝር መረጃ የማገኝበትን የባላምባራስ ማኅተመ ሥላሴን ዝክረ ነገር፣ የነጋድራስ ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር ፣ እንዲሁም ከሳቸው ጋር ተመሣሣይ አመለካከት የነበራቸውን አቶ አስቤ ኃይሉ (በአእምሮ ጋዜጣ በ፲፱፻፲፱ ዓ.ም.) የጻፉትን መግለጫ፣ የምክትል ጸሐፊ ትእዛዝ ገብረ ወልድ ዕንግ ዳወርቅን የመሬት ግብር በኢትዮጵያ መጽሐፍ እና የተክለ ጻድቅ መኩሪያ ከዐፄ ልብነ ድንግል እስከ ዐፄ ቴዎድሮስ የሚለውን የታሪክ መጽሐፍና ሌሎች ማስታወሻዎችም እንደሚሆኑ ዝርዝር ይዤ መሥራት ጀመርኩ። ስለመሬት ሥሪት በኢትዮጵያ ሲነሳ አቶ ተክለጻድቅ መኩሪያ አንዱ ተጠቃሽ መሆናቸው አያከራክርም። እንዲህ በመሆኑ አቶ ተክለጻድቅ ከዐፄ ልብነ ድንግል እስከ ዐፄ ቴዎድሮስ በተባለው የታሪክ መጽሐፋቸው «ዐፄ ኢያሱ አድያም ሰገድ፣ "በጐንደር ደንብ አውጥተው የመሬት ሥሪትን ጀመሩ» በማለት፤ በጥቅሉ ሲገልጹ በዝርዝር ያነሱት ነገር የለም። በዚህ ላይ ሰፋ ያለ መግለጫ የማገኝበትን በማሰላሰል ላይ እንዳለሁ፣ በ፲፱፻፶፰ ዓ.ም. ማለቂያ ገደማ በቅርብ የማውቃቸውን እኔው የተወለድሁበት አካባቢ ሰው የሆኑትን አቶ ዘውዴ መኳንንት ከጐንደር ወደ አዲስ አበባ መጥተው ባጋጣሚ በድንገት አገኘኋቸውና ባማከራቸው ከፍተኛ ዋጋ ያለው መረጃ ከብዙ ልፋት በኋላ ሰጡኝ። ዝርዝር መረጃውን እንደሚከተለው አቀርበዋለሁ።[25]

---

[25] አቶ ዘውዴ መኳንንት ዕውቅ ያገር ሰው እና የሕግ ባለሙያ ስለሆኑ፤ "ስለመሬት ሥሪት" ሊያውቁ ይችላሉ በሚል ግምት፤ ስለጉዳዩ ጥያቄ አቀረብኩላቸው። ትንሽ ሲያስቡ ቆይተው ሊነግሩኝ ፈቃደኛ ቢሆኑም ማስረጃውን ለመፈለግ ግን የስምንት ቀን ጊዜ እንደሚያስፈልጋቸው ገለጹልኝ።" እኔም እሺ ብዬ በስምንተኛው ቀን በቀጠሮአችን መሠረት 'ተገናኘን። "ይቅርታ! የተለያዩ ጉዳዮች አጋጥመውኝ፣ ለመፈለግ ጊዜ አላገኘሁም" አሉኝና እንደገና ከሦስት ቀን በኋላ ልንገናኝ ሌላ ቀጠሮ ያዝን። ከሦስት ቀን በኋላም ስጠይቃቸው መልሳቸው "ነገ" የሚል ሆነ። እምቢ ለማለት ከብዷቸው እንጂ ማስረጃውን ለመስጠት ወይም ለማሳየት ደስተኛ እንዳይደሉ ተሰማኝ። ሆኖም በስልክ እንዳስታውሣቸው ነገሩኝና ከብዙ ውትወታ በኋላ ተገናኝተን ስለመሬት ሥሪቱ አጫወቱኝ። እንደአቶ ዘውዴ መኳንንት ‹‹የመሬት ሥሪት የተደነገገው በጐንደር በዐፄ ኢያሱ አድያም ሰገድ ዘመን ነው። ...፡ ሲሉ የተክለጻድቅ መኩሪያን አባባል በማረጋገጥ ለጥናቱ በእጅጉ የረዳኝን ታላቅና መሠረታዊ የታሪክ ቅርስ ማስረጃ ሰፋ እና ዘርዘር ባለ ሁኔታ አጫወቱኝ። ይህን ሁሉ ከየት አመጡ? ስላቸው "በዐፄ ኢያሱ አድያም ሰገድ ዘመን በወረቀት ላይ የተጻፈ አንድ ትልቅ መዝገብ በእጄ አለ" አሉኝ። ስለመሬት ሥሪት ለማወቅ የነበረኝ ጉጉት በመጨመሩ የተባለውን መዝገብ እንዲያሳዩኝና የምፈልገውን ጽፌ እንድወስድ፤ ወይም (በዚያን ጊዜ ፎቶ ኮፒ ስላልነበረ) ፎቶግራፍ እንዳነሳው ጠየኳቸው። «መዝገቡን በምንም ዓይነት መንገድ አላሳይም" ሲሉ፤ ቁርጥ ያለ መልስ ሰጡኝ። "ለምን?" አልኳቸው። "በሁለት ምክንያት አሉኝ"። አንደኛው፤ ልታስወስድብኝ ትችላለህ። ሁለተኛው፤ ለሰው ባሳየው ለማገላበጥ ስለሚፈልግ፤ ወረቀቶቹ በቀላሉ የሚገላበጡ አይደሉም። ደርቀው ፍንክት ፍንክት ብለው ይወድቃሉ። ስለዚህ፤ እኔ አይቼ ይሆንሃል ብዬ ያመጣሁልህ ይህን ማስታወሻ ነው። በተረፈ፤ እኔ የማውቀውን በቃል እነግርሃለሁ ያ አላረካ ካለህ ደግሞ እንደገና መዝገቡን አይቼ ተመልሼ መጥቼ እነግርሃለሁ" ብለውኝ፤ በዚሁ ተስማምቼ ያመጡልኝን ማስታወሻ ተቀበልኳቸው። ማስታወሻው ነጥብ ነጥቦችን ብቻ የያዘ በመሆኑ ዝርዝሩን በቃል አጫወቱኝ።

ዐፄ ኢያሱ አድያምሰገድ፣ ሰው በሰውነቱ እኩል ሆኖ የተፈጠረ ስለሆነ፤ የአገሩ የተፈጥሮ ሀብት ከሆነው መሬት ድርሻ ሊኖረው ይገባል።...›› የሚል አቋም (ዐላማ) ነበራቸው። ንጉሡ ይህን ዐላማቸውን በሥራ ላይ ለማዋል የንጉሡ ግዛት ከነበረችው ኢትዮጵያ ተጠርተው የመጡ የሕዝብ ተወካዮችን ሰብስበው፤ በሁሉም አካባቢ የሚታወቅና ተቀባይነት የሚኖረው አንድ ወጥ የመሬት መደልደያ (መለኪያ) መክሮ የሚወስን ሕዝባዊ ሸንጎ መሠረቱ። ለሸንጎውም ልዩ ልዩ ማግረጫዎች ቀርበውለት ሠፊ ውይይት ካደረገ በኋላ አንድ የተለካ መሬት ማለትም በቀድሞው አለካክ ቁመቱ ሃያ መጫኛ ወርዱ ሃያ መጫኛ (በሲራራ መጫኛ) በአሁኑ ፬፻ ሜትር በ፬፻ ሜትር አጠቃላይ ስፋቱ ፺ሽህ ካሬሜትር ሆኖ አንድ ቀላድ እንዲባል፤ ፲ ቀላድ ደግሞ አንድ ጋሻ እንዲሆን ተወሰነ። በዚህ "የመሬት ሥሪት" ከያንዳንዱ የመሬት ዓይነት ማለትም ከደጋው፣ ከወይና ደጋውና ከቆላው የተሰባጠረ ሆኖ፣ ሲሦው የነጋሽ፣ ሲሦው የአንጋሽ እና ሲሦው ደግሞ የቀዳሽ (አወዳሽ) ተብሎ መሬት በሦስት ባለቤቶች ተደለደለ። በዚህ ድልድል መሠረት፣

> "የነጋሽ" የሚባለው በአጠቃላይ መንግሥት ለማስተዳደሪያ የሚያስፈልገውን የሚያገኝበት የገቢ ምንጭ ሲሆን፤
> "የአንጋሽ" የተባለው የአርሶ አደሩ፣ ድርሻ፤ እና
> "የቀዳሽ" (የአወዳሽ) የተባለው ደግሞ በቤተ ክርስቲያን አገልግሎትና በአጠቃላይ ክርስቲያናዊ ትምህርትና ተግባር ላይ የተሰማራው ክፍል የሚተዳደርበት ነበር።

ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ በዚህ መለኪያ መሠረት የእያንዳንዱ ሰው ድርሻ መሆን ስለሚገባው የይዞታ መጠን ምክክር ተደርጐ በጊዜው የነበረውን የመሬት ሥፋትና የሕዝብ ብዛት መሠረት በማድረግ "ክረምት ሲሆን ከጭንጫው፣ በጋ ሲሆን ከግጫው" እያለ ተደላድሎ ተመችቶት እንዲኖር፤ ከደጋ፣ ከወይና ደጋና ከቆላ አንዳንድ ጋሻ መሬት በጠቅላላ ሦስት ጋሻ መሬት በርስትነት ለእያንዳንዱ ሰው እንዲሰጥ በመወሰን በኅብረተሰቡ መካከል ልዩነት እንዳይኖር የሚያደርግ የርስት ድልድል ዐዋጅ ዐውጀዋል። በሒደት ደግሞ እንደሕዝቡ ብዛትና እንደለማው መሬት ሥፋት እየተመዛዘነ በየጊዜው በድልድሉ ላይ ማሻሻያ ይደረግ እንጂ ጋሻ የሚለው የመለኪያ ውሣኔ ግን እስከ ፲፱፻፷፯ ዓ.ም. ድረስ ሲሠራበት ቆይቷል። የመሬት ድልድሉ እንዲህ ሲሆን ዘመቻ ሲታወጅ ከመዝመት ግዴታ ጋር የተቆራኘ ነበር። የዘመቻ ግዴታውን የተወጣው ባለርስት በጋሻዬ ያገኘሁት የዘመትኩበት የጋሻ መሬቴ ነው፤ ማን ይነካዋል፤ ብሎ መብቱን ያስከብርበት

ነበር። የዘመቻ ግዴታውን ያልተወጣ ባለርስት ደግሞ የጋሻ መሬቱን የመነጠቅ ችግር ስለሚደርስበት እሱ መዝመት ባይችል ዘማች ቀጥሮ በማዝመት ግዴታውን ይወጣ ነበር። የዘመቻ ግዴታውን ካልተወጣ ግን እንደ ግብረ ጠል[26] መሬቱን ያጣል።

ዐፄ ኢያሱ አድያም ሰገድ የመሬት ሥሪትን በሚመለከት የወሰዱት እርምጃ በዚህ ብቻ የተወሰነ አልነበረም። ንጉሡ አንዱ የሌላውን ድርሻ መሬት ድንበር ገፍቶ ወይም ነጥቆ እንዳይወስድ ማገጃ የሚሆን ሌላ እርምጃም ወስደዋል። ዐፄ ኢያሱ ይህን ሥርዓት ለመትከል ሲነሱ ሦስት ዐላማዎችን ይዘው ነበር። ከእነዚህም አንደኛው ከላይ የጠቀስኩት "ሰው በሰውነቱ እኩል ሆኖ የተፈጠረ ስለሆነ ያገሩ የተፈጥሮ ሀብት ከሆነው መሬት ድርሻ ሊኖረው ይገባል" የሚለው ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ ጉልበት ያለው ደካማውን እያጠቃ ድንበር መግፋቱና ብሎም መንጠቁ በሕዝብና በመንግሥት ላይ ፈጥሮት የነበረው ችግር መቀጠል የለበትም የሚለው ነበር። ይኸውም በባለ ርስቶች መካከል በገፋኸኝ፣ ገፋኸኝ፣ ክርክር ቢነሳ የመስፈሪያው ማመሳከሪያ አንዱ የዐፄ ፋሲል ግንብ ዙሪያ ክብና ሌላው ደግሞ ዛሬ ከጐንደር ወደ እንፍራዝ ሲኬድ ማክሰኝት ከተባለው ከተማ አጠገብ ‹‹መስቀል አውራ›› የተባለው እንደ ችካል በአራት ማዕዘን የቆሙ ኀጦች የውስጥ ዙሪያ ክብ ነበር። ሦስተኛው በአንድ የተወሰነ አካባቢ የሚኖሩ ባለ ርስቶች በይዞታ ወይም በድንበር ግፊ ቢጋጩ ዳኝቶ ችግር የሚፈታ በአካባቢው የነበረውን የያንዳንዱን ባለ ርስት የይዞታ ልክና ድንበር ለይቶ የሚያውቅ የታመነ ያገር ተወላጅ ‹‹ጭቃ ሹም›› (የመሬት አስተዳደር ሹም) አቋም መሥርተው በመሾም ይሠራበት ነበር።

በልማድ ሲሠራበት የቆየው ያስጠማኝና የተጠማኝ ውል ዝርዝርም

- አምሾ ማለት ከ፭ እጅ ፩ እጅ ወይም ፳በመቶ
- ርቦ ማለት ከ፬ እጅ ፩ እጅ ወይም ፳፭በመቶ
- ሲሦ ማለት ከ፫ እጅ ፩ እጅ ወይም ፴፫ በመቶና
- እኩል ማለት ግማሽ ከ፪ እጅ ፩እጅ ወይም ፶ በመቶ ማለት ነው።

በሰሜኑ ክፍለ ሀገራት የተጠማኝና ያስጠማኝ ውል ገበሬው ከባለ መሬቱ ጋር የሚያደርገው ውል ከዚህ በታች ከተመለከቱት ዝርዝሮች ባንዱ የተካተተ መሆን ነበረበት።

- መሬቱን ብቻ በመስጠት፤
- መሬት መስጠትና የዘሩን ግማሽ በማውጣት፤

[26] ግብረ ጠል፦ ግብር ባለመክፈሉ በመንግሥት የሚወሰድ መሬት

- መሬት መስጠት፣ የዘሩን ግማሽ ማዋጣትና በአረም፣ በአጨዳው፣ ወይም በውቂያ ጊዜ ባንዱ እገዛ ማድረግና
- መሬት ሰጥቶ፣ ዘር እኩል አውጥቶና በውቂያ ማገዝ ነበር።

እስከ ዐፄ ምንሊክ ወደ ሥልጣን መምጣት ድረስ ችግሩ በዚህ ሲፈታ ቆየ። ከዐፄ ምንሊክ ሥልጣን መያዝ በኋላ ግን የምሥራቅ፣ የደቡብ፣ የምዕራብና የማዕከላዊው ክፍለ አገሮች የመሬት ሥሪት የመንግሥትና የባላባት ተብሎ በሁለት መደብ ተለየ። የዚህ ምክንያቱ ደግሞ ዐፄ ምኒልክ ወደ ሥልጣን የመጡበት ወቅት የነበረው አጠቃላይ የአገሪቱ ሁኔታና እርሳቸው አገሪቱን ለማስተዳደር የተከተሉት ዘዴ ነበር። ዐፄ ምንሊክ ወደሥልጣን ሲመጡ የሰሜኑ ክፍል ሕዝብ ገዢነታቸውን ስለተቀበለው፤ የኢትዮጵያን አንድነት አጠናክሮ ወደ ጥንት ይዞታዋ ለመመለስ ፊታቸውን ወደ ምሥራቅ፣ ደቡብ እና ምዕራብ ለማዞር አጋጣሚው ፈቅዶላቸዋል። በመሆኑም፣ በእነዚህ ክፍሎች የነበሩ የየጎሣ ባላባቶችና ገዢዎች የርሳቸውን የማዕከላዊ መንግሥት መሪነት አምነው በመቀበል የሚፈልግባቸውን ግዴታ እስካሟሉ ድረስ ሲሦ ምርጥ መሬታቸውን አንስተው (ይዘው) የቀደመ መብታቸው ሳይነካ በሰላም ሊኖሩ እንደሚችሉ የሚያረጋግጥ እና በዚህ ዕድል እንዲጠቀሙ የሚጋብዝ ዐዋጅ አስነገሩ። ዐዋጃቸውን ባለመቀበል ያመፁትን ደግሞ፣ በጦር ኃይል ድል እያደረጉ ከማዕከላዊ መንግሥት በሚሾም የበላይ ሹም እንዲተዳደር አደረጉ። ይህም ነባሮቹ የምሥራቅ፣ የደቡብ፣ የምዕራብና የማእከላዊው አገሮች ገዥዎችና የጐሣ መሪዎች ሲሦ ምርጥ መሬታቸውን ካነሡ በኋላ፣ ከነባሩ ኑዋሪ ጋር ይዘው በቆየው አባት አደር ሥርዓት እየተዳደሩ፤ ለመንግሥት መግባት ያለበትን አሥራትና ግብር እያንዳንዱ ገበሬ በየራሱ ያስገባል። ሌሎቹ ገዥዎችና የጐሣ ባላባቶች ደግሞ ሲሦ ምርጣቸውን አንሥተው ከነባሩ ኑዋሪ ሕዝብ ጋር እንደ ቀድሞው መሬቱን ይዘው እያረሱና፣ እንደላይኛው ገበሬ ግብር እና አሥራቱን ቀጥታ ለአካባቢው የመንግሥት ሹም ሳይሆን ለገዥው ወይም ለጐሣ መሪው እያስገቡ፣ የጐሣ መሪዎቹ ደግሞ ሁሉን አሰባስበው በስማቸው ለመንግሥት ያስገባሉ። አጠቃላይ የመሬት ይዞታው ስምም በእነዚህ መሪዎች ስም እንጂ፤ በእያንዳንዱ ገበሬ ስም አልነበረም።

የመንግሥት መሬት የሚባለው ይዞታነቱ የማዕከላዊው መንግሥት ሆኖ ለመንግሥት ሹማምንት፣ ለቤተ-ክህነት አገልጋዮች፣ ለወታደር እና ለሌላም ባለውለታ በግል ርስትነት ሳይሆን፤ በማደሪያነት፣ በመትከያ መንቀያነትና ሌላም ልዩ ልዩ ስም ያለው መንግሥት የሚያስተዳድርበት ብሔራዊ ሀብት ነበር። የባላባት ተብሎ የተመደበው መሬት፣ የአገሩ ተወላጅ በግል ይዞታነት (በርስትነት) የያዘው መሬት እንዳለ ሆኖ፤ እንደላይኞቹ

የመሬት ባለይዞታዎች (ባለርስቶች) የዚህ ክፍል መሬት ይዞታም ከዘመቻ ግዳጅ ነፃ አልነበረም። የዚህ ክፍል ሌላ ግዴታም ያለበት ሲሆን፤ እርሱም ከባላባቱ የሚታዘዙ ልዩ ልዩ አገልግሎቶችን መፈፀምን የሚያጠቃልል ነበር።

እንዲህ በመሆኑ አንዳንድ የመሬት ባለይዞታ (ባለርስት) የሆኑ የአገሩ ተወላጆች፣ ይህ ባለይዞታነት የሚያስከትለውን የዘመቻ ግዴታን በመጥላት፤ የዘመቻ ግዴታ የሌለበትን የቤተክርስትያን አገልጋይ፣ ወይም የዘመቻ ግዴታውን ራሱ የሚወጣውን የወታደር መሬት እየተጠመኑ (እየተከራዩ) ማረስን በመምረጣቸው፤ እንደ ሰሜኑ ክፍል አንዱ ለሌላው እያረሰ ለባለ መሬቱ እህል የሚሰፍርበት እና አሥራት እና ግብርም የሚከፍልበት ሁኔታ ተፈጠረ። ሁኔታው በጥሞና ሲታይ፣ የተጠማኝ ወይም የገባርነት ሥርዓት በሁሉም ክፍል የነበረና፤ ሊፈጠር የቻለውም በሕዝቡ የተለያዩ ፍላጎቶች ምክንያት እንጂ በመንግሥት ድንጋጌ የተጫነ አልነበረም።

በምዕራብ፣ በምሥራቅ በደቡብና በማዕከል ክፍለ ሀገራት የመሬት ባለቤቶች ከተጠማኙ ወይም ከመሬት ተከራዩ ገበሬ ጋር በኑሮ የማይገናኙ ከመሆኑ በላይ እንደ ላይኞቹ አስጠማኞች መሬት ከመስጠት ሌላ ምንም ዓይነት ድጋፍ አያደርጉም ነበር። አቶ ዘውዴ ስለዚህ ሁኔታ ደግሞ እንዲህ ይላሉ :-

ዐፄ ምኒልክ ከዚህ ሌላ፣ ለኢትዮጵያ መናገሻ ከተማነት የተመረጠችውን የአዲስ አበባ ከተማን ዕድገት ለማፋጠን እንዲረዳ የከተማውን መሬት ለተወሰኑ መሳፍንትና መኳንንት ከነሠራዊታቸው በመሥፈሪያነት የማከፋፈል እርምጃ ወስደዋል። የዚህ የመሬት አደላደል ዐላማ፣ በወቅቱ ንጉሠ ነገሥቱን ተከትለው አዲስ አበባ የገቡት መሳፍንትና መኳንንት ከነሠራዊታቸው መኖሪያቸውን በመሥራት፤ እራሳቸውን ጠቅመው ከተማዋንም በማልማት ጣምራ ጥቅም ያስገኛል በሚል እምነት የተመሠረተ ነበር።

ይህ በዐፄ ምንሊክ ዘመነ መንግሥት ለመሳፍንቱና ለመኳንንቱ ከነሠራዊታቸው በሠፈርነት ተከፋፍሎ የተሰጣቸው የከተማ ቦታ እና በመንግሥት ስም የነበረው የምሥራቅ፣ የምዕራብና የደቡብ ክፍል የሀገሪቱ መሬት እየዋለ እያደረ አስቀድሞ በሥፍራው ለቆዩትና በየጊዜው ተከታትለው ለመጡት የመንግሥት ሹማምንትና የጦር አለቆች፣ እንዲሁም ለቤተ ክህነት አገልጋዮች ሊሸጥና ሊለወጥ በሚችል በግል ይዞታነት የሚሰጥበት ሁኔታና ሒደት በተጠቃሚዎች ተፈጠረ። መሳፍንቱና መኳንንቱ ከነሠራዊታቸው «ለመኖሪያና ለመተዳደሪያ ይሁናችሁ» ተብሎ የተሰጣቸውን የገጠርና የከተማ ቦታ አብሮ የተመራውን ሠራዊት በትነው በግል ርስትነት ይዞታቸውን በማጠናከር፤ የገጠሩን መሬት ከፊሉን በጢሰኛ ጉልበት እያለሙ በሚገኘው ምርትና

> የከተማውንም ቦታ ሸንሽነው በውድ ዋጋ እየሸጡ በሚያገኙት ገንዘብ ራሳቸውን በማበልፀግ የማኅበራዊና የኢኮኖሚያዊ ኑሮውን ደረጃ ልዩነት አሠፉት። ከሕዝብ ተለይተው መሬት ለእነሱ ብቻ እንደተፈጠረ ወደማድረጉ አዘነበሉ። መኳንንቱ በዚህ ብቻ ሳይወሰኑ በመሬት ይዞታቸው ለመንግሥት መክፈል የነበረባቸውን አሥራትና ግብር ባለመክፈል፣ የመንግሥትን ገቢ እያስቀሩ፣ መንግሥትን የልማት ሥራ ማካሄጃ ገንዘብ በማሳጣት በበደል ላይ በደል መፈጸሙን ቀጠሉ። ይህ ሁኔታ ንጉሣውያን ቤተሰብን በማጠቃለል ተጠናክሮ በተባባሰ ሁኔታ ቀጠለ። ይህን ተከትሎም መሳፍንቱና መኳንንቱ የጋራ ሀብትና ንብረት የነበረውን መሬት የግል መበልፀጊያ ያደረጉበት አዲስ ክስተትም መታየት ጀመረ። በአንጻሩ ደግሞ አብዛኛው ሕዝብ መሬት አልባ እየሆነና ይበልጥ እየደኸየ በመሔዱ በኅብረተሰቡ መካከል የነበረው የኑሮ ደረጃ በሚያሳፍር ልዩነት እየተራራቀ ሔደ።
>
> የብዙ ጋሻ መሬት ባለቤት የሆኑት ገዢዎችና የጎሣ መሪዎች ደግሞ እየዋሉ ሲያድሩ፣ በተለይ በዐፄ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት አስተዳደር ከመንግሥቱ መኳንንትና ወይዛዝርት ጋር በአበልጅነት፣ በጡት ልጅነትና ወዳጅነት በመቀራረብ፣ «በወለድ አገድ መሬት አስይዘን ወይም አውርሰን» እያሉ፣ በየቦታው ብዙ ሺ ጋሻ መሬቶች ስለወረሱ፣ በመሬቱ ላይ የነበረው ገበሬ በገዛ አገሩና በገዛ መሬቱ የነዚህ የመንግሥት ባለሥልጣኖችና ወይዛዝርት ጢሰኛና ገባር እየሆነ ሔደ።

እንግዲህ ይህን መረጃ ነው ከሌሎች መረጃዎች ጋር አገናዝቤና አጠናቅሬ እንደመሠረታዊ የመሬት ሥሪት (ይዞታ) ታሪክ ዘገባ አዘጋጆቼ ላዘዙኝ የመፈንቅለ መንግሥቱ መሪዎች በማቅረብ የተሰጠኝን የሥራ ድርሻ የተወጣሁት።[27]

ገርማሜ የመሬት አያያዝ ሥርዓቱን በመጀመሪያ ዲግሪው መመረቂያ ጽሑፍ ውስጥ ያሠፈረው፣ በኬንያ ይታይ የነበረውን "ማው ማው" ንቅናቄ ካስነሣው ምክንያት ጋር ተመሳሳይ አድርጎ ነበር። የዚህን ጥናት ዘገባ መግለጫ ከሰማና ሙሉ ዝርዝሩን ጽሑፍ አቅርቤ ካነበበ በኋላ ድሮ ከነበረው ስሜት መለስ ማለቱን ገመትኩ። ምክንያቱም ነጮች በኬንያ መሬት የወሰዱት በኃይል ሲሆን የኢትዮጵያው መሬት አወሣሰድ በኃይል አለመሆኑን በመረዳቱ ነበር። በኬንያ የነበረው የመሬት ይዞታ ሥርዓት የአገሩ ተወላጆች እና የመሬቱ ባለቤቶች በአገራቸው መሬት የለሽና የፈረንጅ አራሽ እንዲሆኑ ሲያደርግ፣ ያገሩ ተወላጅና የመሬቱ ባለቤት ያልሆኑት መጤ ነጮች የኬንያን ለም መሬት በኃይል ወስደው ተወላጁን የነሱ አራሽ አደረጉት። ልክ እንዲሁ

---

[27] ይህንን ኃላፊነት እንድወጣ ላበቁኝ ወዳጄ ለአቶ ዘውዴ መኳንንት በዚህ አጋጣሚ በጣም አመሰግናለሁ። አቶ ዘውዴ መኳንንት ካረፉ አሥራ አምስት ዓመት ይሆናቸዋል። ለእኔ ያብራሩልኝ ታሪክ የተገኘበት መዝገብ አሁንም በቤተሰባቸው እጅ ይኖራል ብዬ አስባለሁ። የሃገር ቅርስ ስለሆነ ጉዳዩ የሚመለከተው ክፍል ቤተሰባቸውን አነጋግሮ ቢያገኘው ለሃገር ጠቃሚነቱ የጎላ ነው።

ወዳገሩ ሁኔታ ሲመለስ ለዚህ ነው ገርማሜ እነዚህን ከመሬት ባገኙት ኢኮኖሚ ተጠቃሚ የሆኑ ጥቂቶች፣ የፖለቲካ ሥልጣኑንም በመጨበጣቸው በሕዝቡ ላይ ይደርስ ለነበረው የአስተዳደር በደልና የፍትሕ መጓደል በዋናነት ተጠያቂ አድርጎ ያቀርባቸው የነበረው፡፡

በሌላ በኩል በ፲፱፻፶፪ ዓ.ም. መንግሥት ከወቀሳ ለመዳን አንድ ወጥ የሆነ የግብር አከፋፈል ሥርዓት በማውጣት፣ ከዚያ በፊት ባለመሬት ይጠየቅ የነበረውን አንዳንድ ግዴታ በማስቀምና ከውጭ በተገኘ የማልሚያ ብድር እየተጠቀመ ባለመሬት መሬቱን እንዲያለማ በማበረታታት የእርሻ ልማት ሥራ እንዲስፋፋ ሥራ ጀመረ፡፡ ይህም ቢሆን ግን ይበልጥ የጠቀመው እነዚያኑ መሬቱን የያዙትን ጥቂት ባለሥልጣኖችና ባላባቶች ነበር፡፡ የመሬት ይዞታን መሠረት ለማስፋት በማሰብ የአገሪቱ ባለ ውለታ ናቸው ለሚባሉ ሰዎችና ለመንግሥት ሠራተኞች መሬት ሊሰጥ የሚችልበት ዐዋጅም ወጣ፡፡ ይሁን እንጂ አፈጻፀሙ ለሌላው ይቅርና «እግሩን ለጠጠር፣ ደረቱን ለጦር በመስጠት ግንባር ቀደም መሥዋትነት እየከፈለ የአገሩን ነፃነት የሕዝቡን ሰላም ለጠበቀውና ለሚጠብቀው ክፍል እንኳ፤ አገልግሎቱን ሲጨርስ የሚያርፍበትና ሠርቶ የሚኖርበት መሬት ሊያገኝ የሚችልበት ፍትሐዊነት ያለው ተግባራዊ የመሬት ይዞታ ማሻሻያ ለመሆን አልቻለም፡፡ እንግዲህ ለግብርና ሥራ እጅግ አስፈላጊ የሆነ ለም መሬት፣ ጠንካራ የሰው ጉልበት፣ መልካም የአየር ጠባይ የተሟላላትና «ለአፍሪካ የዳቦ ቅርጫት» ትሆናለች የተባለላት አገር፤ ለዚህ ቅድመ ሁኔታ የሆነው የመሬት ይዞታን ሕጋዊ በሆነ መንገድ ሥርዓት የማስያዝ ቁርጠኛ እርምጃ ወስዶ፣ በዘመናዊ ሥልት ዐቅዶና አቀናጅቶ በተፈጥሮ ሀብቶችዋ የመጠቀም እድሏን ለማቃናት አለመቻል ነው የገርማሜን ኅሊና ሰላም የነሳው፡፡

በመኳንንቱ አድራጐት የተከፋው የአገሪቱ ሕዝብ ጣትን በቆይ ብቻ ዛቻ ከመቀሰር አልፎ ለጊዜው ባልተሰባሰበ መልኩ ቢሆንም ቅሬታውን አሥራት እና ግብር አልከፍልም በማለት ያሳይ ጀመር፡፡ አመቺ ሆኖ ሲያገኝ ደግሞ፣ በመንግሥት ላይ ግልጽ ተቃውሞና አሻፈረኝ ባይነትን በልዩ ልዩ መንገድ በመግለጽ፣ በደሉ ከሚችለው በላይ መክበዱን ማሳየት ያዘ፡፡ ይህ የመሬት ይዞታና የፍርድ መጉደል ያስከተለው ችግር ከሌሎች ችግሮች ጋር ተደምሮ፤ ገርማሜ «ሥር ነቀል ለውጥ» ያስፈልጋል የሚል ዐላማ እንዲይዝ ሳይገፋፋው አልቀረም፡፡ በዚህ ሐሳቡ አድናቂዎች ባያጣም አብዛኞቹ ተሰብሳቢዎች የአስተሳሰቡ ተራማጅነት ወደ አክራሪነት እንዳያሻቅብ ሥጋት ስለገባቸው ወደ ኋላ በማለታቸው፤ መድረኩ ወደ መቡተን ደረሰ፡፡

ከዚህ በኋላም ገርማሜ አንድ ጊዜ በቁርጠኝነት የተነሣ በመሆኑ፤ ተስፋ ሳይቆርጥ ሌላ መንገድ ማፈላለግ ቀጠለ፡፡ በዚህ ጊዜ በሚያደርገው ጥረት የፖለቲካውን ሁኔታ ማገናዘብ እንደሚኖርበት የሚመክሩትን የወዳጆቹን አስተያየት ተቀብሎ፤ ለዘብተኛነት ያለው የሚመስል «የቤተክርስቲያን ኅብረት» የተባለ የአዲስ ማኅበር መሥራች አባል በመሆን መድረኩን ለዐላማው ሊጠቀምበት እስከመሞከር

ደርሶ ነበር። እንደሚነገረውም ይኸው ጥረቱ ተሳክቶለት ለተወሰነ ጊዜ እንቅስቃሴ ከተካሄደ በኋላ ግን ይህም መድረክ በአገር ውስጥ በተማሩና ውጭ አገር ተምረው በተመለሱ ወጣቶች መካከል በተነሳ የሐሣብ አለመጣጣም ምክንያት እንቅስቃሴው ይዳከምና ሐሳቡ ይቀጫል።

ገርማሜ አዘውትሮ በሚያሳየው ሁኔታና በሚያቀርበው ሐሳብ፣ በወጣት ምሑራንና በወጣት ጦር መኮንኖች ዘንድ ለውጥ ፈላጊነቱ እየታወቀና ሥር እየሰደደ በመሔዱ በነዚህ ክፍሎች ውስጥ የእርሱን አስተሳሰብ በሚመለከት ክርክር መጧጧፍ ከመጀመር አልፎ የለውጥ ፈላጊው ጎራ መንፈስ እየተጠናከረ የመሔድ አዝማሚያ ማሳየቱን ቀጠለ። ከዚህ ሌላ፣ ወጣቱ ትግሉን ያካሂድ የነበረው የተለያዩ መድረኮችን በመጠቀም ከእነዚህም መካከል አንዱ በጄኔራል ሙሉጌታ ቡሊ ዙሪያ ይንቀሳቀስ የነበረውን ለውጥ ፈላጊ ቡድን ነበር። እነዚህ ሁሉ መቼም በንጉሡ ዘንድ ይታወቁ ስለነበር አንድ ደረጃ ላይ ሲደርስ፣ በተለይ እነዚህ ሁለት መድረኮች የሚያካሂዱዋቸው እንቅስቃሴዎች ወደ አሥጊነት ደረጃ እየተሸጋገሩ ናቸው የሚል ሥጋት በመፈጠሩ፤ ለጉልታዊ ሥርዓት ሕልውና አደገኛ ናቸው ተብለው ከሚገመቱት ምሑራን መካከል በፖለቲካ አመለካከትና ማኅበራዊ መሠረቱ ሰፊ ሆኖ የሚቆጠረውን የገርማሜ እንቅስቃሴዎችን በአጭር ለመቅጨት የወላይታ አውራጃ ገዥ ተብሎ ከዋናው ከተማና ከምሑሩ ጐራ እንዲርቅ ተደረገ።

ገርማሜ በግዛት አገሩ በወላይታ አውራጃም ዳኝነት በማስተካከል፣ የመንግሥትን መሬት ለድሃ ገበሬ እየሸነሸነ በመስጠት፣ ትምህርት ቤት በማስፋፋት፣ በጉቦና በምዝበራ ላይ ዘመቻ በማካሄድ ተቀባይነት በማግኘት፤ ፈጥኖ ወደ ሕዝቡ ልብ ገባ። ይህ አዲስ ሁኔታ ያስደነገጣቸው የአውራጃው የመሬት ከበርቴዎች የወጣቱን ዐላማ በገንዘብ ማስለወጥ የሚቻል መስሎአቸው ያደረጉት ሙከራ ሳይሳካ ቀረ። ወጣቱን በቅን አስተሳሰብ ከተቀበለውና በበጎ ምግባሩ ከወደደው የአውራጃው ሕዝብ በመነጠልም ዐላማውን ለማክሸፍ ተሞክሯል። በጊዜው እንደሰማሁት የወቅቱ የሲዳሞ ጠቅላይ ገዥ የነበሩት ደጃዝማች መንገሻ ሥዩም (በኋላ ልዑል ራስ) በወቅቱ የአገር ግዛት ሚኒስትር ለነበሩት ለራስ መስፍን ስለሺና ለጃንሆይ በሚያቀርቡት ሪፖርት፤ «የአገሪቱን የመሬት ይዞታ ሥርዓት አናግቶ የመንግሥትን መሬት ለሕዝብ አድሏል ብለው በመክሰስ፣ ወደ ጅጅጋ እንዲዛወር አስደረጉት» እየተባለ ይወራ ነበር። እዚህ ላይ ሊጤን የሚገባው፣ ለብዙ ዓመታት ጦም ያደረን የሚያርሰው መሬት ላልነበረው ገበሬ አከፋፍሎ ሥራ ላይ እንዲውል የማድረግ የወጣቱ የተቀደሰ ተግባር፤ በወቅቱ የሚያስከስስና የሚያሰወቅስ ጉዳይ ሆኖ መቅረቡ ነው። ይህ የነበረው ሥርዓት ከሕዝብ ፍላጐት አንጻር ምን ያህል ኋላ ቀርና ጨቋኝ እንደነበር ፍንትው አድርጎ የሚያሳይ ነው።

ገርማሜ ግን በጅጅጋም ቢሆን፣ የሕዝቡን የኑሮ ሁኔታ ለማሻሻል እንደጉቦና ምዝበራ ባሉት በተበላሹ ምግባራት ላይ በመዝመት እንደወላይታው ሁሉ የሕዝቡን ከበሬታና ፍቅር መጐናጸፍ ችሏል። ይህ በዚህ እንዳለ፣ በ፲፱፻፶፪ ዓ.ም. ገርማሜ የራስ

ገብረ ሕይወት ሚካኤልን የልጅ ልጅ ወ/ሪት አያልነሽ ዘውዴን፣ የቢትወደድ ታፈረ ተሰማን ልጅ ወ/ሪት ከፈይ ታፈረን ደግሞ ታላቅ ወንድሙ ጄኔራል መንግሥቱ በአንድ ቀን በሕግ አገቡ። የከፈይ ታፈረ ታናሽ እህት በላይነሽ ታፈረም በዚያው ዕለት የልዕልት ሣራ ግዛውን አጐት ልጅ ፊታውራሪ ገብረዋህድ አበራን በማግባት ሠርጋቸውን በአንድ ላይ አከበሩ።



*ከግራ ወደቀኝ ወ/ሪት አያልነሽ ዘውዴና ገርማሜ ንዋይ፣ ወ/ሪት ከፈይ ታፈረና ጄኔራል መንግሥቱ ንዋይ፣ ወ/ሪት በላይነሽ ታፈረ እና ፊታውራሪ ገብረዋህድ አበራ*

ገርማሜ በራሱ አቅም ማድረግ ከሚችለው በተጨማሪ በጅጅጋ የሕዝቡን የአኗኗር ሁኔታ ለማሻሻል የሚረዳ ዕቅድ አውጥቶ ለማስፈፀም ጥረት አድርጓል። እንዲህ ዓይነት ዕቅድ አውጥቶ በሥራ ለመተርጎም የሚያስችል የባጀት ድጋፍ እንዲደረግለት ለመንግሥት ጥያቄ ሲያቀርብ ግን ምላሽ አያገኝም ነበር። ለጥያቄው አድማጭ አለማግኘቱ ቢያበሳጨውም፤ በራሱ ዐቅም ሊያደርግ የሚችለውን ለሕዝብ የሚጠቅም ተግባር ለማከናወን ባደረገው ጥረት ነው በአውራጃው ሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት ለማግኘት የቻለው። ገርማሜ ከላይ በተጠቀሱት አውራጃዎች ባደረጋቸው ጥረቶች ከመንግሥት በኩል ድጋፍ አለማግኘቱ ያሳደረበትን ቁጭት አንዳንድ ሰዎች ሲገልጹ፤ ቀደም ብሎ በጃንሆይ መሪነትም ቢሆን በኢትዮጵያ የአስተዳደርና የኑሮ ዕድገትን ማሻሻል ይቻላል የሚል ዕምነቱን፤ በአገር ግዛት ሚኒስቴር የነበረውን አስተሳሰብ እና አካሄድ እንዲሁም ሌሎች ድርጊቶችን ሁሉ አስተውሎ ለወጠ ይላሉ። በወቅቱ የዚሁ መሥሪያ ቤት ሚኒስትር የነበሩት ሰው የሥራ አካሔድ እና አመለካከት ለእምነቱ መለወጥ ዓይነተኛ አስተዋፅኦ አድርጓል ማለት ነው። ይህም ከእንግዲህ መፈታተን የሚገባው የንጉሡን ሥልጣን ብቻ ሳይሆን፤ ራሱን



*ከግራ ወደቀኝ ወ/ሪት አያልነሽ ዘውዴና ገርማሜ ንዋይ፣ ወ/ሪት ከፈይ ታፈረና ጀኔራል መንግሥቱ ንዋይ፣ ወ/ሪት በላይነሽ ታፈረ እና ፊታውራሪ ገብረዋህድ አበራ*

«የኢትዮጵያን መንግሥት ኋላቀር ሥርዓት ነው» ወደሚል ስላሸጋገረው፣ በአገሪቱ «ሥር ነቀል» ለውጥ መምጣት አለበት የሚለውን ዐላማ ማራመድ ጀመረ።

እንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ ነው በመለዮ ለባሹና በብዙ የከተማ ነዋሪ ሕዝብ ዘንድ ከፍተኛ ከበሬታና አድናቆት አትርፈው ከነበሩት ከሜጀር ጀኔራል ሙሉጌታ ቡሊ ጋር የቅርብ ግንኙነት በመፍጠር፣ በእኚሁ ጀኔራል ዙሪያ የለውጥ ፈላጊ ቡድን እንዲያቆጠቁጥ አድርጐ የነበረው። የዚህ ቡድን መፈጠር ሙሉጌታ ቡሊን ከወታደሩ ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት በሌለው፣ የሕዝባዊ ኑሮ ዕድገትና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር እንዲሆኑ ምክንያት ሆነ ይባላል። ልክ እንዲሁ ወጣቱ ገርማሜም በሹመት ሰበብ ከወዲያ ወዲህ ሲዘዋወር ቆየ። ገርማሜ ለነበረው የመንግሥት የሥርዓት ለውጥ እንቅስቃሴ አስተዋፅኦ ሲያደርግ ግን ከአንዳንድ ምሑራን ጋር የአመለካከትና ያለመጣጣም ልዩነት ነበረው።

በመጨረሻም ገርማሜ በግድም ቢሆን ሥር ነቀል የመንግሥት ለውጥ ለማምጣት፣ ድጋፍ የሚሰጥ የተደራጀ ኃይል ስለማስፈለጉ ማውጠንጠን ሳይጀመር አልቀረም። ከዚህ በኋላ ወገናዊነቱንና አብሮ የመዋል አዝማሚያውን ከወንድሙ ከጀኔራል መንግሥቱ፣ ከሌ/ኮሎኔል ወርቅነህና በነሱ አማካኝነት ካወቃቸው ታማኝ የክብር ዘበኛ መኰንኖች ጋር አደረገ። ለትግሉ ቅየሳ በመድረክነት ሊጠረጠር የማይችለውን የወንድሙን ቤት በመጠቀም ግንኙነቱን ማዳበር ቀጠለ። በዚህም ወቅት ታላቅ ወንድሙ ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣን እንደመሆናቸው፣ ለንጉሡ ፈጽሞ ታማኝ መሆን እንዳለባቸው ቢያውቅም፣ በወንድምነታቸው በመተማመን ከእርሳቸው ጋር በሚያደርገው ጭውውት ነገሮችን የንጉሡ ፍጹም ታማኝ ከመሆን አንጻር ብቻ ሳይሆን፣ በአገርና በሕዝብ ላይ ከሚያደርሰው ጉዳት አንጻር ጭምር መመልከት አስፈላጊ መሆኑን በልባቸው እንዲያድር ምክንያት ሳይሆን አልቀረም።

# ብርጋዴር ጄኔራል መንግሥቱ ንዋይ (፲፱፻፱ - ፲፱፻፶፫ ዓ.ም.)



*ብርጋዴር ጄኔራል መንግሥቱ ንዋይ*

ብርጋዴር ጄኔራል መንግሥቱ ንዋይ የመናገሻ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን አስተዳደር ኃላፊ (ቄሰ ገበዝ) ከነበሩት ከአለቃ ንዋይ ተክለ ሃይማኖት እና የደጃዝማች ገርማሜ የልጅ ልጅ ከሆኑት ከወይዘሮ አካሌ ሐሰን በ፲፱፻፱ ዓ.ም. አዲስ አበባ ከተማ ገዳም ሠፈር በሚባለው ቦታ ተወለዱ:: መንግሥቱ ዕድሜአቸው ለትምህርት እንደደረሰ በዚሁ ሠፈር በቅዱስ ዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ትምህርት ከተከታተሉ በኋላ ተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት ገቡ:: እዚሁ ትምህርት ቤት እያሉ ሆለታ በተቋቋመው ገነት የጦር መኮንኖች ማሠልጠኛ ትምህርት ቤት እንዲገቡ ወጣቶች ሲመለመሉ ከሌሎች ጓደኞቻቸው ጋር ተመልምለው የጦር ትምህርት ጀምረው፤ ትምህርቱን ለአንድ ዓመት ከተከታተሉ በኂላ በ፲፱፻፳፰ ዓ.ም. በምክትል መቶ አልቅና ተመረቁ::



ብርጋዴር ጄኔራል መንግሥቱ ንዋይ

ከምሩቃኑ መካከል የተወሰኑት በዚህ ጦር ትምህርት ቤት አሠልጣኝ ሆነው ሲመደቡ፤ የቀሩት መንግሥቱን ጨምሮ ወደ ማይጨው ጦር ግንባር እንዲዘምቱ ታዘዙ:: ምሩቃን መኰንኖቹ ገና መንገድ ጀምረው ጣርማ በር ሲደርሱ፤ የኢትዮጵያ ጦር ተፈትቶ፤ ያለቀው አልቆ፣ የተረፈው በመመለስ ላይ መሆኑን ሰሙ:: ከዚያም በሁኔታው አዝነው አማራጭ ለመፈለግ ወደ አዲስ አበባ ተመለሱ:: ያገኙት አማራጭ በሰሜን ሸዋ ይንቀሳቀስ ከነበረው ከደጃዝማች ኃይለ ማርያም ማሞ ያርበኞች ግንባር ሠራዊት ጋር መቀላቀል ነበር:: በዚያ ለአንድ ዓመት ያህል ከደጃዝማች ኃይለ ማርያም ማሞ ጋር በአርበኝነት ቆይተው ወደ ጅቡቲ ተሰደዱ:: ከተወሰነ የጅቡቲ ቆይታ በኋላ ወደ ሱዳን ሔዱ:: ከዚያም ‹ሶባት› በተቋቋመው የተሐድሶ የጦር ትምህርት ቤት ከሌሎች የጦር መኰንን ጓደኞቻቸው ጋር ሆነው የወታደራዊ ሙያ ክለሳ ተሳትፈው በእንግሊዝ መንግሥት ድጋፍ ንጉሡ ከስደት በሱዳን በኩል ወደ አገራቸው ሲመለሱ፤ መንግሥቱም በኦሜድላ (ጐጃም) በኩል አብረው እየተዋጉ ወደ አገራቸው ገቡ::

ነፃነት እንደተመለሰ የክብር ዘበኛን ሠራዊት እንደገና ለማቋቋም እንቅስቃሴ ሲደረግ፤ በ፲፱፻፴፩ ዓ.ም. መጀመሪያ መንግሥቱም በሻምበልነት ማዕረግ የሠራዊቱ የምልመላና ሥልጠና መኰንን ሆነው ሥራ ጀመሩ:: በሠራዊቱ ልዩ ልዩ ክፍሎች ተመድበው በፈፀሙዋቸው ተግባሮችም የመሪነት ብቃት እንዳላቸው ለማስመስከር በመቻላቸው፤ በ፲፱፻፴፯ ዓ.ም. ሜጀር ጄኔራል ሙሉጌታ ቡሊ ከክብር ዘበኛ አዛዥነት በመከላከያ ሚኒስቴር «ኤታ ማዦር ሹም» ሆነው ሲዛወሩ፤ በምትካቸው መንግሥቱ፣ በመጀመሪያ በተጠባባቂነት ቀጥሎም በብ/ጄኔራልነት ማዕረግ የክብር ዘበኛ ዋና አዛዥ በመሆን ሠራዊቱን መምራት ጀመሩ:: በዚህ ኃላፊነት ሳሉ፣ ብ/ጄኔራል መንግሥቱ የክብር ዘበኛ ሠራዊትን በትጥቅ፣ በሰው ኃይል፣ በልዩ ልዩ መገልገያ መሣሪያዎችና ተሽከርካሪዎች፣ በበጀት፣ በአደረጃጀትና በሥልጠና ከሌሎች አቻ ኃይሎች ሁሉ ልቆ እንዲገኝ ያላደረጉት ጥረት አልነበረም:: ጥረታቸውም ከንጉሡ ጋር በነበራቸው ቀረቤታ በመታገዙ ተሳክቶላቸው እንደነበር ብዙዎች ይመሰክራሉ::[28] ለምሳሌ ስለጄኔራል መንግሥቱ የሻለቃ አንጋጋው የሚከተለውን ይላሉ::

> ብርጋዴር ጄኔራል መንግሥቱ እጅግ የነቃ ወታደራዊ አቋም የነበራቸው የሠልፍ ሰው፣ በሰውነት ይዘት፣ በአቋም፣ በአለባበስና በቅልጥፍና ተወዳዳሪ የሌላቸው የወታደር ተምሳሌት የሆኑ መኰንን ነበሩ:: መንግሥቱ ንዋይ በክብር ዘበኛ የጄኔራል ሙሉጌታ ቡሊ የቅርብ ረዳት ሆነው ሲሠሩ፤ ከዚያም ወዲህ የክብር ዘበኛን በጥብቅም ሆነ በዋና አዛዥነት እያስተዳደሩ ሳለ፤ ሠራዊቱን ዕለት ተዕለት በመስክ

[28] ስለ ጄኔራል መንግሥቱ አሠራርና ጠቅላላ ባሕሪ፣ በቅርበት ከሚያውቋቸው ብዙ ሰዎች በርካት ያሉ የተለያዩ መረጃዎችን ለማግኘት ችዬአለሁ:: ከክብር ዘበኛ የሻለቃ በኋላ (ኰሎኔል) አንጋጋው ኃይሌ ያገኘሁት መረጃ ግን ከሌሎቹ ከተገኙት መረጃዎች አብዛኛውን የያዘ በመሆኑ አንዳንድ ማሻሻያና ለውጦች ካደረግሁበት በስተቀር፤ በዚህ ምዕራፍ ለማቀርበው ፍሬ ነገር ሙሉ ለሙሉ ተጠቅሜበታለሁ:: ኰሎኔል አንጋጋው በቃል ከሰጡኝ ማብራሪያ በተጨማሪ በጽሑፍ የሰጡኝ ፴፯ ገጽ ወረቀት ጽሑፍ ነው::

> እየተከታተሉ የሠልፍ፣ የጅምናስቲክ እንዲሁም የጦር ታክቲክ ብሎም የቴክኒክ ሥልጠናን ስለሚቆጣጠሩ፤ የያንዳንዱን መኮንን፣ አልፎም የወታደሩን፣ ሥልጠናና ዕድገት የመገምገም ችሎታ ነበራቸው። በዚህ ሒደት እያንዳንዱን መኮንን ወይም ወታደር ስም፣ መልክና ምግባሩን ጨምሮ ያውቁታል። ሠራዊቱም ያውቃቸዋል።
>
> መንግሥቱ ንዋይ የተፈጥሮ ደግነት ስለነበራቸው፤ ለተቸገረ ሁሉ መለገሥ ያዘወትራሉ። በእናታቸው ከደጃዝማች ገርማሜ ከወረደ ሠፊ የገጠር ርስት በሚያገኙት ገቢ በመደገፋቸው እየተዳደሩ እንጂ ደሞዛቸውን በቅድሚያ እየተበደሩ ለተቸገረ በመርዳት በወር መጨረሻ ወደ ብር አንድ መቶ ብቻ በጥሬ ገንዘብ ቀርቶ እሱኑ ብቻ እንደሚቀበሉ፤ መኮንኑ ብቻ ሳይሆን ሠራዊቱ በሙሉ ያውቃል። መንግሥቱ ንዋይ ከሥራ ውጭ ዘፈን መስማት፣ ዳንስና ጨዋታ ያዘወትራሉ። በግል ቤታቸውም መደገስ፣ ማብላት፣ ማጠጣትና መጫወት ይወዳሉ።

በሌላ በኩል ደግሞ የሻለቃው የጄኔራል መንግሥቱን አመራር አከራካሪ ስላደረገው ሁኔታ ሲገልጹ፡-

> ጄኔራል መኮንኑ በሠራዊት አዛዥነታቸው ሥልጣን አማክለው መያዝ ሲገባቸው፤ ዴሞክራሲ እያሉ የአስተዳደሩን ተግባር ለስታፎች ስለሚተዉ፤ በዚህ መስክ የሚከሰተው ችግር ውስብስብ ይሆን ነበር። በዚህ ምክንያት የሚከሰተው ድክመትም ያስወቀሳቸው ነበር። መንግሥቱ የክብር ዘበኛን አዛዥነት ከተረከቡ በኋላ መኮንኖችን እንደየችሎታቸው በሥራ መስክ ማሠማራትና በሚያሳዩት የሥራ ውጤት ማስመሰገንም ሆነ ማሸም እንዲሁም ሁሉንም በየመልኩ ማስተዳደር ሲገባቸው፤ በሚያደርጉት አድሎና አንዱን በአንደኛው የማስጠቃት ዘይቤ የመኮንኖችን መንፈስ ማሸፈት ጀመሩ። ይህ ዓይነት አመራር ያበሳጫቸው አንዳንድ መኮንኖች በሚችሉት መንገድ ሁሉ እየተጠቀሙ ብሶታቸውን ለግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ያሰሙ ነበር።[29]

ጄኔራል መኮንኑ የአመራር ይዞታቸው ባጭሩ ይህን ሲመስል፤ በክብር ዘበኛ ሠራዊት ውስጥ ባሳለፉት ጊዜ ሁሉ ግን ለንጉሠ ነገሥቱና መንግሥታቸው እጅግ ታማኝ እንደ ነበሩ ይነገራል። በታማኝነት ከፈፀሙዋቸው የሚከተሉት ይጠቀሳሉ። አንደኛ በ፲፱፻፴፭ ዓ.ም. አካባቢ በደጃዝማች ታዬ ጉልላቴ አቀነባባሪነት በጃንሆይ መንግሥት ላይ በመኳንንቱ የተውጠነጠነውን ሤራ ለማክሸፍ ከተሰለፉት ታማኞች መኸል አንዱ ነበሩ። ሁለተኛ በ፲፱፻፴፮ ዓ.ም ደጃዝማች በላይ ዘለቀና ደጃዝማች ማሞ ኃይለ ሚካኤል ከታሠሩበት ከታላቁ ቤተ መንግሥት የጥበቃውን አካል አጥቅተው በወጡበት ወቅት ከአዲስ አበባ አካባቢ ሳይርቁ የከተማውን ዙሪያ በጦር ኃይል በማስከበብ ዱካቸውን የሚከተል ተወርዋሪ የጦር ኃይል በማዘጋጀት፣ አስይዘው እጅግ አስጊ የነበረውን የደም መፋሰስ ዕቅድ ካከሰሙት አንዱ ነበሩ። ሦስተኛ በ፲፱፻፵፪ ዓ.ም.

[29] ዝኒ ከማሁ

በቢትወደድ ነጋሽ በዛብህ አነሣሽነት በአሥጊ ደረጃ ላይ የነበረው የአርበኞች ሤራ እንደታወቀ፤ በጦር ኃይል ለማክሸፍ በግንባር ቀደም የተሰለፉና ዐመፀኞቹም በደጃዝማች ገረሱ ዱኪ መኖሪያ ቤት ተሰብስበው እያሉ አስከብበው እጅ እጃቸውን በመያዝ ለፍርድ እንዲቀርቡ ካደረጉት አንዱና ዋናው ነበሩ። አራተኛ ስመጥር የነበሩት ሜጀር ጄኔራል ሙሉጌታ ቡሊ የጦር ሠራዊቱ ኤታማዦር ሹም ሆነው ከተሾሙ በኋላ፣ የጦር ሠራዊቱ ሕይወት እንዲሻሻል በማድረጋቸው በሠራዊቱ ዘንድ ባገኙት ተደናቂነት ቅናት ባደረባቸው አሉባልተኞች መንግሥት ሊገለብጡ ነው እየተባለ ሲናፈስ፤ የስለላውን መረብ ከዘረጉት አንዱና ዋነኛው ጄኔራል መንግሥቱ ነበሩ።

እነዚህ ነጥቦች ለምሳሌ ያህል ይቅረቡ እንጂ፤ ጄኔራል መንግሥቱ በክብር ዘበኛ ነታቸው የሚጠበቅባቸውን ሁሉ በእውነትና በንፁሕ መንፈስ ይፈፀሙና ያስፈፀሙ ነበሩ። መንግሥቱ ለጃንሆይ ጥበቃ ከሚፈፅሙት ሁሉ እጅግ የሚደነቀው፣ ጃንሆይ በሚሔዱበት ቦታ ተከታይ ሲሆኑ ለማረፊያ የተመደበላቸውን ቤት እየተዉ አልጋቸውን ከጃንሆይ መኝታ በር ላይ መዘርጋታቸው ነበር። ጃንሆይም በበኩላቸው መንግሥቱን የሚመለከቷቸው አባት ለወለደው ልጅ ከሚያደርገው የፍቅር አስተያየት ምንም ባልተለየ መልኩ ነበር ቢባል ማጋነን አይሆንም። እንዲሁም፣ መንግሥቱ በጃንሆይ ፊት እንደ በኩር ልጅ የሚዝናኑ እንደነበር በጊዜው ያስተዋሉ ሁሉ የሚያወሱት ነው። ይህን የተመለከተ ሁሉ፣ መንግሥቱ ንዋይ ከቤተ መንግሥቱ የትውልድ ሐረግ ይኖራቸዋል ከሚል ግምት ላይ ይደርሳል። ከዚህ ሌላ ቤተ መንግሥቱ ጄኔራል መንግሥቱን የበለጠ ለማቅረብ ፈቃድ እንዳለው የሚያሳይ አንድ ዓይነት ግንዛቤ ነበር። ይኸውም ከጃንሆይ የልጅ ልጅ አንደኛዋ በአንድ ወቅት ከመንግሥቱ ጋር የቅርብ መፈቃቀድ ፈጥረው በፈረስ ሽርሽር ሲወጡና ወደ መንግሥቱ መኖሪያ ቤት ሲመላለሱ መታየታቸው ነበር። ይህ ሁኔታ በወቅቱ ከቤተ መንግሥት የጋብቻ ፈቃድ እንዳለ እንዲገመት አድርጎ ነበር። ነገር ግን በግልጽ ባልታወቀ ምክንያት ግንኙነታቸው ተቋረጠ።

ያም ሆነ ይህ ጄኔራል መንግሥቱ በመጨረሻ ያገቡት የቢትወደድ ታፈረ ተሰማን ልጅ ወ/ሪት ከፈይ ታፈረን ነበር። ብርጋዴር ጄኔራል መንግሥቱ ከሕጋዊ ባለቤታቸው ሁለት ልጆች ያፈሩ ሲሆን፤ ከጋብቻ በፊት ሁለት ልጆች እንደነበሯቸው ይታወቃል። ጄኔራል መንግሥቱ ትዳር የመመሥረታቸው ሁኔታ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የነበራቸውን መቆርቆር አልቀነሰውም። እንዲያውም፣ ለሥርዓቱ በነበራቸው ቅርበት ሳቢያ የአስተዳደርና የሕግ በደል ስለደረሰባቸው ወገኖች ለንጉሡ የሚያቀርቡዋቸው ሪፖርቶችና አስተያየቶች አንዳችም ፋይዳ ሳያገኙ መቅረታቸው ውስጥ ውስጡን እየበላቸው፤ የፍርድ መታጣቱ ለሕዝብ የነበራቸውን መቆርቆር (ፍቅር) ይበልጥ አጠናክሮታል። በአንጻሩ፣ ጃንሆይ ለመንግሥቱ የነበራቸው አመለካከት ግን እየጠነከረ ሔደ እንጂ ቀንሶ አልታየም።

ጄኔራል መንግሥቱ ወደኋላ ላይ የቅሬታ ምልክት ያሳዩ እንደ ነበር አንዳንድ ምልክቶች ታይተዋል፡፡ መንግሥቱ በመኖሪያ ቤታቸው በየአሥራ አምስት ቀን ቅዳሜ ምሽት ከወጣቶች ጋር የራት ግብዣና የዘፈን ምሽት ስለሚያደርጉ፤ በዚህ ጊዜ የሚዘወተረው ዘፈን በ፱ አለቃ ካሣ ተሰማ የሚዘፈነው «እንዲያው ጉምጉም» የሚለው እና በጥላሁን ገሠሠ የሚዜመው "አልቻልኩም" የሚሉት ነበሩ፡፡ የኮሎኔል አንጋጋው ለምሳሌ "ጄኔራል መንግሥቱ ለጃንሆይ ሕይወትም ሆነ መንግሥት እጅግ የታመኑ ከመሆናቸው አንጻር ከ፲፱፻፶፪ ዓ.ም. መባቻ ጀምሮ ይታይባቸው ከነበረው የፀረ ዘውድ አቋም ጋር ስመዝነው መንግሥቱ ምን ዓይነት ችግር ተፈጠረባቸው የሚል ሐሳብ ይመላለስብኝ ነበር" ይላሉ፡፡[30] እንደሳቸው አገላለጽ በመጀመሪያ ደረጃ የጄኔራል መንግሥቱ አቋም መለወጥ ጉልህ ማስረጃ የሆነው፤ ከመንግሥት ሥልጣን ከተገለሉት ከጸሐፌ ትእዛዝ ወልደ ጊዮርጊስ ወልደ ዮሐንስና ከብላታ (ደጃዝማች) ታከለ ወልደ ሐዋርያት ጋር የአስተሳሰብ ወገናዊነትን ማሳየታቸው ነበር፡፡ ቀጥሎም በጃንሆይ ዙሪያ ስለሚገኙት የካቢኔ አባላት፣ ለምሳሌ እንደ እነ ክቡር አቶ መኮንን ሀብተ ወልድና ጄኔራል ሙሉጌታ ቡሊ የመሳሰሉት ላይ የስም ማጥፋት ዘመቻ ማድረጋቸው ነው፡፡ በዚህም ሰዎቹ የክብር ዘበኛን እንደሚጨቁኑ ያነሱ ነበር የሚለውን የኮሎኔል አንጋውን አነጋጋር ልብ ይሏል፡፡ ይሔው ቅስቀሳ መቀጠሉን በ፲፱፻፶፫ ዓ.ም. መጀመሪያ የክብር ዘበኛ ሠራዊት በጃንሆይ ላይ ቅሬታ እንዲያድርበት በማድረግ፤ በዕድገትና በደሞዝ እንደተበደለ፣ ለዚህም የንጉሠ ነገሥቱ ፈቃድ በመታጣቱ ምክንያት እንደተከሰተ ጄኔራል መንግሥቱ ውስጥ ውስጡን ያካሒዱት ስለነበረው ቅስቀሳ በመጥቀስ ያስረዳሉ፡፡

> የዚህ ውስጣዊ እንቅስቃሴያቸው ፍንጭ እንዳይገኝም የክብር ዘበኛን የመረጃ መዋቅር ራሳቸው ይዘዋል፡፡ በፖሊስ በኩል ላለው ደግሞ፣ አዛዡን ጄኔራል ጽጌ ዲቡን በጥብቅ ጓደኝነት ይዘዋል፡፡ የአገሪቱ የፀጥታ አቋም የሚመራው በሌ/ኰሎኔል ወርቅነህ ገበየሁ ስለነበር፤ በዚህም በኩል ወርቅነህን ይዘዋል፡፡
>
> በልዩ የንጉሠ ነገሥቱ ካቢኔ እንዳይሰማ በጊዜው ልዩ ኤታማዦር የነበሩትን ሜጀር ጄኔራል ሙሉጌታ ቡሊን በመንግሥት ግልበጣ ተጠርጣሪ አድርገው በንጉሠ ነገሥቱ የጥቁር ነጥብ መዝገብ ላይ የመጀመሪያው አድርገዋቸዋል፡፡ ከዚህ ውጪ በክብር ዘበኛ ውስጥ የነበሩትን በሳል መኮንኖች ከሙሉጌታ ቡሊ ጋር ግንኙነት አላቸው፡፡ አላሠራ አሉኝ የሚል ምክንያት እየፈጠሩ ለጃንሆይ በማመልከት በሲቪል ሹመት፣ ማለትም "የአውራጃ ገዥ" እያሰኙ በማሸም ከክብር ዘበኛ ብቻ ሳይሆን፤ ከአዲስ አበባም ጭምር ርቀው በየጠረፉ እንዲመደቡ አድርገዋል፡፡ ዝቅ ያሉትም ጉርሱም ወደሚገኘው ፯ኛ ሻለቃ እንዲዛወሩ፤ ከዚያም ያለ ጄኔራል መንግሥቱ ፈቃድ ወደ መኸል አገር እንዳይገቡ አድርገው ነበር፡፡ በወርቅነህ ገበየሁ የሚመራው የአገሪቱ የፀጥታ መዋቅር፣ የፖሊስና

[30] የኮሎኔል አንጋጋው ማስታወሻ

የራሱ የክብር ዘበኛው ሪፖርት ሁሉ ‹ለመንግሥት ግልበጣ ያሜራል› በሚል የሚረባረበው በጄኔራል ሙሉጌታ ቡሊ ላይ ነበር። በአንድ ሰው ላይ ይህን ያህል ርብርቦሽ ሲደረግ፤ በአንጻሩ ለጃንሆይ አንዳንድ ግለሰቦች «መንግሥቱ ያሠጋዎታል» እያሉ የሚያቀርቡላቸውን ሀሜት ንጉሡ ጆሮ ዳባ ልበስ ብለውት ነበር። ለምሳሌ፣ ከንጉሠ ነገሥቱ የካቢኔ ሚኒስትሮች ውስጥ "ጃንሆይ የመንግሥቱን ጉዳይ እንዴት ይመለከቱታል?" የሚሉ እንደ እነ አቶ መኮንን ሀብተ ወልድ ያሉ ይጠቀሳሉ። ይህ ቢባልም፣ ለጃንሆይ አብዛኛው የመረጃ መዋቅር ያስመዘገበው የሜጀር ጄኔራል ሙሉጌታ ቡሊን ሒደት በሐሰት ቅባት እያወዛ ስለ ነበር፤ የመንግሥቱን ሲሰሙ "ትኩረቴን ሊያዛቡ ነው ሳይሉ አልቀሩም"።[31]

ይህ በእንዲህ እንዳለ የጄኔራል መንግሥቱን እንቅስቃሴ ግን ከወንድማቸው ከነገርማሜ ጋር ማያያዝ የተለመደ ነው። ይህ በስፋት የሚነገረውና ጄኔራል መንግሥቱ በወንድማቸው በገርማሜ ተቀስቅሰው ነው የሚለው አስተያየት ግን አሳማኝ አይደለም። ከተለያዩ መረጃዎች እንደሰማሁትና እንደተገነዘብኩት የጄኔራል መንግሥቱ ለለውጥ መነሣት እንደሚባለው በወንድማቸው ውትወታ ሳይሆን፣ ነገሮችን በጥሞና ከመመልከት አንጻር በሕዝብ ላይ የሚደርሰውን በደል ዐይናቸውን ገልጠው ከመመልከት የመነጨ ነበር። በመሆኑም፣ ከሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ ጋር በመሆን በሥራቸው ምክንያት ይበልጥ የሚያውቁትን የመለዮ ለባሹን ክፍል በሚመለከት፣ በጦሩ ልዩ ልዩ ክፍል አባላት መካከል የነበሩ አንዳንድ የአድልዎ አሠራሮች እየከረሩ መጥተው ወደ አደገኛ ደረጃ እየደረሱ መሆናቸውን በመጥቀስ፤ እነዚህ አሠራሮች የሚሻሻሉበት እርምጃ እንዲወሰድ ለንጉሠ ነገሥቱ አጥብቀው አሳስበው ነበር። ይህ ሃሳባቸው ግን እንደሌላው ማናቸውም ቅን ሐሳብ በንጉሡ ዘንድ ተቀባይነት ሊያገኝ ያልቻለ እውነታ ሆኗል።

ብርጋዴር ጄኔራል መንግሥቱ ንዋይ በሥርዓቱ ላይ የመረረ ትችት ያነሱ የነበረው በተለይ የፍትሕ ሂደቱን አስመልክቶ ነበር። የጄኔራሉ ልዩ ረዳት በመሆን ለብዙ ጊዜ አብረው የሠሩት ወዳጄ ኮሎኔል እዮብ ገብረ ሚካኤል ይህን አስመልክቶ የሚያነሱት ሐሣብ የጄኔራሉን አስተያየት በደንብ የሚያሳይ ስለሆነ እንደሚከተለው አቀርበዋለሁ።

> ... ጄኔራል መንግሥቱ ንዋይ አዘውትረው የሚጠቅሱት አንድ ምሳሌ አለ። እሱም ‹አንድ ሰው እራሱ ሊሸከመው ያልቻለውን ምስጢር ለሌላው ሲነግር ‹ልብ አድርግ! ይሄ የምነግርህ ነገር ብርቱ ምስጢር ነው፤ ለሌላ ሰው እንዳትናገር› ይላል። ይህ ሞኝነት ነው። እሱ አልችል ብሎ ለሌላ ሰው ከተናገረ ያኛውስ ያው እንደሱ ሰው አይደለም ወይ? ምስጢር ለሰው ከተነገረ መውጣቱ እንዴት ይቀራል ብሎ ያስባል› ይሉ ነበር።

---

[31] ዝኒ ከማሁ፣ የኮሎኔል አንጋጋው ለምክትል ጸሐፊ ትእዛዝ ገብረወልድ እንግዳወርቅ መረጃ እያቀበሉ ለንጉሡ መረጃ ይሠጡ ነበር የሚል ሀሜት ይናፈስ ነበር።

> ከዚህ የተነሣም እሳቸው መፈንቅለ መንግሥት ላካሂድ አስቤአለሁ ብለው አንድ ቀን ግልጽ አድርገው አጫውተውኝ አያውቁም። ነገር ግን፣ ብዙ ጊዜ በሥራ ጉዳይ ፋይሎች ይዤ ወደ ቢሮአቸው ስገባ፤ በተለይም ከሰዓት በኋላ፣ የፋይሎች ጉዳይ ቀርቶ በአገሪቱ ስላለው የፍርድ መጓደልና የአስተዳደር በደል ደጋግመው ያወሩ ነበር።

ብለው ስለፍትሕ የነገሯቸውን እንደሚከተለው ቀጠሉ፡-

> ‹አየህ! ቀደም ባለው ጊዜ አገሪቱ ለፍትሕ አሰጣጥ ስትመራ የኖረችበት ባህልና የፍትሐ ነገሥት ሕግ ነበራት። ከሥርም ይሁን የይግባኝ ዳኝነት ሲታይ ከሳሽና ተከሳሽ ሦስት ሦስት ሰዎች ይመርጣሉ። ወንበሩ (ዳኛው) ከመኸል ሆኖ ችሎት ተቀምጠው የግራ ቀኙን ጉዳይ በሚገባ አድምጠው ሲያበቁ፣ ፍርድ ተችዎቹ አላግባብ ብፈርድ ይፍረድብኝ፣ ባደላ ያድላብኝ፣ እኔ የምናገረው አምላክ ያሳየኝን መንፈስ ቅዱስ የገለጸልኝን ነው በማለት፣ ከቀደመ ተመሳሳይ ሁኔታና ብይን ጋር እያገናዘቡ፣ የተሰማቸውን የፍርድ ሐሳብ አሰምተው ይጨርሳሉ። ዳኛው የተቺዎቹን ሐሳብ ከሰማ በኋላ የራሱን ሐሳብ በመጨመር አብዛኛው ያሰማውን የፍርድ ሐሳብ በማጠናከር ወይም በመለየት ባጭር ጊዜ ፍርድ ይሰጣል። በዚህ ሥርዓት የፍርድ አሰጣጥ ብዙውን ጊዜ ከሳሽና ተከሳሽ ረክተው ክርክሩ ይቆማል። ፍርዱ ያልተስማማው ከስንት አንዱ ወደሚቀጥለው ደረጃ ይግባኝ ብሎ ይቀጥላል። የዚያም ሂደት እንደመጀመሪያው ነው። የዚህ ዓይነቱ የፍርድ አሰጣጥ ብዙዎችን ያሳተፈ፣ ግልጽነት ያለበት፣ በመሐላ የተሰጠ የፍርድ ውሳኔ ስለሆነ ሙሉ በሙሉ ከአድሎና ከጉቦ የጸዳ ነው ባይባልም፣ አድሎን ያጠበበ እንደነበር አያጠራጥርምና ክርክሩም በዚህ ፍርድ ያበቃ ነበር። ‹ከነፃነት መመለስ በኋላ ኢትዮጵያ ስትጠቀምበት የነበረውን የራሷን የፍትሐ ነገሥት ሕግ እና ባህላዊውን የፍርድ ሥርዓት ዘመናዊ ለማድረግ እና ከሠለጠነው ዓለም የፍርድ ሥርዓት ጋር ለማመሳሰል፣ ጃንሆይ የወንጀለኛ መቅጫና የፍትሐ ብሔር ሕግ አጽፈው ለሕዝብ አገልግሎት እንዲውል አድርገዋል። ሕጉ እና ዐላማው መልካም ሆኖ ሳለ፤ በአፈፃፀም ግን በፊት ከነበረው የፍርድ አሰጣጥ ጋር ሲነጻጸር በእጅጉ የተዛባ፣ ለጥቅም ሲባል አድሎ የበዛበት፣ ብዙ ዓመታት የሚፈጅ፣ አሰልቺ፣ ተስፋ አስቆራጭና ቤተሰብ በታኝ እየሆነ ሔደ።

ብለው ከነገሯቸው በኋላ በ፲፱፻፹፰ ዓ.ም. የተሻሻለው ሕገ መንግሥት መውጣት በኋላ ስለተከሰተው ችግር ደግሞ ጄኔራሉ የከፍተኛ፣ የጠቅላይ ፍርድ ቤት የፍርድ ምርመራ (አጣሪ) እና ሰበር ሰሚ፣ የዙፋን ችሎት የሚባሉ የዳኝነት ማያ የችሎት ደረጃዎች መቋቋማቸውን፣ የእነዚህ የይግባኝ ደረጃዎች መብዛት ለአፋጣኝና ትክክለኛ ፍርድ ማግኘት ከሰጠው ጥቅም ይልቅ ያደረሰው ጉዳት ጉልቶ መታየቱን፣ ለምሳሌ አንድ የመሬት ባለቤት ከቅርብ ዘመዱም ሆነ ከሌላ ሰው ጋር በሚያነሣው ክርክር ወይም የዘመኑ ባለሥልጣኖች የሰውን ድንበር እየገፉ ወይም እየቀሙ ባለቤቱን ወንጅለው የማሳሠሩና የማስገደሉ ግፍ እየጐላ ስለሔደ፣ በደል የደረሰበት ጉዳዩን በሕግ ለመጨረስ አደባባይ መውጣቱ ስላስከተለው ችግር በቁጭት እንደነገሯቸው

ኮሎኔል እዮብ ያስታውሳሉ፡፡ የተሚጋቾች ችግርንም አስመልክቶ የጄኔራሉ ንግግር ተሚጋቾቹ ክሳቸውን ሕጉ በሚፈቅደው ፍርድ ቤት ይጀምሩና በይግባኝ ካንዱ ወደ ሌላው ደረጃ እየተረማመዱ ሙግታቸውን መቀጠላቸውን፣ በተለይ ወደ መጨረሻ የይግባኝ ደረጃ ያሉት ችሎቶች የሚገኙት በአዲስ አበባ ብቻ በመሆኑ፤ ይግባኝ ባዩም ሆነ መልስ ሰጪ ሳይወዱ አዲስ አበባ ድረስ መጥተው መንገላታት ግድ እንደሚሆንባቸው፣ በዚህ አኳኋን እስከ ዙፋን ችሎት የሚቀጥለው ይግባኝ እስኪታይ ድረስ፤ ሁለቱም ወገኖች የኑሮ ችግር ለመቋቋም ራሳቸውን ዝቅ አድርገው በአልባሌ ሥራ በመሠማራትና በችግር በመገረፍ ከ፫-፭ ዓመታት በአዲስ አበባ እንዲያሳልፉ መገደዳቸው ሁሉ ያልተገባ እንደነበር እንደ ነገሯቸው እና የዚህ ሁሉ የአሠራር መዛነፍ ውጤት ችግርተኛውን ሕይወቱን እስኪያሳልፍ የሚያደርሰው መሆኑ የበለጠ ጄኔራሉን የሚያብሰለስል እንደነበር ኮሎኔሉ ጠቅሰውልኛል፡፡

በጄኔራሉ አስተያየት የችግሩ መጠን እንደሚከተለው ነበር፡፡

> ከዚህ ሁሉ ችግርና እንግልት በኋላ የመጨረሻው ፍርድ መስጠቱ ስለማይቀር፣ የተፈረደለትም ሆነ የተፈረደበት ብዙ ዓመታት ከየቤታቸው እርቀው በመቆየታቸው፤ ትዳራቸው ፈርሶና ቤተሰባቸው ተበትኖ፤ ከትውልድ ሥፍራቸውና ከቤተሰባቸው ተለይተው እንደወጡ የሚቀሩት ቁጥር ጥቂት አልነበረም፡፡ ይልቁንም በወንጀል ተከሶ ሞት የተፈረደበት ሰው ፍርዱን ንጉሡ ካላፀኑት ስለማይፈፀም ከ፫ እስከ ፭፮ ዓመታት በእሥር ቤት ኑሮ ሥጋው ካለቀና አጥንቱ ከመነመነ በኋላ የሞቱ ፍርድ ይፈፀምበታል፡፡ ይህ የሚሆነው ላንድ ጉዳይ ውሳኔ ሳይሰጥ ለብዙ ዓመታት ስለሚጐተት ነው፡፡
>
> የኢትዮጵያ ሕዝብ ከምንም በላይ የሚረካበትና ትልቅ አለኝታ አድርጐ የሚጠብቀው ትክክለኛ ፍርድ በዚህ አኳኋን እየጠፋ ሕዝብ ለችግርና ለእንግልት ቢዳረግም፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለዳኝነት ከፍተኛ ክበሬታ የመስጠት ባህል ስላለው፤ ተስፋ ባለመቁረጥ ትክክለኛ ፍርድ እንዲሰጥ አጠንክሮ አቤት ማለቱን አላቋረጠም፡፡ ሆኖም፣ የሕዝቡን ትክክለኛ ፍርድ የማጣት ብሶት እንደ ችግር የማያዩት ባለ ጥቅሞች፣ ችግሩን ለማቅለል ጥረት ስለማያደርጉ በኢትዮጵያ የትክክለኛ ፍርድ አለመኖር የመንግሥት አቋም ሆኖ ታወቀ፡፡ ይህ ሊሆን የቻለው የአስተዳደር ሥርዓቱ በአገር አስተዳደርና በፍርድ ሥራ ላይ የሚመደቡት ሰዎች አብዛኞቹ በዕውቀት፣ በትምህርት፣ በልምድ በዳበረ የሥራ ችሎታና በምግባራቸው፤ ታይተው፣ ተመዝነውና ብቁነታቸው ተረጋግጦ ሳይሆን፤ ለሹመት ከሚያቀርቧቸው ጋር ባላቸው ዝምድና፣ ጋብቻና የጥቅም ግንኙነት ትሥሥር አንጻር እየታየ በመሆኑ ነው፡፡ እነዚህ ሰዎች የሥልጣናቸው ዋስትና ከበላዮቻቸው ጋር ያላቸውን ግንኙነት ማጠናከር መሆኑን ስለሚያውቁ፤ ለዚህ የሚረዳቸውን ገንዘብ ከከሳሽም ሆነ ከተከሳሽ ላይ እንደመተያያ ጉቦ ‹አንተ መጭ ብለህ ብትመጣ፣ እሱ ብር ብሎ ቀደመህ› እያሉ ፍርድን እንደ ዕቃ ተመን እያወጡለት ተሸጠ፡፡ በዚህም ሕዝቡን አንገላቱት፣ ጋጡት፡፡ ፍርድ ያጓደለ ቢበዛ ፍርዱን መሻር እንጂ፤ ላደረሰው በደል ወይም ጉዳት ተጠያቂ ሆኖ በሕግም ሆነ በአስተዳደር

የተቀጣ የለም። አለ ቢባል ከሺህ አንድ ይገኝ ይሆናል። ሥርዓቱ ከላይ እስከታች እንዲህ በመሆኑ፤ ‹ፍርዴ ይገለበጣል እንጂ፤ ጀርባዬ አይገለበጥም› በሚል ትምክህት ፍርደ ገምድልነታቸውን ስለቀጠሉበት፤ ዛሬ ይግባኝን እንደ መፍትሔ አድርጐ ከሚንከራተተው ባለጉዳይ መካከል ትክክለኛ ፍርድ ለማግኘት የሚታደለው እጅግ በጣም ጥቂቱ ነው። በእርግጥ ሕግን የጠበቁ፣ ዳኛና ዳኝነትን ያስከበሩ፣ ለሹመት፣ ለሀብትና ለንብረት ማፍሪያ ኀሊናቸውን ያላሳደፉ ሕዝብ የሚወዳቸውና የሚያከብራቸው ጥቂት ምስጉንና ክቡር ዳኞች አሉ።›

ብለው በመዘርዘር ይነግሯቸውና፤ በዚህ ላይ ሲከራከሩ እስከ ምሽቱ ሁለት እና ሦስት ሰዓት ድረስ ያመሹ እንደ ነበር ኮሎኔል እዮብ ይገልጻሉ።

እንደ ኮሎኔል እዮብ ጀኔራል መንግሥቱ ስለጉዳዩ ባነሱ ቁጥር በቁጭት ያናግራቸው የነበረው በክብር ዘበኛ ጠቅላይ መምሪያ ጽሕፈት ቤትና በገነተ ልዑል ቤተ መንግሥት ያሁኑ ዩኒቨርስቲ በር መካከል በነበረው ክፍት ሜዳ ቁጥሩ ከ፪፤ እስከ ፫፤ የሚገመት ሕዝብ ለአቤቱታ ፊሶ ይውል ያድር የነበረ መሆኑ ነው። ኮሎኔል እዮብ ስለዚሁ ሁኔታ በዝርዝር ያጋጠማቸውን ሲገልጹ እንዲህ ይላሉ።

> አንድ ቀን እንደውም በክርክራችን መኻልም እኔን እነሱን ወደሚያሳየው መስኮት ጠርተው ‹ይኸውልህ! ይህ የሚያሳይህ በአገሪቱ የአስተዳደርና የፍርድ በደል መግዘፉን ነው። ይህ ሕዝብ እኮ የሚመራው አጥቶ እንጂ የአስተዳደር ለውጥ ከጠማው ብዙ ጊዜ ሆኖታል። ያጣው የሚመራው ነው። አይመስልህም?› ብለው ዞረው ጠየቁኝ። እኔም ‹የኢትዮጵያ ሕዝብ እኮ በዘውድ የሚያምን ነው። ለምሳሌ በአገር ቤት የተለያዩ የከብት መንጋዎች በበጋ ጊዜ ውሃ ለመጠጣት ከተለያየ አቅጣጫ መጥተው ወንዙ ውስጥ ገብተው ከጠጡ በኋላ በአካባቢያቸው ከሚገኙ የዋርካ የዋንዛ ወይም ትንሽ የሾላ ዛፍ ሥር ተሰብስበው ይጠለላሉ። ፀሐይ በረድ ሲልም በእረኞች ቅስቀሳ ወይም በራሳቸው ፈቃድ ሁሉም ወደየመጡበት ይሄዳሉ። የኢትዮጵያ ሕዝብም እንደዚሁ አንድ የሚያሰባስበው ዘውድ ይፈልጋል› በማለት ብዙ እንነጋገር ነበር። ከዚህ ባለፈም በቀጥታ የናስርን የመፈንቅለ መንግሥት ታሪክ ደጋግመው ያነሡ እንደነበርና አጥብቀውም ያደንቁት እንደነበር አስታውሳለሁ። አልፎ አልፎም በኃይል ከተነፈሱ በኋላ ‹ያለምንም ደም ጠብታ የመንግሥት ለውጥ› ይሉ ነበር።[32]

የጀኔራል መንግሥቱ ሰውን ወደ መፈንቅለ መንግሥቱ መሳቢያ ሥልት አካሔድ እንደ ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ ዐውቀህ ድረስበት ሥልት እንደነበር ይህ ውይይትና አነጋገር ያረጋግጣል። ይህንንኑ ጉዳዩን በምስጢር የመያዝ አዝማሚያቸውን የሚያመለክት ትውስታቸውን የነገሩኝ ኮሎኔል እዮብ የሚጨምሩት ማረጋገጫም አላቸው።

---

[32] ኮሎኔል እዮብ ገብረ ሚካኤል አስተያየታቸውን በስምንት ገጽ ጽፈው የሰጡኝ ብቻ ሳይሆን በቃልም ማብራሪያ ስላከሉበት በእጅጉ ጠቅሞኛል።

አልፎ አልፎ በ፲ እና ፲፭ ቀናት እና በበዓላት ጊዜ በርካታ የክብር ዘበኛ መኮንኖች ባሉበት እያንዳንዱ የክብር ዘበኛ ብርጌድ ወይም ሻለቃ ተራ በተራ በሚያዘጋጁት የመዝናኛ ድግስ መኮንኖች እየተሰበሰቡ እንዲጋበዙና በቅርብ እንዲገናኙ ፕሮግራም ተይዞ ለሁለት ወራት ያህል ተካሂዶ፤ በመኻል በመንግሥት አቋሙ ተብሎ ተቋረጠ። ከመቋረጡ በፊት በዚህ ግብዣ ላይ ጄኔራል መንግሥቱ ንዋይ፣ ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ ገበየሁ፣ ኮሎኔል ሰሎሞን ከድርና ሌሎችም ከፍተኛ የክብር ዘበኛ መኮንኖች ይሳተፉ ነበር። ይህ አብሮ መብላትና መጠጣት የመቀራረቢያ ፕሮግራም ከመሆን በቀር ምንም ዓይነት ፖለቲካ ነክ ነገር አይነሳበትም ነበር።

እንቅስቃሴው በምስጢር ቢያዝም ምልክቶቹ እንደነበሩ ግን ሁዋላ ላይ ለመገንዘብ የሚረዱ ጠቋሚ ነገሮችን መንቀስ ይቻላል። ለምሳሌ ጥቂት ምርጥ የክብር ዘበኛ መኮንኖች የሚገኙበት ከ፲፱፻፶፫ ዓ.ም. የመጀመሪያው ሩብ ከመስከረም እስከ ታኅሣሥ ከቀኑ አሥራ አንድ ሰዓት በኋላ በጄኔራል መንግሥቱ ቢሮ ስብሰባ ይደረግ ነበር። ስብሰባው ላይ ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ እየመጡ ‹ጥናቱ ሲጠናቀቅ ለግርማዊ ጃንሆይ አቅርቤ ማሻሻያውን አስገኛለሁ› በማለት ለተሰብሳቢዎች የተለያዩ የጥናት ርእሶች ይሰጡ ነበር። ርእሶቹም የአስተዳደር በደል፣ የፍርድ መጓደልና የኢኮኖሚ ድቀትን የተመለከቱ ነበሩ። በዚህ መሠረት በየርእሰ ጉዳዮቹ በማስረጃ የተደገፈ ሐሳብ እየተሰባሰበ ሪፖርት እንዲጠናቀር በመደረጉ በመንግሥቱ አስተዳደር ላይ ስለነበረው ጉድለት ሁሉ ዝርዝር መረጃ ተዘጋጅቶ ነበር።

ኮሎኔል እዮብ እንደሚገልጹት ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ ‹ግርማዊ ጃንሆይ በማስረጃ የተደገፈ የሥራ ጉድለት ከቀረበላቸው እንዲስተካከል ሙሉ ፈቃደኛ ናቸው። እመኑኝ፣ እኔ አስፈፅማለሁ› በማለት ጥናቱ በአምስት ምርጥ መኮንኖች እንዲካሔድ ያደርግ እንደነበር ይገልጻሉ። በዚህ የአጥኚ መኮንኖች ቡድን ውስጥ፣ የሻለቃ አዲስ ዓለም ጽጌም ተካፋይ እንደነበርና የአገኛቸው በብርቱ ማስረጃ የተደገፉ ብዙ አሳዛኝና አናዳጅ አድራጎቶችን፣ "ከእያንዳንዳችን የውስጥ ቁጭት ጋር አያይዘን በመግለጽ ፶፯ ገጽ የያዘ አንድ ጥራዝ ሪፖርት አዘጋጅተን ላዘዙን መኮንኖች ሰጥተናል" ሲል ወህኒ ቤት ሳለን አጫውቶኛል።

እንግዲህ ጄኔራል መንግሥቱ ለንጉሡ የነበራቸው ታማኝነት በሚያዩት የአስተዳደር በደልና የፍትሕ መጓደል እየተሸረሸረ መሄዱን ዓየን። እሳቸውም ቀስበቀስ በስውርም በግልጽም የክብር ዘበኛውን ጥያቄ መደገፍ እያሳዩ ሔዱ። ከዚህ ጋር በተያያዘ ለመፈንቅለ መንግሥቱ እንደምክንያት በተደጋጋሚ የሚነሳው፤ በጦሩ ውስጥ ይታይ የነበረው ልዩነት ነበር። ሐረር የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የጦር አካዳሚ ምሩቅ ምክትል የመቶ አለቃ ደመወዝ ብር ፩፻፷፭ እና የቀለብ ድርጎ ብር ዘጠና በድምሩ ፪፻፲፭ ሲሆን፤ የክብር ዘበኛ፣ የጦር ሠራዊትና የፖሊስ መኮንኖች ምክትል የመቶ አለቃ ደመወዝ ብር ፩፻፷፭ ብቻ ነበር። ምክንያቱም፣ በሐረር ጦር አካዳሚ በዕጩ መኮንንነት

የሚገቡት ተመልማዮች፣ በትምህርት ደረጃቸው ፲፪ኛ ክፍልን የጨረሱ እና ኮሌጅ ለመግባት የሚያበቃ ውጤት ያላቸው ሲሆኑ፤ በክብር ዘበኛ፣ በገነት ጦር ትምህርት ቤትና በፖሊስ አባዲና የፖሊስ መኮንኖች አካዳሚ የሚገቡት ደግሞ ከ፬ኛ-፲ኛ ክፍል የደረሱ ተማሪዎች ነበሩ:: ይሁን እንጂ የክብር ዘበኛ መኮንኖች ክርክር ሥልጠናቸው እንደ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሚሊቴሪ አካዳሚ፣ ኮርሱ የሦስት ዓመት ሲሆን፤ የትምህርቱ ደረጃም ከስዊድን የጦር አካዳሚ ጋር እኩል ሆኖ ትምሕርቱ የተሰጠውም በስዊድን የጦር መኮንኖች ራሳቸው በሠለጠኑበት ዓይነትና ደረጃ መሆኑ ነው። ስለዚህ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሚሊቴሪ አካዳሚ ዕጩ መኮንኖችን "እኛ በሠለጠንበት ትምህርት ያሠለጠንም ያስመረቅንም እኛ ሆነን ሳለ፤ ለነሱ ከተወሰነው ደመወዝና አበል የኛ ማነስ የለበትም" በማለት፣ በኅዳር ወር ፲፱፻፶፫ ዓ.ም. በስብሰባ ከተነጋገሩ በኋላ አቋም እንደያዙ በሹክሹክታ ይሰማ ጀመር:: ትንሽ ቆይተው መኮንኖቹ በንጉሠ ነገሥቱ አስተዳደር ላይ ዓመፅ ማነሣሣት ጀመሩ:: አንዳንድ የታወቁ ሰዎችም ነገሩን ሊያበርዱ ወይም ሊገቱ ሞክረው ነበር ይባላል::

በዚህ ጊዜ ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ በክብር ዘበኛ ሠራዊት ውስጥ የመኮንኖች አለመረጋጋት መኖሩንና ሁኔታው የሚያሳስብ መሆኑን ለንጉሡ ገልጾ አስረዳ:: ሌ/ኰሎኔሉ የችግሩ መነሻ ደመወዝ መሆኑን ለሽንገላ ቢገልጽም፤ የውጭ ዲፕሎማቶች ነገሩ ከዚህም ጠለቅ ያለ ሥር የሰደደ እንደሆነ፤ በንጉሡ አመራርና በእርሳቸውም ዙሪያ ባሉት ባለሥልጣኖች ላይ ከፍተኛ ቅሬታ እንዳለ መግለጻቸውን የውጭ ጸሐፍቶች ዘግበውታል:: ከጸሐፊዎቹ አንዱ ሃሮልድ ማርክስ ስለሁኔታው ሲዘግብ በጊዜው የነበሩት አርተር ሬቻርድ የተባሉ አዲስ የመጡ የአሜሪካ መንግሥት አምባሳደር መኮንኖቹ የጠነሰሱት አድማ በደሞዝ ምክንያት ብቻ ሳይሆን፤ ሠፋና ጠለቅ ያለ፣ በግርማዊነትዎና በባለሥልጣናቱ የሥራ ሁኔታ ላይ ጭምር ስለሆነ፤ ትኩረት ቢሰጡት ይሻላል ብለው ሐሳብ አቅርበው እንደነበረ ይገልፃል::[33] ሆኖም፣ ንጉሡ ወደ ምዕራብ አፍሪካና ደቡብ አሜሪካ ለጉብኝት ለመሄድ ተነሥተው ስለነበር፤ ችግሩን ከነሰንኮፉ የሚነቅል እርምጃ ከመውሰድ ይልቅ፤ ለተነሣሣው ዐመፅ ማስታገሻ እንዲሆን ኅዳር ፲፪ ቀን ፲፱፻፶፬ ዓ.ም. በመከላከያ ሚኒስቴርና በምድር ጦር የከፍተኛ መኮንኖች ሹመትና ዝውውር አደረጉ:: ዝርዝሩም:-

፩ኛ) ብርጋዴር ጄኔራል ያዕቆብ ገብረ ልዑል ከእንግሊዝ አገር ሚሊቴሪ አታሼነት የመከላከያ ሚኒስቴር የባጀት ረዳት ሚኒስትር፣

፪ኛ) ብርጋዴር ጄኔራል አማን ሚካኤል አንዶም፣ ከምድር ጦር ስንቅና ትጥቅ መምሪያ አዛዥነት፣ የ፫ኛ ክፍለ ጦር ዋና አዛዥ፣[34]

---

[33] Harold Marcus, ***Ethiopia, Great Britain and U.S.A*** *ገጽ 120-121*

[34] *እዚህ ጋር እኔም እራሴ የማስታውሰው ሌ/ኮሎኔል እንደአልባሌ ነገር አስመስሎ የነገረኝ ነገር አለ:: ነገሩ እንዲህ ነው:: ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ ወደ ም/ኤታ ማዦር ጽሕፈት ቤቱ አስጠርቶኝ ሄጅኩና ከእንግዳው ማረፊያው ግማሽ ሰዓት ያህል ከቆየሁ በኋላ እሱ መለዮውን እያደረገ ከቢሮው ወደ ውጭ ወጣና ተከተለኝ ሲለኝ ተከትየው ወጣሁ:: ከመንገዱ ስንደርስ የታል መኪናህ? ቶሎ አምጣ አለኝና አምጥቼ ከፍቶ ገባና ወደ ስድስት ኪሎ ውረድ አለኝ:: ወረድኩ:: ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሆስፒታል*

፫ኛ) ብርጋዴር ጄኔራል ወልደ ሥላሴ በረካ የ፪ኛ ክፍለ ጦር ዋና አዛዥ፣
፬ኛ) ኮሎኔል አስፋ ደምሴ በ፩ኛ ክፍለ ጦር የ፫ኛ ብርጌድ አዛዥ፣
፭ኛ) ኮሎኔል በለጠ አበበ የ፫ኛ ክፍለ ጦር ኤታማዦር ሹም፣
፮ኛ) ኮሎኔል ጽጌ በሻህ የ፫ኛ ክፍለ ጦር ም/ኤታማዦር ሹም፣
፯ኛ) ኮሎኔል ሽፈራው ተሰማ ከገነት ጦር ት/ቤት አዛዥነት የ፩ኛ ክፍለ ጦር ኤታማዦር ሹም፣
፰ኛ) ኮሎኔል ወርቁ መታፈሪያ የ፪ኛ ክፍለ ጦር ኤታማዦር ሹም፣
፱ኛ) ኮሎኔል አበበ ተፈሪ የጦር ኃይሎች ረዳት ኤታማዦር ሹም፣
፲) ኮሎኔል ጽጌ ገዝሙ የምድር ጦር ረዳት ኤታማዦር ሹም፣
፲፩ኛ) ኮሎኔል ከበደ ወርቁ በ፫ኛ ክፍል ጦር የ፲ኛ ብርጌድ አዛዥ፣
፲፪ኛ) ኮሎኔል ጥግነህ አድማሱ በመከላከያ ሚኒስቴር የፐርሶኔልና የሰው ኃይል ዋና ዳይሬክተር ሆነው ተሾሙ።

ከላይ የተዘረዘሩት ተሿዋሚዎች ከጥቂቶቹ በቀር አብዛኞቹ ከአዲስ አበባ አልተንቀሳቀሱም ነበር። ስለዚህ ጃንሆይ ምዕራብ አፍሪካ በጉብኝት ላይ እንዳሉ ተሿዋሚዎቹ ወደየሥራ ምድባቸው እንዲሔዱ ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ ገበየሁ ለራስ አበበ ትዕዛዝ እንዲሰጥ የሚጠይቅ ቴሌግራም በህዳር ወር መጨረሻ ለጃንሆይ አስተላልፎ ቶሎ መልስ ስላላገኘ፣ ራሱ እርምጃ ከወሰደ በኋላ ለጃንሆይ እንዲያውቁት ቴሌግራም አስተላልፎላቸዋል።

*(አሁን የካቲት ፲፪ ሆስፒታል በር ስደርስ ወደቀኝ ተጠምዘዝና ወደ ናዝሬት ትምህርት ቤት ሂድ አለኝ። እሺ ብዬ ስሔድ ሰዓቱ አራትና አምስት ሰዓት ገደማ ነበር። እኛ እዛ ስንደርስ የጠቅላይ ሚኒስትሩን ቢሮ የሚጠብቁ ወታደሮች የዘብ ልውውጥ ያደርጉ ነበር። ሌ/ኮሎኔል ያን እያዩ ቆየና «በቅርቡ አንዳንድ ነገር ይደረጋል። አማንን (ጄኔራል) ማለቱ እንደሆነ ገብቶኛል ወደ ሐረር አዛውረዋለሁ። ተሰማ (የሻለቃ ተሰማ ዋቅጅራን ማለቱ ነው) እንዲያግዘው ወደዚያው አዛውረዋለሁ።» አለኝ። ግን ለምን እንደሆነ አልገለጸልኝም። ከዚያ መንገዳችንን በናዝሬት ትምህርት ቤት ፊት ለፊት አድርገን ቁልቁል ወርደን ራስ መኮን ድልድይን ይዘን በጊዮርጊስ ወደ ፀጥታ መሥሪያ ቤት ሔድን። ወደፊት እንደምናየው ይህ ሐሳቡ ከጄኔራል ጃገማ ኬሎ ሪፖርት ጋር ይሔዳል።*

## ምዕራፍ ፬

# የመፈንቅለ መንግሥቱ ጥንስስ ጠቋሚ ሁኔታዎች

ሥርዓቱ የፈጠራቸው ችግሮች በየቦታው ተቃውሞ ባረገዙበትና ወደ ዐመፅ ለመሸጋገር እየተጧያጧያሉ በነበሩበት ጊዜ፣ ንጉሡ ከማዕከላዊ ሳይሆን ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች የደርሳቸውን ጥቆማ "መረጃ አይናቅም፤ አይደነቅም" በሚለው መሠረታዊ የመረጃ ንድፈ ሐሳብ መርህ መሠረት እርምጃ ሳይወስዱበት ቀሩ። እንደዚህ ሆኖ እያለ በሥልጣናቸው ላይ ለብዙ ዓመታት መቀመጥ የቻሉት በወግ የተደራጀና ጠንካራ ተቃዋሚ ስላላጋጠማቸው ነበር ማለት ነው። በ፲፱፻፶፫ ዓ.ም. ስለተደረገው የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራም ከተለያዩ አቅጣጫዎች መረጃ መስማታቸውን የሚያረጋግጡ ፍንጮች አሉ። የሰሙትን ሁሉ "የት ይደርሳል" በሚል ንቀት፣ የተሟላ ጥንቃቄ ሳያደርጉ ነበር ወደ ምዕራብ አፍሪካና ብራዚል ጉብኝት ጉዞ የተዘጋጁት። ጄኔራል መንግሥቱ መፈንቅለ መንግሥቱን የጠነሰሰው በራሱ ስሜት ሳይሆን፤ በወንድሙ በገርማሜ ግፊት ነበር፤ ብለው የሚያምኑትና በታኅሣሥ ፲፱፻፶፫ ዓ.ም. በተደረገው የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ በ፲፪ ጥይት ታፋቸው ላይ ቆስለው ከሞት የተረፉት[1] ብርጋዴር ጄኔራል መኮንን ደነቀ ለንጉሡ ደርሷቸው ነበር የሚሉትን ጥቆማ ሲዘረዝሩ እንዲህ ይላሉ።

> አንደኛ ጃንሆይ ወደ ብራዚል ለመሔድ በተቃረቡበት ወቅት የክብር ዘበኛ መኮንኖች አንዳንድ ጉምጉምታ እያሰሙ ነው የሚል ወሬ ይነፍስ ነበር። ከዚህ ጋር በተያያዘም ጃንሆይ ከመሔዳቸው በፊትም ጄኔራል መንግሥቱ ወደ ግርማዊነታቸው ቀርቦ «የሐረር ሚሊቴሪ አካዳሚ ምሩቃን መኮንኖች ከሌላው ጦር ትምህርት ቤት ምሩቆች የተለየ ደሞዝ ተቆርጦላቸዋል። እንዴት እኛ ሳሠለጠናቸው ከኛ በላይ ደሞዝ ይቆረጥላቸዋል? በማለት ቅሬታ እያሰሙ ነው። ይህ ነገር ቢስተካከልላቸው ይሻላል» ብሎ ሐሳብ አቅርቦ ነበር። ጃንሆይ ግን «የአቤቱታው መነሻ አንተ ነህ! አውቀነዋል። እንመለስ!» ብለው መለሱ። ስለዚህ ጃንሆይ ከሔዱበት ሲመለሱ ከቦታው እንደሚያነሱት ስለገመተ ነው መንግሥቱ እንዲያ ያደረገው።
>
> ሁለተኛ የመፈንቅለ መንግሥቱ ሤራ ጥንስስ መረጃ ለንጉሠ ነገሥቱ በተለያዩ ባለሥልጣኖች በኩል ደርሷቸው ነበር። በሜጀር ጄኔራል ሙሉጌታ ቡሊ በኩል የሻለቃ ዮሐንስ ምስክር፣ በምክትል ጸሐፊ ትዕዛዝ ገብረ ወልድ እንግዳ ወርቅ በኩል የሻለቃ ማሩ ጋረድነ በሻምበል ደረጀ ኃይለ ማርያም በኩልና እኔ ራሴ ስለሤራው ለንጉሡ መድረስ በግልጽ ፍንጬን በሰማሁበት

---

[1] የግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዋና የእልፍኝ አስከልካይ፣ በኋላ የግቢ ምክትል ሚኒስትር ቀጥሎም በአገር ግዛት ሚኒስቴር ምኒስትር ደኤታ የነበሩት በኋላ ለኔ ለዚህ ታሪክ ጸሐፊ የሰጡት ምስክርነት ቃል ነው። ጄኔራል መኮንን ይህን የምስክርነት ቃል የሰጡኝ ከሸራተን ሆቴል በላይ ካለው ቤታቸው ሒጄ አነጋግሬአቸው ነው። ጄኔራል መኮንን እስኪያርፉ ድረስ በየወሩ የሚካኤል ዕለት የካ ሚካኤል አብረን እናስቀድስ ነበር።

# ምዕራፍ ፬

# የመፈንቅለ መንግሥቱ ጥንስስ ጠቋሚ ሁኔታዎች

ሥርዓቱ የፈጠራቸው ችግሮች በየቦታው ተቃውሞ ባረገዙበትና ወደ ዐመፅ ለመሸጋገር እየተጧያጧያሱ በነበሩበት ጊዜ፤ ንጉሡ ከማዕከላዊ ሳይሆን ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች የደርሳቸውን ጥቆማ "መረጃ አይናቅም፤ አይደነቅም" በሚለው መሠረታዊ የመረጃ ንድፈ ሐሳብ መርህ መሠረት እርምጃ ሳይወስዱበት ቀሩ። እንደዚህ ሆኖ እያለ በሥልጣናቸው ላይ ለብዙ ዓመታት መቀመጥ የቻሉት በወግ የተደራጀና ጠንካራ ተቃዋሚ ስላላጋጠማቸው ነበር ማለት ነው። በ፲፱፻፶፫ ዓ.ም. ስለተደረገው የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራም ከተለያዩ አቅጣጫዎች መረጃ መስማታቸውን የሚያረጋግጡ ፍንጮች አሉ። የሰሙትን ሁሉ "የት ይደርሳል" በሚል ንቀት፣ የተሟላ ጥንቃቄ ሳያደርጉ ነበር ወደ ምዕራብ አፍሪካና ብራዚል ጉብኝት ጉዞ የተዘጋጁት። ጄኔራል መንግሥቱ መፈንቅለ መንግሥቱን የጠነሰሰው በራሱ ስሜት ሳይሆን፤ በወንድሙ በገርማሜ ግፊት ነበር፤ ብለው የሚያምኑትና በታኅሣሥ ፲፱፻፶፫ ዓ.ም. በተደረገው የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ በ፲፪ ጥይት ታፋቸው ላይ ቆስለው ከሞት የተረፉት[1] ብርጋዴር ጄኔራል መኮንን ደነቀ ለንጉሡ ደርሷቸው ነበር የሚሉትን ጥቆማ ሲዘረዝሩ እንዲህ ይላሉ።

> አንደኛ ጃንሆይ ወደ ብራዚል ለመሔድ በተቃረቡበት ወቅት የክብር ዘበኛ መኮንኖች አንዳንድ ጉምጉምታ እያሰሙ ነው የሚል ወሬ ይነፍስ ነበር። ከዚህ ጋር በተያያዘም ጃንሆይ ከመሔዳቸው በፊትም ጄኔራል መንግሥቱ ወደ ግርማዊነታቸው ቀርቦ «የሐረር ሚሊቴሪ አካዳሚ ምሩቃን መኮንኖች ከሌላው ጦር ትምህርት ቤት ምሩቆች የተለየ ደሞዝ ተቆርጦላቸዋል። እንዴት እኛ ላሠለጠናቸው ከኛ በላይ ደሞዝ ይቆረጥላቸዋል? በማለት ቅሬታ እያሰሙ ነው። ይህ ነገር ቢስተካከልላቸው ይሻላል» ብሎ ሐሳብ አቅርቦ ነበር። ጃንሆይ ግን «የአቤቱታው መነሻ አንተ ነህ! አውቀነዋል። እንመለስ!» ብለው መለሱ። ስለዚህ ጃንሆይ ከሔዱበት ሲመለሱ ከቦታው እንደሚያነሱት ስለገመተ ነው መንግሥቱ እንዲያ ያደረገው።
>
> ሁለተኛ የመፈንቅለ መንግሥቱ ሤራ ጥንስስ መረጃ ለንጉሠ ነገሥቱ በተለያዩ ባለሥልጣኖች በኩል ደርሷቸው ነበር። በሜጀር ጄኔራል ሙሉጌታ ቡሊ በኩል የሻለቃ ዮሐንስ ምስክር፣ በምክትል ጸሐፌ ትዕዛዝ ገብረ ወልድ እንግዳ ወርቅ በኩል የሻለቃ ማሩ ጋረድን በሻምበል ደረጀ ኃይለ ማርያም በኩልና እኔ ራሴ ስለሤራው ለንጉሡ መድረስ በግልጽ ፍንጩን በሰማሁበት

---

[1] የግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዋና የእልፍኝ አስከልካይ፣ በኋላ የግቢ ምክትል ሚኒስትር ቀጥሎም በአገር ግዛት ሚኒስቴር ምኒስትር ደኤታ የነበሩት በኋላ ለኔ ለዚህ ታሪክ ጸሐፊ የሰጡት ምስክርነት ቃል ነው። ጄኔራል መኮንን ይህን የምስክርነት ቃል የሰጡኝ ከሸራተን ሆቴል በላይ ካለው ቤታቸው ሒጄ አነጋግሬአቸው ነው። ጄኔራል መኮንን እስኪያርፉ ድረስ በየወሩ የሚካኤል ዕለት የካ ሚካኤል አብረን እናስቀድስ ነበር።

በብርጋዴር ጄኔራል ወልደ ዮሐንስ ተክሉ ባለቤት በወ/ሮ ኪሮስ ወልደ ሚካኤል በኩል ነው። ነገሩ እንዲህ ነው ወ/ሮ ኪሮስ እቢሮዬ መጥታ ባስቸኳይ ከጃንሆይ ዘንድ እንዳቀርባት ጠየቀች። እኔም ‹‹ታዲያ በእልፍኝ አስከልካይ በኩል ጠይቀሽ ቅረቢ እንጂ፣ እኔ ከዚያ ለቅቄ የለም ወይ?›› ብላት አጥብቃ በመጠየቅ ስላስቸገረችኝ ለጃንሆይ ነገርኳቸውና ‹‹አቅርባት›› ብለው ቀረበች። ተነጋግራም ስትመለስ ከቢሮዬ መጥታ ‹‹ሰሙ! ለጃንሆይ ትልቅ ነገር ነው የነገርኳቸው፣ በጣም የሚያሳዝን ነው!" አለች። ነገሩ አልገባ ብሎኝ ስለምንነቱ ብጠይቃት ‹‹ጄኔራል መንግሥቱ፣ ጄኔራል ጽጌ ዲቡ፣ ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህና አቶ ገርማሜ ሁለት ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ መፈንቅለ መንግሥት ሊያደርጉ መሆኑን ነገርኳቸው›› አለች። እኔም ‹‹ከምን አገኘሽው? አልኳት። እሷም መለሰችና ‹‹ምን ቸገረዎ!›› አለችኝ።

ከዚህ ውጪ ሜጀር ጄኔራል ሙሉጌታ ቡሊም በክብር ዘበኛ መኮንኖች የሚካሔደውን ሤራ ደርሶበት፤ "ጃንሆይ ከመሔድዎ በፊት መንግሥቱንና ወርቅነህን ከቦታቸው ሳያነሡዋቸው ቢሔዱ ሲመለሱ ዙፋንዎን አያገኙትም" ብሎ ቢነግራቸው፤ «አንተ ነበርክ የምትጠረጠረው» አሉት። እሱም «የኔ ይቆይ፤ ግድ የለም፣ ይህን ይልቅ ያስቡበት» አላቸው። ጄኔራል መንግሥቱና ጄኔራል ጽጌ፣ ባንደኛቸው መኪና እየሔዱ ምስጢራቸው እንዳይወጣ ሾፌር በሌለበት ነበር የሚጨዋወቱት።

እንዲህ ዓይነቶቹን ጥቆማዎች እንደማግኘታቸው ግን ጃንሆይ ተገቢውን ጥንቃቄም ሆነ እርምጃ አልወሰዱም። ከመፈንቅለ መንግሥቱ መክሸፍ በኋላ፣ የሻለቃ ማሩ ጋረድ ከጠቅላላ የክብር ዘበኛ ሠራዊት ጋር በክፍለ ጦር ታሥሮ ስለነበር፤ ወ/ሮ አስገደች ከበደ (የራስ ተሰማ የልጅ ልጅ) ወደ ጃንሆይ ቀርበው «ባሌን ይፍቱልኝ» ብለው ጠየቁ። ጃንሆይም ሻለቃ ማሩን ከእሥር ቤት አስመጥተው «ለመሆኑ የኛ ውለታ ይሄ ነው? እንዲህ ነው የሚመለስልን?» ብለው ሲጠይቁት፤ እርሱም «በመኮንኖቹ ውስጥ ይካሔድ የነበረውን ሤራ በሻምበል ደረጀ ኃይለ ማርያም በኩል አቅርቤልዎ እርምጃ ስላልተወሰደ ነው እንጂ፤ እኔማ ግዴታዬን ተወጥቻለሁ።» አለ። ጃንሆይም «አዎ! አዎ!» አሉና ወዲያው «ይፈታ» ብለው አዘው ተፈታ።[2]

በዚህ አጋጣሚ ስለሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ ያነሱት በተለይ ንጉሡ ምን ያህል ለጉዳዩ ትኩረት እንዳልሰጡት ማሳያ ነው።

ጃንሆይ በ፲፱፻፶፪ ዓ.ም. ከሩሲያ ጉብኝት እንደተመለሱ፤ ቤተ መንግሥት ግቢ ውስጥ ካለው ቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን ለማስቀደስ ሲሔዱ፤ እኔም አጀበዋቸው ከሔዱት ሹማምንት አንዱ ነበርኩ። በኋላ ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ አይቶኝ መጣና ከኋላዬ ጠቆም! ጠቆም! አድርጎኝ ዞር ብዬ ሳይ ‹ይምጡ እፈልገዎታለሁ› ብሎ ወደ አንድ ዛፍ ሥር ወሰደኝና ‹ጥብቅ ምስጢር እነግርዎታለሁ። ይህንንም ለእርስዎ የምነግረው ለማንም እንደማይነግሩ ስለማምን የሞትኩ እንደሆነ ወርቅነህ እንዲህ ብሎ ነበር ብለው እንዲመሰክሩ ነው› ብሎ የሚከተለውን ነገረኝ።

---

2 ብርጋዴር ጄኔራል መኮንን ደነቀ

> ጃንሆይ ሩሲያን ለመጎብኘት ሲሔዱ አብሬ ሔጄ ነበር። ከዚያም በባቡር ከሌኒንግራድ ወደ ሞስኮ ከተማ ለመሄድ ብዙ ሰዓት የፈጀ ጉዞ በማድረግ ላይ እንዳለን ጃንሆይን ብቻቸውን በቂ ጊዜ አግኝቼ ያነጋገርኩበት መልካም አጋጣሚ ስለነበር፤ በአገራችን በአስተዳደር፣ በፍርድ፣ በምጣኔ ሀብትና በመሬት ሥሪቱ ያለውን ብልሽትና ባለሥልጣኖች በጠቅላላው በሕዝብ ላይ የሚፈፅሙትን በደል በሠፊው ዘርዝሬ ገለጽኩላቸው። ከዚያም ይህ ሁኔታ ቶሎ መግቻ ካልተደረገበት የጉዳቱ ብዛት ይህ ነው የማይባል እልቂት የሚያመጣ፣ የብዙ ሰው ሕይወት የሚያጠፋ፣ ብዙ ደም የሚያፋስስ፣ ንብረት የሚያወድም፣ የግርማዊነትዎን ታሪክ የሚያጉድፍና የዘውድ አስተዳደር ቀጣይነትን ገትቶ ለውጥ የሚያመጣ ብርቱ እንቅስቃሴ ስለሚያስነሣ፤ ግርማዊነትዎ ይህን ሥርዓት አንስቶ ሥልጣኑን ለአልጋ ወራሹ ሰጥቶ ግርማዊነትዎ ከኋላ ሆኖ በመምከርና በመቆጣጠር፣ እንደ እንግሊዝና ጃፓን ያለ የመንግሥት አስተዳደር ሥርዓት በኢትዮጵያ ቢዘረጋ፤ ዘውዳዊውን ሥርዓት የሚያስቀጥልና ኢትዮጵያን ከጥፋት በማዳን ስምዎ፣ ክብርዎና ታሪክዎ የተወደደና እንደተከበረ ለዘላለም እንዲኖር የሚረዳ ነው። እንዲህ ቢያደርጉ ኢትዮጵያን ከመከራና ከብጥብጥ ያድኑዋታል› ብዬ ንግግሬን ሳቆም፤ ዝም ብለው ቆይተው "አይ! አይ! ወርቅነህ! እኔ የበሰልክ ይመስለኝ ነበር፣ ለካስ ልጅ ነህ! ከልጅ ጋር ነው የምንሠራው! እግዚአብሔር የሰጠንን ሥልጣን እስካለን እንሠራበታለን። ከዚያ በኋላ እሱ እንደፈለገ ያድርጋት። ለመሆኑ ማን ሥልጣኑን ለሌላ አሳልፎ የሰጠ ዓይተሃል? አሉኝ። እኒህ ሰውዬ እርቀው አያዩም። ለኢትዮጵያ ጨርሶ የማይበጁና በጎ የማይመኙ ሰው ናቸው።
>
> ብሎ ስላጫወተኝ ጉዳይ በዚህ አጋጣሚ ምስክርነቴን መስጠት እፈልጋለሁ።[3]

በማለት በ፲፱፹፮ ዓ.ም. አደራቸውን ለማውረድ አጋጣሚውን እንዳገኙ እየተሰማቸውና ደስ እያላቸው ነግረውኛል።

ወደቀደመ ነገሬ ስመለስ ከዚህ በፊት እንደገለጽኩት፣ ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ ይህን ታሪክ ደብረዘይት ከአልጋ ወራሽ ጋር ከተደረገው ግንኙነት በኋላ ወደ አዲስ አበባ ስንመለስ፤ ዘርዘር በማድረግ ንጉሠ ነገሥቱ "ራሳቸውን ወዳድ፣ ጨካኝ፣ ለአገርና ለወገን ችግር ደንታ የሌላቸው ናቸው። ሌላው አልቆ እሳቸው ብቻቸውን ቢቀሩ ግድ የላቸውም። የሚመጣው መከራ ደግሞ እሳቸውንም አይለቃቸውም። ይህችን አገር ሊያጠፏት ነው።" ብሎ እያዘነና እየተናደደ ከነገረኝ ጋር በእጅጉ የሚመሳሰል እንደሆነ እናያለን። በሌላ በኩል ደግሞ፣ ጃንሆይ ብዙ ጊዜ ስለሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ ሲናገሩ "መንፈሴ ወርቅነህን አሳድገው! አሳድገው! ይለኛል። ለጥፋቴ ይሁን

---


3 ዝኒ ከማሁ

ለልማቴ አላውቅም" ይሉም ነበር::[4] እንደ ጄኔራል መኮንን፣ ንጉሡ ስለ መፈንቅለ መንግሥቱ ጥንስስ መኖር ከተለያዩ አቅጣጫዎች ብዙ መረጃ ደርሷቸው ሳለ ምን እንደያዛቸው አልታወቅም:: ምናልባት በክብር ዘበኛ ላይ ጥርጣሬ ስላልነበራቸው ይሆናል ብሎ ማሰብ ይቻላል::

በዚህ ሁኔታ ነው እንግዲህ፣ ንጉሡ ለጉብኝት ለመሔድ የተነሡት:: ይህን አስመልክቶ በጊዜው የነበሩት የአገሪቱ ጋዜጦች ሁሉ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ከሦስት የምዕራብ አፍሪካ አገሮችና ከብራዚል መሪዎች በቀረበላቸው የክብር ጥሪ መሠረት አገሮቹን ለመጎብኘት፣ ረቡዕ ኅዳር ፳፩ ቀን ፲፱፻፶፫ ዓ.ም. ከአዲስ አበባ በመነሣት ጉዞአቸውን ስለመጀመራቸው አትተዋል:: የአተታው ይዘት ጭብጥ ዘርዘር ያለ መረጃን ቢያካትትም ፍሬ ነገሩ እንደሚከተለው ነው:: የግርማዊ ንጉሠ ነገሥት የምዕራብ አፍሪካና የብራዚል ጉዞ፣ ከ፲፱፻፲፮ ዓ.ም. የአውሮፓ የመጀመሪያ ጉብኝት ጀምሮ ስድስተኛው እንደነበረ፤ ግርማዊ ጃንሆይ የውጭ ጉብኝት የጀመሩት ገና ልዑል አልጋ ወራሽ ራስ ተፈሪ መኮንን ይባሉ በነበረበት ጊዜ በ፲፱፻፲፮ ዓ.ም. ለመጀመሪያ ጊዜ ከአገራቸው ወጥተው የአውሮፓን ምድር በረገጡበትና ኢትዮጵያ የዓለም ማኅበር አባል እንድትሆን ለማስመዝገብና፣ እግረ መንገዳቸውንም የአውሮፓን ሥልጣኔ ለማየት ከሔዱበት ጊዜ እንደሚጀምር ያወሳል:: ከዚያም በ፲፱፻፳፰ ዓ.ም. ኢትዮጵያ በኢጣሊያ በግፍ ስትወረር፤ የዓለም ማኅበር በቀረፀው የመተዳደሪያ ደንብ መሠረት በግፍ የተወረረውን አገር ሸምግሎ ወይም ዳኝቶ ነፃነቱን ያስመልሳል ስለሚል አቤቱታቸውን ለማኅበሩ ለማሰማት ለሁለተኛ ጊዜ ከአገራቸው ወጥተው ወደ አውሮፓ መጓዛቸውን፤ ነፃነት ተመልሶ አገር ከተረጋጋ በኋላ ከ፲፱፻፵፮ ዓ.ም. ጀምሮ እስከ ፲፱፻፶፫ ዓ.ም. ድረስ አሜሪካ፣ አውሮፓ፣ ሕንድ፣ ጃፓን፣ ሩቅ ምሥራቅ፣ ግብፅ፣ ሩሲያ፣ ችኮዝሎቫኪያ፣ ዩጎዝላቪያ፣ ምዕራብ ጀርመንና ቤልጅግን ለመጎብኘት ለሦስት ጊዜ ያህል ከአገራቸው እየወጡ በደህና መመለሳቸውን፤ ይህ ስድስተኛው ጉዞአቸውም እንደ ሌሎቹ ጉብኝቶች ሁሉ የራሱ ዐላማ እንደነበረው የሚገልጽ ነው::


ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ምዕራብ አፍሪካንና ብራዚልን ለመጐብኘት ከአዲስ አበባ ከወጡ በኋላ፣ ከኅዳር ፳፪ ጀምሮ ከማረፊያ ቤታቸው በነበረው ማስታወሻ ወረቀት በራሳቸው የእጅ ጽሑፍ ስለጉዟቸው፣ በሰላም መድረሳቸውና በአገር ቤት ስለነበሩ አንዳንድ ሁኔታዎች የሚከተሉትን ቴሌግራሞች በፀጥታ መሥሪያ ቤት በኩል አከታትለው ልከው መልሱንም አግኝተዋል::

4 ዝኒ ከማሁ





*ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በራሳቸው የእጅ ጽሑፍ ለቴሌግራም ክፍሉ የላኩት የቴሌግራም ረቂቅ*[5]


[5] *በዚህ መጽሐፍ የተካተቱትን ቴሌግራሞችና የቴሌግራም ረቂቆችን ያገኘሁት፣ በሕዝብ ፀጥታ ጥበቃ መሥሪያ ቤት የአስተዳደር ክፍል ኃላፊ ከነበረው ከአቶ ወርቁ ተስፋ ነው። አቶ ወርቁ ጃንሆይ ምዕራብ አፍሪካን እና ብራዚልን ለመጎብኘት ሲሔዱ፣ ከአዲስ አበባ ጋር በኮድ (በምሥጢር ቃል) በሬዲዮ ይደረግ ለነበረው የመልእክት ግንኙነት ኃላፊ ሆኖ አብሮ የሔደ ሰው ነበር። በ፲፱፻፹፬ ዓ.ም. አጋማሽ ገደማ አዲስ ከገባበት መሥሪያ ቤት ሔጄ አግኝቸው "ስለ ፲፱፻፶፫ ዓ.ም. ስለ መፈንቅለ መንግሥቱ ሙከራ" መጽሐፍ ልጽፍ ስለሆነ፣ ጃንሆይ ለጄኔራል መንግሥቱ ስለ ገርማሜ ያስተላለፉት ቴሌግራም በእጅህ እንዳለ ብትሰጠኝ ወይም የት እንዳለ ብትጠቁመኝ" ስል በጠየቅሁት መሠረት፣ ለጄኔራል መንግሥቱ የተላከውንና የጄኔራሉን የመልስ ቴሌግራም አምጥቶ ስለሰጠኝ እጅግ በጣም አመሰግነዋለሁ። ከሦስት ወራት በኋላ ደግሞ በአጠቃላይ በእጁ የነበሩትን በኮድ የገቡና የተፈቱ በቁጥር ከ፳፯ በላይ የሆኑ የቴሌግራም ሰነዶች "እኔ ምንም ላደርጋቸው ስለማልችል፣ ወስደህ እንደፈለግህ አድርጋቸው" ብሎ የሰጠኝ በመሆኑ፣ ትብብሩ ለዚህ መጽሐፍ ዋጋ ካስገኙት ሰነዶች ውስጥ ከፍ ያለውን ድርሻ የያዙት የነዚህ ቴሌግራሞች በመጽሐፉ ውስጥ መካተት እውን እንዲሆን ረድቶኛል። በዚህም፣ አቶ ወርቁ ተስፋ ያደረገው ታላቅ አስተዋፅኦ የታሪክ ክፍተት ፈጥሮ ባከኖ ሊቀር የነበረውን ክስተት ለዚህ እንዳበቃ አድርጎኛል። አቶ ወርቁ ተስፋ አሁን ደብረ ዘይት በጡረታ እየተዳደረ ይገኛል።*





*የእቴጌ መነን የመልስ ቴሌግራም*



*ጃንሆይ ለሌ/ኮሎኔልወርቅነህ የላኩት ቴሌግራም በራሳቸው የእጅ ጽሑፍና ፊርማ*



ከላይ ለሰፈረው የጃንሆይ ቴሌግራም
ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ በራሱ የእጅ ጽሑፍ ያዘጋጀው የቴሌግራም መልስ ረቂቅ





ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ በራሱ የእጅ ጽሑፍ ያዘጋጀው ቀጣይ የቴሌግራም መልስ

## ምዕራፍ ፭


# ለመፈንቅለ መንግሥቱና በመፈንቅለ መንግሥቱ ሙከራ ላይ የተደረጉ ዝግጅቶች

### የክብር ዘበኛ ዝግጅት ማክሰኞ ታኅሣሥ ፬ ቀን


ቀደም ብሎ እንደተመለከተው የመፈንቅለ መንግሥቱ መሪዎች የተመደቡበት የሥራ ቦታና ተግባር በአገሪቱ ውስጥ ያሉትን የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካ፣ የማኅበራዊና የአስተዳደር ችግሮች ጠለቅ አድርጎ ለማወቅ ረድቷቸዋል። በአገሪቱ የሚታዩትን የአስተዳደር ጉድለቶች ለመፍታትም ንጉሠ ነገሥቱ ከመሪነት ሳይነሱ አስፈላጊውን የማሻሻያ እርምጃ በመውሰድ በኢትዮጵያ ዕድገትና መሻሻል ማምጣት ይቻላል የሚል እምነት ነበራቸው። ይህን እምነታቸውን መሠረት አድርገው፤ በቀና መንፈስና በንጹሕ ልቦና ለንጉሠ ነገሥቱ በተለያዩ ጊዜያት ማሻሻያ መንገድ አመላክተው ነበር። የማሻሻያ ሐሳቦቹ ግን በንጉሡ ተቀባይነት ሊያገኙ አልቻሉም። ስለዚህ፣ በሕዝቡ ላይ የሚታየው የፍርድ ጉድለት፣ የአስተዳደር በደልና የኢኮኖሚው ድቀት እያስጨነቃቸውና ሰላም እየነሳቸው ስለሄደ፤ አማራጭ መፈለግ ግድ እየሆነባቸው መጣ። አማራጩም ምንም ይጠይቅ ምን መተግበር እንዳለበት አምነው፤ የውሳኔያቸውን ማስፈፀሚያ ዕቅድ ገና በመዘርጋት ላይ እንዳሉ፤ በድንገት ኅዳር ፳፱ ቀን ፲፱፻፶፫ ዓ.ም. ንጉሠ ነገሥቱ ምዕራብ አፍሪካ ሆነው በራሳቸው እጅ ጽሑፍ የጻፉትና በሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ በኩል ለጄኔራል መንግሥቱ የላኩት ቴሌግራም[1] ያለ ጊዜው እሳት ጫረ።



ጃንሆይ ለብ/ጄኔራል መንግሥቱ ስለግርማሜ ንዋይ ትእዛዝ
የላኩት የቴሌግራም መልዕክት ረቂቅ በራሳቸው የእጅ ጽሑፍ



ጃንሆይ ለብ/ጄኔራል መንግሥቱ ስለኮንጐ ጉዳይ
የላኩት የቴሌግራም መልዕክት ረቂቅ በራሳቸው የእጅ ጽሑፍ





ብጀኔራል መንግሥቱ ስለገርማሜና ስለኮንጎው ጉዳይ በአንድ ላይ
ለጃንሆይ ያስተላለፉት የመልስ ቴሌግራም[2]


---

[2] የቴሌግራሙ ጽሑፍ ጉላ ብሎ እንዲታይ ሲባል የቴሌግራሙ ቅጂ ቁመቱ እንዲረዝም ተደርጓል።


መንግሥቱም ስለገርማሜ የጉዞ አነሣስና በንጉሡ ሁለተኛ ቴሌግራም ስለወቅቱ የኮንጐ ሁኔታም ማብራሪያ ተጠይቀው ስለነበር፤ በኮንጎ ከሚገኘው ዘማች ጦር ያገኙትን መረጃ ለጃንሆይ ገልጸው መለሱ። በወቅቱ የሉሙምባ ደጋፊዎች ሚስተር ሉሙምባ ዛሬ ማታ ካልተፈቱ በዚያ የሚገኙትን አውሮፓውያን አብዛኞቹን የሚያሥሩና ሀብታቸውን የሚወርሱ፣ እንዲሁም ጥቂቶቹን የሚገሉ መሆናቸውን ለሚስተር ካዛ ቡቡና ለኮሎኔል ሞቡቱ በላኩት መልእክት አስታውቀው ነበር። ከዚህ ቀጥሎ የተቀመጠው ቴሌግራም ንጉሡ ስለሁኔታው ማብራሪያ የጠየቁበት ነው። የጉዳዩን አሳሳቢነትን ለማመልከት የንጉሡ የልዩ ጽሕፈት ቤት ሹም የአቶ ከተማ ይፍሩ ቴሌግራም ሲታከልበት የጄኔራል መንግሥቱን መልእክት ያጠናክራል።



የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ለብ/ጄኔራል መንግሥቱ የላኩት በቴሌግራም ክፍሉ በቀጥር ቃል (በኮድ) የተላለፈ ቴሌግራም




የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ልዩ ጽሕፈት ቤት ሹም የአቶ ከተማ ይፍሩ ቴሌግራም



*የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በራሳቸው የእጅ ጽሑፍ ለቴሌግራም ክፍሉ የላኩት አጭር መልዕክት*[4]

[4] *ይህ መልእክት ቀድሞ በታሰበው መሠረት በኢትዮጵያ የዩኒቨርስቲ መንደር ለመሥራት የተመረጠው ቦታ አዲስ አበባ ካልሆነ ባሕርዳር እንዲሆን የጃንሆይ ምርጫ መሆኑን ለአጥኚዎቹ እንዲነገር ፍላጎታቸው እንደነበር የሚገልጽ ነው። ይህም፣ ጃንሆይ መፈንቅለ መንግሥት ይካሔዳል የሚል ግምት ያልነበራቸው ብቻ ሳይሆን፤ ምን ያህል ስለዝርዝር ጉዳዮች ሳይቀር የሚያስቡ እንደሆኑ የሚያሳይ ነው።*




*የአቶ ከተማ ይፍሩ ቀጣይ ቴሌግራም*


እነዚህ ቴሌግራሞች የሚያስገነዝቡን

፩ኛ/ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የገርማሜ አዲስ አበባ መቆየት አሳስቧቸው እንደ ነበር፣

፪ኛ/ ጄኔራል መንግሥቱ ደግሞ በስበብ አስባብ እያመካኙ ገርማሜ እንዳይሔድ ፍላጐት እንደነበራቸውና መፈንቅለ መንግሥቱም የተካሄደው ገርማሜ ወደ ምድብ ሥራው ይሔዳል በተባለበት ቀን መሆኑን ነው::

፫ኛ/ በእስታንቪል ሊወሰድ ስለታሰበው የሉሙምባ ደጋፊዎች ማስጠንቀቂያ በጄኔራል መንግሥቱ ቴሌግራም መነሣቱ ደግሞ፤ በዚያን ጊዜ የተባበሩት መንግሥታት

የሰላም አስከባሪ ኃይል ሆኖ ኮንጐ የተላከው ኃይል ከጦር ሠራዊትና ከክብር ዘበኛ ተውጣጥቶ ስለነበር፤ የዚያን ሠራዊት የዕለት ከዕለት እንቅስቃሴ ለንጉሡ ማሳወቅ ተገቢ ስለነበረ፤ ይህንኑ ከመግለጻቸው በላይ ሉሙምባ ለደጋፊው ጦር የሚሆን ደመወዝ ከሞስኮ በመጠየቁ፤ ወደ ግራ የማዘንበል አዝማሚያ ያለው መሆኑን ለንጉሡ በመጠቆም፤ በገርማሜ ላይ የነበረውን ትኩረት ለማርገብ የቀረበ ሐሳብ ይመስላል።




ፓትሪክ ሉሙምባ

፬ኛ/ በአገር ውስጥ ሰላም መኖሩንና የነሱን ታማኝነት ማረጋገጣቸው ደግሞ፤ እስከ ቀኑ ድረስ ለማዘናጋት ሊሆን ይችላል።




*ፓትሪክ ሉሙምባ*

፬ኛ/ በአገር ውስጥ ሰላም መኖሩንና የነሱን ታማኝነት ማረጋገጣቸው ደግሞ፣ እስከ ቀኑ ድረስ ለማዘናጋት ሊሆን ይችላል።





የአገር ግዛት ሚኒስትሩ ራስ አንዳርጋቸው ያስተላለፉት መልእክትና ያገኙት መልስ[5]





የፀጥታው መሥሪያ ቤት ምክትል ሚኒስትር አፈንጉሥ እሸቴ ገዳ ያስተላለፉት መልእክት

[5] ሁለት የተለያዩ ቴሌግራሞች አንድ ላይ ተጋጥመው ነው።




ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ያስተላለፈው መልእክት



*አቶ አምደ ሚካኤል ደሳለኝ (የፕሮፓጋንዳ) በኋላ የማስታወቂያ ም/ሚኒስትር ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ያስተላለፉት መልእክት*

አቶ መኮንን የመፈንቅለ መንግሥት ሤራ እየተካሔደ መሆኑን ባሏቸው መረጃዎች አስቀድመው ደርሰውበት ስለነበር፤ ንጉሡ ጉብኝቱን አቋርጠው ከምዕራብ አፍሪካ ወደ አገራቸው እንዲመለሱ ለማድረግ ሞክረው ነበር። ሙከራውም ቶሎ ይመለሱ የሚል ጥሪ በስልክ ወይም በቴሌግራም ለንጉሡ ቢያስተላልፉ፤ በፀጥታ መሥሪያ ቤትና በጄኔራል ሙሉጌታ ቡሊ የሬዲዮ መገናኛ መቆጣጠሪያ እንደሚጠለፍ ስለሚያውቁ በሌላ ዘዴ መልእክቱን ማስተላለፍ ነበር። እርሱም፣ መልእክቱን በቀጥታ በአውሮፕላን መላክ ነበር። የአየር ኃይል ምክትል አዛዥ ኮሎኔል አሰፋ አየነን (ኋላ ሌፍተናንት ጄኔራል) ባስቸኳይ ለጃንሆይ መድረስ ያለበትን ዕቃ የሚወስድ አውሮፕላን

እንዲያዙላቸው ጠየቁ:: ኮሎኔል አሰፋ አየነም "በአስቸኳይ ለጃንሆይ መድረስ ያለበት ዕቃ ካለ ግርማዊነታቸው ይዘዙኝ እንጂ፤ ይህን ያህል ሩቅ አገር በርስዎ ትእዛዝ አውሮፕላን ማንቀሳቀስ አልችልም" አሏቸው:: አቶ መኮንን ይህ ዕቅዳቸው ቢሰናከልም ሌላ መንገድ ሞከሩ። ይኸውም የጄኔራል ጽጌ ዲቡ ባለቤት ወንድም፣ አቶ ታምራት ተስፋዬ ባጋጣሚ በጋና የኢትዮጵያ ኤምባሲ ሁለተኛ ጸሐፊ ሆኖ በዚያን ዕለት ይሔድ ስለነበር፤ አጋጣሚውን በመጠቀም የሚከተለውን ልዩ ማስታወሻ አስይዘው ሰደዱት:: የማስታወሻው ይዘትም "ወደ ብራዚል አለመሔድዎን አጥብቄ! አጥብቄ! አጥብቄ! እፈልገዋለሁ!" የሚል ነበር:: ሆኖም፣ መልእክተኛው እንደታሰበው ንጉሠ ነገሥቱን፣ ምዕራብ አፍሪካ ላይ ሳይደርስባቸው ቀድመውት ሔዱ:: የሚገርመው ጄኔራል ጽጌ ዲቡ ከንደኛቸው ከጄኔራል መንግሥቱ ጋር ሆነው የአቶ መኮንንን መልእክት ይዞ ወደ ጋና የሚሔደውን የባለቤታቸውን ወንድም፣ አቶ ታምራት ተስፋዬን አውሮፕላን ማረፊያ ድረስ አብረው ሒደው ሸኝተውት ነበር የተመለሱት። ሸኚና ተሸኝ ስለ መልእክቱ ይዘት የሚያውቁት ወይም የጠረጠሩት ነገር አልነበረም::[6]

ያም ሆነ ይህ፣ ከላይ የሠፈረው ንጉሡ ስለገርማሚ ለጄኔራል መንግሥቱ የላኩት የቴሌግራም መልእክት ተዳፍኖ ውስጥ ለውስጥ ሲጢያጢያስ የቆየውን የመፈንቅለ መንግሥት ጥንስስ፤ በቂ ጥናትና ዝግጅት ሳይደረግ የለውጡ እሳት ባልታቀደለት ጊዜ እንዲጫር አድርጐታል:: በመሆኑም የለውጡ መሪዎች በተለይም ጄኔራል መንግሥቱ፣ ከዚህ የገርማሜ አዲስ አበባ ከተማ መቆየት አይበጅም ከሚለው ቴሌግራም መልእክት በኋላ ሊከተል የሚችለውን ሁኔታ በመገመት "ሳይቀድሙኝ ልቅደም" የሚል ርምጃ ለመውሰድ ግድ ሊሆንባቸው እንደቻለ መገመት ይቻላል:: ይህን ጉዳይ ወደፊት ተዛማጅ ከሆኑ ነጥቦች ጋር ስለማነሳ እዚህ ላይ በመተው፤ የመፈንቅለ መንግሥቱን ዐድማ በግብታዊነት ወደተግባራዊ እንቅስቃሴ መሸጋገር በሚያመለክቱት የዕለቱ ዝግጅቶች ላይ ላተኩር::

6 አንድ ስሙ እንዲጠቀስ ያልፈለገ የአቶ መኮንን ሀብተ ወልድ የቅርብ ረዳትና ባለሥልጣን ዲፕሎማት የነበረ ወዳጄ የነገረኝ፤

## የመፈንቅለ መንግሥቱ አጀማመር[7]

ታሪካዊው የመፈንቅለ መንግሥት እንቅስቃሴ ጥንስሱ ወደ ተግባር የተሸጋገረው፣ ታኅሣሥ ፬ ቀን ፲፱፻፶፫ ዓ.ም. ከቀኑ ፲፩ ሰዓት ላይ ነበር። በዚህ ዕለት የክብር ዘበኛ አዛዥ ጄኔራል መንግሥቱ ሹፌራቸውን የሃምሳ አለቃ ታከለን ልከው ም/የመቶ አለቃ አስፋው ጀማነህን፣ ም/የመቶ አለቃ ታምሩ ጉዳን እና ም/የመቶ አለቃ ቦጋለ ወልደ ማርያምን ወደቢሮዋቸው አስጠሩ። ተጠሪዎቹ ቢሮአቸው እንደደረሱ ም/የመቶ አለቃ አስፋው ጀማነህን ከአጃቢ ክፍሎች ግምጃ ቤት ለአንድ የአጃቢ ቡድን የሚሆን በቂ ትጥቅ፣ መትረየስ ጠመንጃና ሽጉጥ እንዲያመጣ አዘዙት። መኮንኑም "ጌታዬ አጃቢዎች የሉም" አላቸው። "እኔ አጃቢዎች አዘጋጃለሁ መሣሪያው ወደቢሾፍቱ የሚላክ ስለሆነ ፈጠን በል" አሉት። በትእዛዙ መሠረት መሣሪያዎቹ ከምሽቱ አንድ ሰዓት ገደማ ከጽሕፈት ቤታቸው ደረሱ። ከዚህ በኋላ ደግሞ ከላይ ከተጠቀሱት ሰዎች በተጨማሪ ከየቤታቸው እየተጠሩ፤ የሻምበል አሥራት ደፈረሱ፣ የሻምበል ባዬ ጥላሁን፣ የሻምበል ማሞ ሀብተ ወልድ፣ የሻምበል መሰለ መኩሪያና የመቶ አለቃ በቀለ መንገሻ መጡ። ከዚህ በኋላ ስለነበረው ሁኔታ የሻለቃ አንጋጋው[8] እንዲህ ሲሉ ይገልጻሉ።

> ታኅሣሥ ፬ ቀን ፲፱፻፶፫ ዓ.ም. ከሰዓት በኋላ ፲፩ ሰዓት ከቢሮዬ ስልክ ተደወለ። "ሀሎ" አልኩ። የስማሁት የአቶ ታደሰ ገብረ ወልድ የክብር ዘበኛ ዋና ጸሐፊ ድምፅ መሆኑን አወቅሁ። እሳቸውም "የሻለቃ አንጋጋው ነህ? ጄኔራል መንግሥቱ ይፈልግሃል" ብለው የስልክ መሥመሩን ለጄኔራል መንግሥቱ አስተላለፉት። ጄኔራል መንግሥቱ ባለመድኩትና ባልጠበኩት የቁጣ አነጋገር፣ ያልሆነ ምክንያት ፈጥረው በጠየቁኝ ጉዳይ ላይ ጥቂት ቃላትን ከተለዋወጥን በኋላ፣ በመጨረሻው "እፈልግሃለሁ። በአስቸኳይ ቢሮዬ እንድትመጣ" አሉና ስልኩን ዘጉት። እኔም ወዲያው ደረስኩና ወደ ቢሮአቸው ልገባ ስል፣ አቶ ታደሰ ገብረ ወልድ ሲወጡ በር ሲከፍቱ ተገናኘን። እርሳቸውም በተለመደ የእርጋታ አነጋገራቸው፣ "መጣህ? መንግሥቱ ይፈልግሀል" አሉኝ። መዝጊያው እንደተከፈተ ከመንግሥቱ ጋር ተያየን እና "መጣህ? ትንሽ ቆየኝ። እፈልግሀለሁ" አሉኝ። በሩን ዘግቼ ቆም እንዳልኩ ደግሞ "አንጋጋው" ብለው ጠሩኝ። እኔም በር ከፍቼ ገባሁ። በዚህ ጊዜ መንግሥቱ ፊታቸው፣ ዓይናቸው፣ በአጠቃላይ ሁኔታቸው ተለዋውጦ ዓየሁ። ይቀመጣሉ፣ ይነሣሉ። በዚህ ሁኔታ ጥቂት እንደቆየን፣ "የሻምበል ክፍሌ ወልደ ማርያምን ታገኘዋለህ? አሉኝ። እኔም "እፈልገዋለሁ" አልኳቸው። "እንግዲያውስ በቶሎ ፈልገህ ይዘህልኝ ና" ሲሉኝ ከቢሮ ወጥቼ ወደ መኪናዬ አመራሁ።
>
> የሻምበል ክፍሌ ወልደ ማርያም የሥራ ቦታ ወደ ሆነው ፫ኛ ሻለቃ ጦር ሠፈር ደርሼ ብጠይቅ፣ ዛሬ ሥራ አልገቡም፤ እቤታቸው ናቸው ተባልሁ። የክፍሌ ቤት ፈረንሳይ ሌጋስዮን አቅራቢያ ስለነበረ፤ ወደዚያው

---

[7] ስለመፈንቅለ መንግሥቱ አጀማመር ያቀረብኩት የሻለቃ አንጋጋው የነገሩኝንና በጽሑፍ የሰጡኝን ጄኔራል መንግሥቱ ለፍርድ ቤት ከሰጡት ቃል ጋር በማዛመድ ነው።

[8] ዝኒ ከማሁ

አመራሁ:: በመንገድ ላይ እያለሁ፣ የጄኔራል መንግሥቱ ያልተለመደ ሁኔታ ከምን የመጣ ነው? በማለት እያሰላሰልኩ፤ ልክ ከአሜድላ መንገድ ወደ ፈረንሳይ ኤምባሲ ከክብር ዘበኛ ጋራዥ ወደ መድፈኛ ሠፈር ከሚያስተላልፈው መስቀለኛ መንገድ ስደርስ፤ ሁኔታዎችን ለማገናዘብ የሚያስችለኝ አንድ ነገር ትዝ አለኝ:: ይኸውም የጄኔራል መንግሥቱን መኖሪያ ቤት እንቅስቃሴ ማወቅ ነበር:: ወደዚያ አመራሁና፣ መኪናዬን ከግቢያቸው አቁሜ በቀጥታ ወደ ምግብ ማዘጋጃው ስገባ፤ ሠራተኞቻቸው የብፌ ጠረጴዛ ዘርግተው የበሰለ ምግብ እየደረደሩ ነበር:: ከዚያ "ምን ጉዳይ አለባችሁ" ብዬ ብጠይቅ፤ ሠራተኞቹ "ገርማሜ ወደ ግዛቱ ስለሚሔድ መሰነባበቻ ግብዣ ይደረጋል›› የሚል መልስ ሰጡኝ::

ይህን በመረዳቴ በመጠኑም ቢሆን ያለብኝን ሥጋት ቀነሰልኝና የሻምበል ክፍሌ ወደሚኖርበት ፈረንሳይ ሌጋሲዮን አቅጣጫ አምርቼ ከቤት አጥቼው በመመለስ ላይ ሳለሁ ፈረንሳይ ድልድይ አጠገብ አገኘሁት:: ጄኔራል መንግሥቱ እንደሚፈልጉት ስነግረው በወቅቱ በወሰደው መድሐኒት መዳከሙን እያወጋኝ አብረን ወደ ጄኔራል መንግሥቱ ቢሮ ሔድን:: ሻምበል ክፍሌ መምጣቱን ገብቼ ነገርኳቸውና «ይግባ» አሉኝ:: ክፍሌ ገባና ሁለታችንም እንደቆምን፤ ጄኔራል የሻምበል ክፍሌን ሥራ አስመልክተው፤ «፫ኛ ሻለቃ ሠፈር የሚመገቡት ወንደላጤ ወታደሮች «በምግብ ተበደልን» በማለት ለአልጋ ወራሽ አቤቱታ አቅርበዋል:: «ይህ እስኪሆን አንተ ምን ትጠብቃለህ?» እያሉ ጮኹበት::' ክፍሌም መልሶ መላልሶ ወታደሮችን የሚያስቆጣ ምንም ጉድለት እንደሌለ ሲያስረዳ ተቀባይ ስላላገኘ፤ በእጄ አለ ያሉትን ወታደሮች ለአልጋ ወራሽ ያቀረቡትን አቤቱታ እንዲያሳዩት ጠየቀ:: ረዳት መኮንኑን ጠርተው «ወታደሮች በምግብ የደረሰባቸውን በደል ያሳወቁበትን ማመልከቻ አቅርብልኝ» አሉት:: ሻምበል አሰፋ «ይህን የመሰለ አቤቱታ አልደረሰንም::» በማለቱ፤ «አሁን ከፊቴ ነበር» እያሉ በጠረጴዛቸው ላይ ወረቀቶች ማገላበጥ ጀመሩ:: በዚህ ወቅት የሻምበል ክፍሌ ደነገጠ:: ከጥቂት ግርግር በኋላ «እውጭ ቆዩኝ» ስላሉ፤ ተያይዘን ወደ ረዳት መኮንኑ ቢሮ ተዛወርን::

ጥቂት እንደቆየን የሻምበል ክፍሌ ብቻውን ተጠራና ገባ:: ቀጥሎም እኔ ተጠርቼ ገባሁና «አባ ሐና ስልክ ደውለው የግርማዊት እቴጌ ቪላ የአጥር ግንብ ስለፈረሰ በአፋጣኝ ይሠራልን ብለዋል:: ነገ ጠዋት ሠራተኞችን በጠቅላላ ወደዚያ አሰማርተህ እንድታስጨርስ:: ግን ከምሽቱ ፪ ሰዓት መጥተህ አብረን ሔደን እናየዋለን» የሚል ትእዛዝ ሰጡኝና ተመለስኩ:: ከምሽቱ ፪ ሰዓት ክብር ዘበኛ ጠቅላይ መምሪያ ደርሼ ወደ አዛዡ ቢሮ ሳመራ፤ ከሕንፃው ፫ኛ ፎቅ ወለል ላይ ሦስት መኮንኖች ፊንጢር፤ ፊንጢር ብለው ቆመዋል:: ለትንቅንቅ የተዘጋጁ ይመስላሉ» በአጠገባቸው ሳልፍ ሰላምታ ለመስጠት አልተቻገሩም።[9] እነሱም ምክትል የመቶ አለቃ አስፋው ጀማነህ፣ ምክትል የመቶ አለቃ ቦጋለ ወልደ ማርያም እና ም/የመቶ አለቃ ታምሩ ጉዳ ናቸው:: እነሱን አልፌ ከጄኔራል

[9] በወታደር ሥርዓት አንድ የበላይ መኮንን ሲመጣ ሰላምታ መስጠት፤ ተገቢም ግዴታም ነው::

> መንግሥቱ ረዳት መኮንን ቢሮ ከፍቼ ስገባ፤ ስድስት የሚሆኑ የ፪ኛው ኮርስ መኮንኖች ተቀምጠው አገኘኋቸው:: እነርሱም የሻምበል አሥራት ደፈረሱ፣ የሻምበል ባዬ ጥላሁን፣ የሻምበል መሰለ መኩሪያ፣ የሻምበል ማሞ ሀብተ ወልድና የጄኔራል መንግሥቱ ረዳት መኮንን የሻምበል አሰፋ ጌታነህ ሲሆኑ፤ ስድስተኛው ማንነቱ ተዘነጋኝ::[10] ከፊሎቹ ካፖርት ለብሰዋል:: ከፊሎቹ በዩኒፎርም ብቻ ናቸው ተደባልቄ ተቀመጥኩ:: ከሁላችንም የሚሰነዘር ንግግር አልነበረም:: ቢሮው ዝምታ ሰፍኖበት ነበር . . .[11]

እንደ ኮሎኔል አንጋጋው ከምሽቱ ፪ ሰዓት ከ፲ ደቂቃ ላይ ጄኔራል መንግሥቱ ከጄኔራል ጽጌ ዲቡ ጋር መጡ:: መኪናቸውን ከቢሮው መዳረሻ ላይ አቁመው፤ መንግሥቱ በሊፍት ሲወጡ ጄኔራል ጽጌ በደረጃው መውጣት ይዘው ኖሮ ጄኔራል መንግሥቱ ቀድመው እንደገቡ፤ «አንጋጋው» ብለው በመቻኮል ጠርተዋቸው በሩን ከፍተው እንደገቡ፣ «ጄኔራል ጽጌን አስቸግረው» ይሏቸዋል:: ኮሎኔል አንጋጋውም፣ "ምን ብየ ነው የማስቸግር" ቢሏቸው «ጥፋቱን ብነግርበት ዛተብኝ እያልክ አስቸግረው» ይሏቸዋል:: ይሁን እንጂ ጄኔራሉ ንግግራቸው በጥድፊያ ስለነበር፤ በሐሳብ ሳይግባቡ፤ ጄኔራል ጽጌ መዝጊያ ከፍተው ይገቡና የሻለቃ አንጋጋው ወደ ነበሩበት ክፍል እንዲመለሱ ተነግሯቸው ይወጣሉ:: ከዚያም «መንግሥቱና ጽጌ» ይላሉ የሻለቃ አንጋጋው፣ ሁለቱ ብቻ በቢሮ ውስጥ ሆነው ምን እንደተነጋገሩ ባላውቅም፣ መንግሥቱ ጽጌን ለማሳመን «ንዋይ ይሙት!» በማለት መሐላ ሲደረድሩ ይሰማን ነበር:: በኂላ እንደተረዳሁት ከብዙ መሐላ በኋላ «በአስተዳደር ምክንያት ልዑል አልጋ ወራሽን ለመያዝ ስለፈለግሁ፤ አንተንም ስለምጠረጥርህ ሽጉጥህን ስጠኝ:: እርሳቸው ከተያዙ በኋላ እመልስልኻለሁ» በማለት ሽጉጣቸውን ተቀበሏቸው::[12] ከዚያም ጄኔራል መንግሥቱ የቢሮ በር ከፍተው መኮንኖች ከተቀመጡበት ቢሮ አልፈው የሻምበል ባዬ ጥላሁንን «ጄኔራል ጽጌ ዲቡን ጠብቅ» ብለው ማዘዛቸውን፤ የሻምበሉም በደረበው ካፖርት ውስጥ ኡዚ ይዞ ኖሮ አውጥቶ ጄኔራል ጽጌን ከተቀመጡበት እንዳይነቃነቁ እንደደገነባቸውና ከዚህ ጊዜ አንሥቶ መፈንቅለ መንግሥቱ እንደተጀመረ፤ ጄኔራል ጽጌም እንደ እሥረኛ እንደሆኑ፤ ኮሎኔል አንጋጋው ይገልጻሉ::

ከዚህ ቀጥሎ ራሳቸው ሻለቃ (ኂላ ኮሎኔል) አንጋጋው የተገኙበት ጄኔራል መንግሥቱ ከአሥር በላይ የሚሆኑ መኮንኖችን አንድ ቢሮ ውስጥ ሰብስበው በምሽቱ ስለሚከናወነው ግዳጅ መመሪያ ሲሰጡ «ጦር ሠራዊት የግርማዊ ጃንሆይን መራቅ ጠብቆ አልጋ ወራሹንና ሚኒስትሮችን ጨምሮ የንጉሡ ነገሥቱን መንግሥት ለመገልበጥ ዐምፃል:: ሚኒስትሮችም በአሁኑ ሰዓት ግርማዊት እቴጌ ቪላ ተሰብስበው እየመከሩ ነው:: አሁን የእኛ ግዳጅ በስብሰባ ላይ የሚገኙትን ሚኒስትሮች መያዝ

---

[10] የሙቶ አለቃ በቀለ መንገሻ ነበር ስላቸው፤ ‹‹አዎ! አዎ! ትክክል ነህ›› ብለው በመደነቅ ዓይተው [የሙቶ አለቃ በቀለ መንገሻ አስር ቤት ሳለን አጀማመሩን ገልጸልኝ ነበር] ገለጻቸውን ቀጠሉ::

[11] ሻለቃ (ኂላ ኮሎኔል) አንጋጋው

[12] ጄኔራል መንግሥቱ ለፍርድ ቤት በሰጡት ቃልም ተረጋግጧል::

ነው።» አሏቸው። ከዚያም «ማነው ሳበላው ጌታ የማይሞት?» ሲሉ፤ የሻምበል ክፍሌ ወልደ ማርያም ቀበል አድርገው ‹‹እኔ እሞታለሁ›› አሉ። ከዚህ ስብሰባ መግለጫ በኋላ ነው ጀኔራል መንግሥቱ ለተሰበሰቡት መኮንኖች የመፈንቅለ መንግሥት ዕቅድ ስለመሆኑ ፍንጭ ሳይሰጡ፤ በበርካታ መኪናዎች ይዘዋቸው ወደ ግርማዊት እቴጌ ቪላ በመሄድ፤ ለዕለቱ ተረኛ የጥበቃ ኃላፊ ለሻለቃ ተፈራ ገለቱ፣ «ማንኛውም ንጉሣዊ ቤተሰብ ወይም ሌላ ባለሥልጣን ወደ ግቢው መግባት ይፈቀድለታል፤ ወደ ውጭ መውጣት ግን ክልክል ነው» ሲሉ ትእዛዝ የሰጡት።

ጀኔራል መንግሥቱ ወደ እቴጌ ቪላ የወሰዱዋቸውን መኮንኖች በዋናው በር ሳይሆን በሁለተኛው በር አስገብተው፤ በዛፎቹ ጥላ ሥር ተጠልለው እንዲቆዩ ነገሯቸው። ወደ ቪላው ግቢ ከመግባታቸው በፊት፣ «ከአሁኑ ሰዓት ጀምሮ ሚኒስትሮችና የጦር አለቆች ይመጣሉ። ወደ ቅጥር ግቢው ሲገቡ እንዳያዩአችሁ በዛፎቹ ሥር ተከለሉ። እኔ ምልክት እሰጣችኋለሁ፣ ያን ጊዜ ወጥታችሁ ትይዟቸዋላችሁ። በምትይዙበት ጊዜ ግን የጥይት ድምፅ እንዳይሰማ ጥንቃቄ እንዲደረግ» ብለው አዘዙ። ይህን ትእዛዝ ለመኮንኖቹ ከሰጡ በኋላ፤ ጀኔራል መንግሥቱ ለፍርድ ቤት በሰጡት ቃል መሠረት አባ ሐና ጂማን ከውስጥ አስጠሯቸው። አባ ሐና ተጠርተው እንደመጡ የጦሩ መንፈስ አስጊ መሆኑን ገለጹላቸው። አባ ሐናም እንደመደንገጥ ብለው፤ «እንግዲያውስ ራስ አንዳርጋቸው መሳይ እዚህ ስላሉ ከእሳቸው ጋር ብትነጋገሩና የሚሻለውን ብታደርጉ» አሉና ራስ አንዳርጋቸውን ጠርተው ከጀኔራል መንግሥቱ ጋር አገናኟቸው። ራስ አንዳርጋቸው ጉዳዩን ከጀኔራል መንግሥቱ እንደሰሙ፤ የመደነቅም ሆነ የመደንገጥ ስሜት አላሳዩም። ኋላ ላይ የዚህን ምክንያት እንደተረዳሁት ስለ መፈንቅለ መንግሥቱ እንቅስቃሴ ራስ አበበ ቀድመው ሰምተው ለግርማዊት እቴጌ መነን ነግረዋቸው ስለነበር፤ እቴጌም ለአልጋ ወራሽ፣ ለልዕልት ተናኘ ወርቅና ለራሳቸው ለራስ አንዳርጋቸው መሳይም የነገሯቸው በመሆኑ ነበር።[13] ጀኔራል መንግሥቱም ይህን ሲያዩ፣ የመፈንቅለ መንግሥቱ እንቅስቃሴ ምሥጢር ቀደም ብሎ አፈትልኳል የሚል ጥርጣሬ ያዛቸው። ጥርጣሬውም ትክክል ነበር። ምክንያቱም ቀደም ሲል እንደገለጹኩት፣ አቶ መኮንን ሀብተ ወልድ የመፈንቅለ መንግሥቱን እንቅስቃሴ ምሥጢር ደርሰውበት ጥብቅ መልእክት ለንጉሡ መላካቸው ነው።

አቶ መኮንን ሀብተ ወልድ በሆነ ወገን መፈንቅለ መንግሥት ሙከራ እንደሚደረግ ማወቃቸውን የሚያሳየው ታኅሣሥ ፬ ቀን ፲፱፻፶፫ ዓ.ም. የመፈንቅለ መንግሥት ሤራ ተጠንስሷል በሚል፤ ጀኔራል መንግሥቱን፣ ጀኔራል ጽጌንና ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህን ለማነጋገር መጥራታቸው ነው። ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ ሳይሔድላቸው ቢቀርም ሁለቱን በቢሮአቸው አነጋግረዋል። ከእነሱ የአወንታ ፍንጭ

13 ይህንን ያልኩት የልዕልት ተናኘ ወርቅ ልጅ ልዕልት ሶፊያ ከደርግ እሥር ከተፈቱ በኋላ በ፲፱፻፶፬ ዓ.ም. ስለጥንስሱ በዚህ በኩልና በአቶ መኮንን በኩል ለልዕልት ተናኘ ወርቅ መረጃው ደርሶ እንደነበር ስላጫወቱኝ ነው።

ባለመገኘቱ፤ ለሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ ስልክ ደውለው የመፈንቅለ መንግሥት ጥንስስ ሹክሹክታ መኖሩን ገልጸው ትብብር ቢጠይቁ፤ ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ፤ "እኔ ከእርስዎ የተሻለ መረጃ አለኝ:: ምንም ነገር የለም" በማለት እንደመለስ ምንጮች ይጠቁማሉ::[14] ራስ አንዳርጋቸውም ተወጠነ ስለ ተባለው ወታደራዊ እንቅስቃሴ ከጄኔራል መንግሥቱ የተነገራቸውን ካዳመጡ በኋላ ሹክሹክታው ደርሷቸው ለነበሩት ለልዑል አልጋ ወራሽ እንዲሰሙት አደረጉ::

ልዑል አልጋ ወራሽም ስለመፈንቅለ መንግሥት ጥንስስ በግልጽ እንደሰሙ፤ «ታዲያ እኛው ተነጋግረንበት አንድ ነገር እናድርግ ወይስ ሌሎችንም እንጨምር?» በማለት ነበር ለነጋሪዎቻቸው ጥያቄና አስተያየት ያቀረቡት:: ጥያቄው እንደቀረበ፤ «ራስ አንዳርጋቸው፤ ራስ አበበ አረጋይና አቶ መኮንን ሀብተ ወልድ ይጨመሩበት» ብለው ሐሳብ አቅርበው እነሱን ለመጥራት ስልክ ወደሚገኝበት ቦታ ለመሔድ መራመድ እንደጀመሩ፤ ራስ አንዳርጋቸው «ሜጀር ጄኔራል መርዕድ መንገሻና ሜጀር ጄኔራል ከበደ ገብሬም ቢጨመሩ መልካም ነው» አሉና ወዲያው መለስ አድርገው «ሜጀር ጄኔራል መርዕድ መንገሻ የደም ግፊቱና ስኳሩ ከፍ ብሎበት ለሦስት ቀናት ከቤቱ ተኝቶ ነው የሰነበተው፤ አልወጣም" በማለት ተናገሩ:: ጄኔራል መንግሥቱም «እንግዲያውስ ሜጀር ጄኔራል መርዕድ ካልሆነለት ሜጀር ጄኔራል ከበደ ባይመጣም ምንም አይደል:: ክቡር ራስ አበበና አቶ መኮንን ሀብተ ወልድ[15] በቶሎ ይጠሩና ሥራችንን እንጀምር» አሉ:: ልዑል አልጋ ወራሽም «መጀመሪያ ከአለቆቻቸው ጋር እንነጋገር:: እነ መርዕድ ካስፈለጉ በኋላ ይመጣሉ» ብለው ጄኔራል መንግሥቱ የቀረበውን ሐሳብ አጢነው መልስ ሳይሰጡ ራስ አንዳርጋቸው መሳይ፣ ራስ አበበንና አቶ መኮንን ሀብተ ወልድን በስልክ ለመጥራት ከነጄኔራል መንግሥቱ ተለይተው ወደ ሌላ ክፍል ሔዱ::

በስልኩ ጥሪ መሠረት ራስ አበበ አረጋይና አቶ መኮንን ሀብተ ወልድ ወደ እቴጌ ቪላ ጊዜ ሳይወስዱ መጡ::[16] ተጠሪዎቹ እቴጌ ቪላ ደርሰው ከየመኪናቸቻቸው እንደወረዱ፤ በየዛፉ ሥር ተከልለው የነበሩ የክብር ዘበኛ መኮንኖች ይዘው ጄኔራል መንግሥቱ መኪና ውስጥ አቆዩዋቸው:: ከእነዚህ በመቀጠል ወደ እቴጌ ቪላ የመጡት አፈንጉሥ እሸቴ ገዳ ነበሩ:: እርሳቸውም ተጠልፈው ተያዙና በዚያው አካባቢ ከነበረ አንድ መኪና ውስጥ እንዲቀመጡ ተደረገ:: በዚህ ሰዓት ራስ አንዳርጋቸው እየወጡ እየገቡ በማየት፤ በስልክ የጠሯቸውን ባለሥልጣኖች በጉጉት ይጠባበቁ ነበር:: «እንዴት እስካሁን አልመጡም? ምን ሆኑ?» እያሉ ጄኔራል መንግሥቱን በመጠየቅ

---

[14] ስሙ እንዲጠቀስ ያልፈለገው የአቶ መኮንን ሀብተ ወልድ ረዳት የነገረኝ፤

[15] ጄኔራል መንግሥቱ አቶ መኮንንን ክቡር አይሉዋቸውም:: ለመንግሥቱ ሥርዓት መበላሸት አንዱና ዋናው ተጠያቂ እሳቸውን በማድረግ አይወዱዋቸውም ነበር (ይህ ግንዛቤ በኮሎኔል አንጋጋው ዘገባም ተንፀባርቋል)::

[16] ዝኒ ከማሁ

ላይ እንዳሉ፤ ም/የመቶ አለቃ አስፋው ጀማነህ ጨለማ ለብሶ ተከልሎ ከነበረበት ዛፍ ሥር ተነሥቶ ሔዶ በመያዝ ወደ ዛፉ ጥላ ሥር ዞር አድርጐ አስቀመጣቸው።

ከዚህ በኋላ ልዑል አልጋ ወራሽ ገብተውበት ከነበረው ክፍል ሲወጡ፣ ጄኔራል መንግሥቱ ከመተላለፊያው ኮሪደር ላይ ቆመው ነበርና ወደ ውጭ እንዲወጡ የእጅ ምልክት አሳዩዋቸው። ይኸውም ወደ ውጭ ወጥተው ተጠርተው የመጡትን ባለሥልጣኖች ያነጋግሩ የሚል ይመስል ነበር። ልዑል አልጋ ወራሽ ከቪላው የይውጡ የእጅ ምልክት ደርሷዋቸው ከመውጣታቸው በፊት ለታላቅ እህታቸው ለልዕልት ተናኘ ወርቅ «የአደራ ቃል» ሰጥተዋል ይባላል። የአደራው ቃል «አባዬ! አባዬ! የእናቴን ነገር አደራ! እኔ የምመለስ አይመስለኝም» የሚል ሥጋት የተሞላበት የኑዛዜ ቃል ነበር።[17] ልዑል አልጋ ወራሽ ምልክት ወደ ተሰጡበት አቅጣጫ ሲወጡ፤ የጠበቃቸው ገርማሜ ይነዳው የነበረ አንድ መኪና ነበር። ስለዚህ ከዚሁ መኪና ውስጥ ገብተው እንዲቆዩ ተደረገ።

እንደልዕልት ሶፊያ ልዑል አልጋ ወራሽ በዚህ ሁኔታ ተይዘው ከግርማሜ መኪና ውስጥ እንደገቡ፤ አባ ሐና ወደ ገነተ ልዑል ቤተ መንግሥት ለመሔድ ፈለጉ። ነገር ግን ከሌላ አንድ መኪና ውስጥ ገብተው እንዲቆዩ ተደረጉ። በዚያ ምሽት ከልዑላን ቤተሰብ መካከል ልዕልት ተናኘ ወርቅና ልዕልት ሣራ ግዛው በእቴጌ ቪላ የነበሩ ሲሆን፤ ልዑል ሣህለ ሥላሴ ደግሞ በእቴጌ ቪላ ግብር ተነሥቶ ፊልም መታየት ሲጀምር፤ መኳንንቱ እየተጠሩ ከመያዛቸው ጥቂት ደቂቃዎች ቀደም ብሎ ግርማዊት እቴጌን ተሰናብተው ወደ ቤታቸዉ ስለሔዱ፤ መፈንቅለ መንግሥቱ ተጀምሮ እስከሚያልቅ የቆዩት ከቤታቸው ነበር። በዚያ ምሽት፣ የልዑል መኮንን ልጆች ልዑል ወሰን ሰገድ፣ ልዑል ሚካኤል፣ ልዑል ዳዊትና ልዑል በዕደማርያም በገነተ ልዑል ቤተ መንግሥት ዱክ ቤት (አሁን የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የሕግ ፋኩልቲ የሆነው ሕንፃ) ውስጥ ነበሩ። እንዲሁም ልዕልት መድፈሪያሽ ወርቅ አበበና ልጆቻቸው ልዑል ዘርዓ ያዕቆብ አስፋ ወሰን፣ ልዕልት ማርያም ስና አስፋ ወሰንና ልዕልት ሲኒን አስፋ ወሰን አልጋ ወራሽ ግቢ ይገኙ ነበር። እነዚህ ልዑላን አለመያዛቸውም በጠቅላይ መምሪያው ለነበሩት መኮንኖች መወያያ ነበር።

በዚያ ምሽት በእቴጌ ቪላ መፈንቅለ መንግሥቱ ተጀምሮ ልዑል አልጋ ወራሽና ሌሎች በቁጥጥር ስር የዋሉ ባለሥልጣኖች ከላይ በታየው ሁኔታ ተይዘው በመኪና ወደ ክብር ዘበኛ ጠቅላይ መምሪያ ተወሰዱ። ይህን አስመልክቶና ቀጥሎ ስለተከናወነው እንቅስቃሴ የተሻለ መረጃ ካለበትና ጄኔራል መንግሥቱ ከተናገሩት እጠቅሳለሁ።

> በእቴጌ ቪላ የተያዙትን መኳንንት ጠቅላይ መምሪያ ላይ አውጥቼ ጠባቂ ካደረኩ በኋላ... ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህን በስልክ ለመጥራት ወደ ምድር ቤት በምወርድበት ጊዜ በመስኮት የጄኔራል መኮንን ደነቀ መኪና ወደ ላይ ሲወጣ አየሁ። በአፈ ንጉሥ እሸቴ ገዳ መኪና ተከተልኩት። ጄኔራል መኮንን

[17] ይህን የነገሩኝ ልዕልት ሶፍያ ናቸው

> ከመኪና ሳይወርድ ደረስኩበትና ክብር ዘበኛ ጠቅላይ መምሪያ ለመሔድ ተከተለኝ አልኩት፡፡ ሲደርስ ወደ ፎቅ ወስጄ እዚያው ተውኩት፡፡[18]

ይሉና ከምሽቱ ፫ ሰዓት ገደማ ሲሆን ደግሞ፣ ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህን ስልክ ደውለው መጥራታቸውንና ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ ክብር ዘበኛ ጠቅላይ መምሪያ እንደደረሰ በሳቸው በኩል የተደረገውን የእንቅስቃሴ ጅምር መግለጫ ከሰማ በኋላ፣ ‹‹፩ኛ ሜጀር ጄኔራል መርዕድ የጦር ኃይሎች ኤታማዦር ሹም፣ ፪ኛ ሜጀር ጄኔራል ከበደ ገብሬ የምድር ጦር አዛዥ፣ ፫ኛ ኮሎኔል አሰፋ አየነ የአየር ኃይል ምክትል አዛዥ የታሉ?›› ብሎ እንደጠየቀ ይዘረዝራሉ፡፡ ጄኔራል መንግሥቱም «ወርቄ![19] ሁሉም ይመጣሉ። ምንም ችግር የለም ተስማምተዋል። ሜጀር ጄኔራል መርዕድ የደም ግፊቱና ስኳሩ ጨምሮበት ታሞ ከቤት ተኝቷል እንጂ ይመጣ ነበር» በማለት መልስ ሲሰጡት፣ ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ «በተለይ ሜጀር ጄኔራል መርዕድን ውጭ ትተን በምንም ዓይነት መንገድ ከዚህ ሥራ አንሠራም፡፡ ካመማቸው እዚህ አንድ ክፍል ውስጥ የመንገድ አልጋ ይዘርጋላቸውና ይተኙ» የሚል ጠንከር ያለ አስተያየት ሰጠ፡፡ ጄኔራል መንግሥቱም በረጋ መንፈስ እንደገና «ወርቄ! አይሆንም! የተበሳጨ እንደሆነ ደሙ ከራሱ ውስጥ ሊፈስ ይችላል፡፡ አይሆንም!» ብለው ይነጋገሩበት ከነበረው ክፍል ወጥተው ሔደው ትንሽ ከቆዩ በኋላ፣ ተመልሰው ገብተው «ወርቄ፣ ለልዑል አልጋ ወራሽም ነግሬአቸው ታሞ ከሚገኝበት እንዲመጣ በማድረጉ አልተስማሙም፣ አታስብ! በሱ በኩል ምንም ችግር አይመጣም፣ የቀሩት ሁለቱም ይመጣሉ፡፡» ብለው በመግለጽ ለማሳመን ሞከሩ፡፡ ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ በዚህ ውሳኔ በማዘንና በመናደድ ሁለት እጆቹን አማትቶ በቃ! አለቀ! ብሎ አንገቱን ደፍቶ ዝም አለ፡፡ ከዚያም ሲጃራ አስገዝቶ እያጤሰ በትካዜ ሲያስብ ቆይቶ «አበቃ! እነዚህ ሰዎች ተይዘው ካልመጡ ይህ እንቅስቃሴ ውጤት አይኖረውም፡፡» ብሎ እጆቹን አጣጥፎ ቁጭ አለ፡፡[20]

ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህን ቅሬታ ላይ የጣለው ሐሳብ በአካባቢው ለነበሩ መኮንኖች የዕለቱና የማግሥቱ የመነጋገሪያ አርእስት ነበር፡፡ ጄኔራል መንግሥቱ ግን ይህን ቅሬታውን ትቶ የሚቀጥለውን ተግባር በማድረግ ድርሻውን እንዲወጣ ስለጠየቁት፣ ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ በእንዲህ ያለ ሁኔታና ቦታ አጀማመሩ ላይ ባየው ጉድለት ቢያዝንም ዳር ሆኖ ማየት፣ «ቅቤ ተቀብቶ ዝንብ አይንካኝ» እንደ ማለት ስለሆነበት፣ የመፈንቅለ መንግሥቱ እንቅስቃሴ የሚጐለብትበትን ሥራ ማካሔድ ጀመረ፡፡ የሕዝብ ፀጥታ ጥበቃ መምሪያ የቴክኒክ ክፍል ኃላፊ የነበረው፣ የመቶ አለቃ (በኋላ ብርጋዴር ጄኔራል) ተድላ ደስታ ስለሁኔታው የነገረኝም የጉድለቱን አሳሳቢነት አጉልቶ የሚያመለክት ነበር፡፡

> ክብር ዘበኛ ጠቅላይ መምሪያ ተጠርቼ ሔድኩ፡፡ ከምሽቱ ፬ ሰዓት ገደማ ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ ከአንድ የክብር ዘበኛ የሻምበል ጋር አገናኘኝ፡፡

---

18 *ጄኔራል መንግሥቱ ለፍርድ ቤቱ ከሰጡት ቃል*

19 *ጄኔራል መንግሥቱ ወርቅነህን በጣም ይወዱት ስለነበር ወርቄ እንጂ ወርቅነህ ብለው አይጠሩትም ነበር፡፡*

20 *ሻለቃ ተሰማ ዋቅጅራ እንደነገረኝ፡፡*

ከዚያ አራዳ (ፒያሳ)ና ራስ ሆቴል አጠገብ ያለውን የስልክ ማዞሪያ፣ እንዲሁም ነፋስ ስልክ የሚገኘውን የሬድዮ መገናኛ አገልግሎት እንዲቋረጥ እንድናደርግ ትእዛዝ ተሰጠን። በትእዛዙም መሠረት ሁለት ሰዓት በፈጀ ጊዜ የስልክና የሬዲዮ አገልግሎት በሙሉ የተቋረጠ መሆኑን፣ ትእዛዝ ለሰጠን ለኮሎኔል ወርቅነህ እኩለ ሌሊት ሲሆን ሪፖርት አደረግን።[21]

ኮሎኔል ቃለ ክርስቶስ ዐባይም ከዚህ ቀጥሎ ባንክን፣ ጠቅላይ ግምጃ ቤትን፣ አቡነ ጴጥሮስ ሐውልት አካባቢ የሚገኘውን ሬዲዮ ጣቢያውንና የቴሌ አገልግሎት መስጫ ተቋማቱን ወታደሮችን አሠማርተው እንዲያስጠብቁ ጀኔራል መንግሥቱ ከለሊቱ ፮ ሰዓት ትእዛዝ ሰጥተው ትዕዛዙ ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ እንደሆነ ገልጸዋል። እንግዲህ ከዚህ ጋር በተያያዘ ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ የስልክ ማዞሪያዎችንና የሬዲዮ መገናኛ ተቋሞችን አገልግሎት ማቋረጥ ተገቢ እንደነበረ ሁሉ የሜጀር ጀኔራል መርዕድ መምጣትም አማራጭ የሌለው ወሳኝ ጉዳይ መሆኑን ጀኔራል መንግሥቱን መወትወቱን በመቀጠሉ ጀኔራል መንግሥቱ ቅር እያላቸውና እየከበዳቸው «እሺ» አሉ።[22] ስለዚህ ከሌሊቱ ፲ ሰዓት ተኩል ሲሆን ሻለቃ ኃይለ ማርያም ሌንጮ ጥቂት ወታደሮች ይዞ ሔዶ ክብር ዘበኛ ጠቅላይ መምሪያ ይዟቸው እንዲመጣ በጀኔራል መንግሥቱ ትእዛዝ ተሰጠው። ሻለቃ ኃይለ ማርያም ሌንጮም ከታዘዘበት ቦታ ሲደርስ፣ ሜጀር ጀኔራል መርዕድ ከቤታቸው ወጥተው ሔደው ስለነበር ሳያገኛቸው መቅረቱን ለጀኔራል መንግሥቱ ሪፖርት አደረገ።

ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህም ይሄን እንደሰማ፣ «እኔ ወይም የሻለቃ ተሰማ ዋቅጅራ ወይም ሌላ መኮንን ከ፴ ያላነሱ ጠንካራ ወታደሮችን ይዞ በመሔድ አንደኛ ክፍለ ጦርን ተጠግቶ ካደረ በኋላ፣ ወገግ ሲል አጥቅቶ ጀኔራሎቹን ይዞ ይምጣ» የሚል ሐሳብ እንደገና ለጀኔራል መንግሥቱ አቀረበላቸው። ጀኔራል መንግሥቱ አሁንም «አይሆንም ወርቁ! ቅድም ከቤቱ ቢገኝ በቀላሉ ሊመጣ ይችል ነበር። ክፍለ ጦሩን አጥቅቶ ለማምጣት ይቻላል። ግን የማንፈልገውን ደም መፍሰስ ያመጣል። በእንዲህ ያለ ነገር ልዑል አልጋ ወራሽም አይስማሙም። ሌላ መንገድ ቢፈለግ ይሻላል... » ብለው ይነጋገሩበት ከነበረው ክፍል ወጥተው ሔዱ። ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ ከብስጭትና ከቁጭት ላይ ወደቀ። ገና ከውጥኑ የተጀመረው ለውጥ ከጥፋት በቀር የትም ሊደርስ እንደማይችል ተረዳ። ከዚህ በኋላ በሚደረገው የተካፈለው ውድቀቱን አስቀድሞ በማወቅ እንደነበር አብረን በቅርብ እንገኝ የነበርን ሁሉ ያስተዋልነው ክስተት ነበር። እንግዲህ ከላይ እንደገለጽኩት፣ በሁለቱ ዋና የመፈንቅለ መንግሥቱ መሪዎች መካከል በእርምጃ አወሳሰድ ሥልት ላይ የታየው እንዲህ ያለ ልዩነት እየቆየ ሲሔድ የፈጠረውን ውጥረት የተሞላበትን ሁኔታና ውጤት ወደፊት እናያለን።

ንጉሠ ነገሥቱ ከአዲስ አበባ ከተማና ከኢትዮጵያ ክልል ውጭ በሚሔዱበት ጊዜ፣ አልፎ አልፎ ወታደራዊ ዝግጁነትን ለማሳወቅ የውጊያ ትርኢት በክብር ዘበኛ

---

[21] የመቶ አለቃ (በኋላ ብርጋዲየር ጀኔራል) ተድላ ደስታ

[22] ሻለቃ ተሰማ ዋቅጅራ

ሠራዊት ይቀርብ ነበር። ዝግጅቱ ጃንሆይ፣ የኮር ዲፕሎማቶች፣ ከፍተኛ የሲቪልና የጦር አለቆች በተገኙበት፤ በእግረኛ ቀላልና ከባድ መሣሪያዎች፣ በአየር ኃይል ተዋጊ አይሮፕላኖች ድጋፍ በእውነተኛ የጥይትና የከባድ ቦምቦች ተኩስ ታጅቦ የጥምር ውጊያ እንቅስቃሴ የሚካሔድበት ነበር። ዐላማውም የንጉሠ ነገሥቱና የመንግሥቱ ጥበቃ አስተማማኝ መሆኑንና፤ የሥራ ብቃቱ ሌላም ግዳጅ ለመፈፀም በተወርዋሪነት ለመዋጋት የሚችል መሆኑን ማሳያና፤ ንጉሠ ነገሥቱ የጠራቸውን ዝግጅት የሚያረጋግጡበት መድረክ ነበር። ጃንሆይ ወደ ብራዚል ከመሔዳቸው በፊት ጥቂት ወራት ቀደም ብሎ ሚያዝያ ፳፪ ቀን ፲፱፻፶፪ ዓ.ም. እሳቸውና ባለሥልጣኖች በተገኙበት፣ መላው የክብር ዘበኛ ሠራዊት የተሳተፈበትን ከፍተኛ የጥምር ኃይል ወታደራዊ ዝግጁነትን በእግረኛ፣ በመድፈኛ፣ በታንከኛና በተዋጊ አውሮፕላኖች የተኩስ ድጋፍ በሱሉልታ ወረዳ የተደረገውን የውጊያ እንቅስቃሴ የአዲስ አበባ ሕዝብ ተመልክቶታል።[23]

በመፈንቅለ መንግሥቱ ሒደት የቅርብ ዕማኝ የሆኑት የሻለቃ ተፈራ ወልደትንሣኤ ሒደቱን አስመልክቶ እንደሚከተለው ያስረዳሉ።

> ጃንሆይ ከኢትዮጵያ ውጭ በሚቆዩበት ጊዜ መንግሥታቸውንና ቤተ መንግሥቱን በተለየ ትኩረት መጠበቅ የተለመደ እንደመሆኑ፤ ጃንሆይ በ፲፱፻፶፫ ዓ.ም. ብራዚል ሲሔዱም፤ የክብር ዘበኛ አንደኛ ብርጌድ የሦስተኛ እግረኛ ሻለቃ የተደረበበትን ቃኚ ታንከኛ ሻምበልና የትራንስፖርት ክፍል ይዞና ታጥቆ ለድንገተኛ አስፈላጊ ሥራ ለመወርወር ፳፬ ሰዓት ቀንና ሌሊት በካምፕ ውስጥ ነቅቶ ትእዛዝ ይጠባበቅ ነበር። ታኅሣሥ ፬ ቀን ፲፱፻፶፫ ዓ.ም. ለሊት ፯ ሰዓት ላይ፣ የሻምበል ባዩ ጥላሁንና የሻምበል መሰለ መኩሪያ አለሁበት ቦታ ድረስ በመምጣት ጄኔራል መንግሥቱ ጠቅላይ መምሪያ ድረስ በአስቸኳይ እንደሚፈልጉኝ ሲነግሩኝ፤ የብርጌዴ ፫ኛ ሻለቃ ታጥቆ በተጠባባቂነት መቀመጡንና ፪ኛ ሻለቃ ደግሞ በተራው ቤተ መንግሥት ጥበቃ ላይ ተሠማርቶ የሚገኝ ስለሆነ ሊያስጠራኝ የሚችል ጉዳይ እንደሚኖር በመገመትና፤ ተልከው የጠሩኝንም መኮንኖች ስለማምናቸው፣ ሳላመነታ በእኔ መኪና ተሳፍረን ጉዞ ጀመርን። መንገድ ላይ ሳለን፤

---

[23] *የሻለቃ ተፈራ ወልደ ትንሣኤ ማክሰኞ ኅዳር ፬ ቀን ፲፱፻፶፫ ዓ.ም. በጄኔራል መንግሥቱ ንዋይ መጀመሪያ እንዲሰበሰቡ ከተጠሩት መኮንኖች አንዱ ነበሩ። በመሆኑም ከተጠሩበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ታኅሣሥ ፯ ቀን ከሰዓት በኋላ ድረስ በመንፈቅለ መንግሥቱ አራማጆች ዙሪያ ያዩትንና የተገነዘቡትን የገለጹበት ነው። ሻለቃ ተፈራ "የንጉሠ ነገሥቱ የክብር ዘበኛ ሠራዊት ይባል የነበረው ታኅሣሥ ፲፱፻፶፫ ዓ.ም. የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን መንግሥት ለማስወገድ በተደረገው እንቅስቃሴ ውስጥ የክብር ዘበኛ ፩ኛ ብርጌድንና እኔንም አስመልክቶ የማስታውሰውን እንድገልጽልህ በቃል ስላሳሰብከኝ ጥያቄዎች የሚከተለውን ማስታወሻ አቅርቤያለሁ"፤ በሚል በስድስት ገጽ ጽፈው ከሰጡኝና በቃልም ከገለጹልኝ ትውስታቸው፤ በጄኔራል መንግሥቱ ዙሪያ በቅርብ ስለተደረጉ ክንውኖች የዓይን እማኝና የተሳታፊ ምስክርነት መረጃ አድርጌ የወሰድኩት ነው። ይህን መረጃ ሻለቃ ተፈራ የሰጡኝ፤ በመፈንቀለ መንግሥቱ ምክንያት የተወሰነባቸውን ፍርድ ሳይጨርሱ በ፲፱፻፶፮ ዓ.ም. በወታደራዊ መንግሥት እንደተፈቱ ነው። ከሻለቃ ተፈራ ወልደትንሣኤ ጋር ከሻምበልነታቸው ጊዜ ጀምሮ በቅርብ የምንተዋወቅና የምንቀራረብ ነበርን። ከመፈንቅለ መንግሥቱ ከሸፈት በኋላ አራተኛ ክፍለጦር ስንገናኝ መቁርስ (መቁስ ማለት አብሮ የሚቆርስ አብሮ የሚበላ የማዕድ ጓደኛ ማለት ነው) ሆነን ቆይተን ወህኒ ቤትም አብረን ወረድን። እስከ ሕይወታቸው ማለፍም እንገናኝ የነበርን ወዳጆች ነበርን።*

"ለመሆኑ ምን ችግር አለ?" ብዬ መኮንኖቹን ስጠይቅ፤ በፈገግታ "ጄኔራል መንግሥቱ የእኛን ዕቅድ በሥራ ላይ አውለውታል" አሉኝ:: እኔም በመገረም መልሼ "እንዴት? ጄኔራል የኛን ዕቅድ ለማወቅ ቻሉና ነው?" ብዬ ሳልጨርስ፤ ተራ በተራ "ባለሥልጣኖች አስረዋል:: አልጋ ወራሽም ተይዘዋል" ብለው እየዘረዘሩ ማምሻውን የተፈጸመውን ነገሩኝ:: ምስጢራችን በነማን ሊወጣ እንደሚችል ለመገመት ስላልተቸገርኩበት፣ ዝም ብዬ ጠቅላይ መምሪያ ደረስን::[24]

ከዚያም ሻለቃ ተፈራ ወልደ ትንሣኤ በየቢሮው ባለሥልጣኖች በጥበቃ ሥር መሆናቸውን እያዩ አልፈው ከጄኔራል መንግሥቱ ጋር ተገናኙ:: ሰላምታ ሰጥተዋቸው ከፊት ለፊት እንደ ቆሙ ትንሽ ትኩር ብለው ዓይተዋቸው ሁኔታውን እንዴት እንደሚነግሯቸው እየተቸገሩ "ምነው ደንግጠሀል እንዴ?" ሲሏቸው "አልደነገጥኩም" ብለው ከመለሱላቸው በኋላ ቀጣዩን ሁኔታ በራሳቸው አገላለጽ እንዲህ ይተርካሉ::

«ሠራዊትህ የት ነው?» አሉኝ:: ፫ኛ ሻለቃ ታጥቆ ሠፈር መገኘቱንና ፪ኛ ሻለቃ በጥበቃ ሥራ ላይ ሲሆን፤ ፩ኛ ሻለቃና የቀሩት ከተማ ውስጥ በየቤታቸው እንደሚገኙ ገለጥኩ:: "፩ኛ ሻለቃንና ሌሎችንም የክብር ዘበኛ ሠራዊት አሁን እንዴት መሰብሰብ ይቻላል?" ብለው ጠየቁኝ:: የምንነጋገርበት ሰዓት ከሌሊቱ ሰባት ስዓት አካባቢ ስለነበር በርግጠኝነት «ሠራዊቱ ጠዋት በተለመደው ሁለት ሰዓት ሲሰበሰብ ይገኛል» አልኳቸው:: ለብዙ ጊዜ የክብር ዘበኛ ማሠልጠኛና የዘመቻ ሥራ ኃላፊ ሁኜ እስከ ቅርብ ጊዜ በቅርባቸው እሠራ ስለነበር፤ የብርጌድ አዛዥነቴን ዘንግተው ይመስላል፤ እንደ ቀድሞው የክፍለ ጦር ዘመቻና ማሠልጠኛ መኮንን አድርገው ነበር የሚያነጋግሩኝ:: «በል እዚህ ሁነህ የክፍለ ጦሩን የዘመቻ ሥራ ጀምሩ» አሉኝ:: እኔም መልሸ "በቦታው ላይ በኃላፊነት የተመደበው የሻለቃ ቃለ ክርስቶስ ዐባይ ስለሆነ ቅሬታ ይፈጥራል፤ ብርጌዴም ብቻውን ነው እንዴት ይቻለኛል?" ብዬ ጠየቅኋቸው:: ዝም ብለው ስላዩኝና ሻለቃ ቃለ ክርስቶስም ያለመምጣቱን ስላወቅሁ፤ ሠራዊቱ ሲሰበሰብ የት የት መቀመጥ እንዳለበትና ትእዛዝ እንዲጠባበቅ ለማድረግ ጥቁር ሰሌዳ አስመጣሁና የዝግጅት አሰላለፍ ነደፍኩ:: የጠላት ዋና አቅጣጫ መከላከያ ሚኒስቴር፣ ራስ ብሩ ሠፈር፣ መሿለኪያና ጨርቆስ መስመር ግምት ተወስዷል:: "ትንሽ ቆየት ብሎ የሻለቃ ቃለ ክርስቶስ ዐባይ ስለመጣ ሥራውን ትቸለት ወደ ብርጌዴ ለመሄድ ጄኔራል መንግሥቱን ፈቃድ ለመጠየቅ ገና ሐሳብ ላይ እንዳለሁ፤ ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ፣ የሻለቃ ተሰማ ዋቅጅራ፣ የሻለቃ ቃለ ክርስቶስ፣ የሻለቃ ዮሐንስ ምስክርና፣ እኔም እራሴ ሆነን፤ ጄኔራል መንግሥቱ ስለ ክብር ዘበኛ፣ የጦር ሠራዊትና አየር ኃይል ስለ ጠቅላላ ወታደራዊ አቀማመጥ ሁኔታ ከእሳቸው ጋር ሐሳብ ለሐሳብ እንድንለዋወጥ አድርገው በመጨረሻም የወታደራዊ አሰላለፍ ንድፈ ሐሳብ በማጠናቀቅ ስንወያይ ቆየን::

[24] ይህ ምስጢራችን የተባለው በክብር ዘበኛ መኮንኖች ውስጥ ለውስጥ ሲካሔድ የነበረውን ዐድማ ነው:: ጃንሆይ በተለያዩ ባለሥልጣናት አማካኝነት ክብር ዘበኛ የለውጥ ሤራ እንቅስቃሴ እየተባለ የሚነገራቸው ስለዚህ እንቅስቃሴ ነበር:: በዕለቱ ሻለቃ ተፈራ ለግዳጅ የተጠሩበት የመፈንቅለ መንግሥቱ እንቅስቃሴ ግን እርሳቸው የነበሩበት የዐድማው ቅጥያ ሳይሆን ራሱን የቻለ የለውጥ እንቅስቃሴ ነበር::

ከንጋቱ ፲፩ ሰዓት አካባቢ የሚከተለው ትእዛዝ ከጄኔራል መንግሥቱ ተሰጠ። «ተፈራ! በል በየጦር ሠፈሩ ያሉትንና በሌላም ቦታ የሚገኙትን የሠራዊቱ አባሎች መድፈኛ ግቢ በፍጥነት እንዲሰበሰቡ፤ የመሣሪያ ግምጃ ቤቶች ሁሉ ክፍት ሆነው ሠራዊቱ እንደአመጣጡ እንዲታጠቅና ትእዛዝ እንዲጠባበቅ አድርገህ ቶሎ እንድትመለስ» ብለው አዘዙኝ። ይህንኑ እንዲያስፈፅሙም መኮንኖች በየአቅጣጫው ላኩ። መኮንኖቹም ሻለቃ አበበ ገብረየስ፣ የሻምበል አሰፋ አርአያ፣ መቶ አለቃ በቀለ መንገሻና ጠቅላይ መምሪያ ከነበሩ የተጨመሩ አንድ ሦስት መኮንኖች ነበሩ።[25]

እንግዲህ በዚህ መልኩ የመሣሪያ ግምጃ ቤቶች ሁሉ መድፈኛ ግቢ ውስጥ ስለሚገኙ፤ መከፈታቸውንና ሠራዊቱም መታጠቅ ላይ መሆኑን፣ ራሳቸው ሔደው ማረጋገጣቸውንና ፫ኛ ሻለቃ ሠፈር ደርሰው በመመለስ ሁኔታውን ለጄኔራል መንግሥቱ ማስረዳታቸውን በማስታወሻቸው ገልጸዋል። ታኅሣሥ ፬ ቀን ማታ እንደ ጠቅላይ ግምጃ ቤት፣ ባንክ፣ ቴሌ፣ ማስታወቂያ ሚኒስቴር፣ ሬዲዮ ጣቢያ፣ አየር ማረፊያ፣ ውሀ ማጠራቀሚያ (ኮተቤ) እና በየኤምባሲዎች በር አጠገብ በመሳሰሉ በአንዳንድ ቁልፍ ቦታዎች አንዳንድ አንቂ ቃፊሮች (የተጠናከረ ጓድ) አንዳንድ መሪ መኮንን ተመድቦላቸው ሲጠብቁ አድረው ነበር። በማግሥቱ ደግሞ ጠዋት የሕዝብ መገልገያና መተላለፊያ ቦታዎች በሲቪል ፖሊስ እንዲጠበቁ ለኮሎኔል ጋሻው ከበደ ትእዛዝ ተሰጥቶ፤ ፊት ለፊት ለሕዝብ ይታዩ የነበሩ ወታደሮች ከሕዝብ እይታ ዘወር እንዲሉ ተደረገ።

ሻለቃ ተፈራ ማክሰኞ ማታ እስከ ሐሙስ ፲ ሰዓት ድረስ፣ ጄኔራል መንግሥቱ ከአጠገባቸው እንዳይለዩ አዘዋቸው ስለነበር አብዛኛውን ጊዜ እዚያው ጠቅላይ መምሪያ በተከናወኑ ሥራዎች ውስጥ እንዳልተለዩ ይታወቃል። በመሆኑም ጄኔራል መንግሥቱን በመተባበርና በዙሪያቸው የነበሩት ሰዎች ያደረጉትን በቅርብ ለመከታተል ችለዋል። ዝርዝሩንም እንዲህ ይገልጻሉ።

ማክሰኞ ማታ ሰዎች የተፈጠረውን ሁኔታ ለማወቅ ጄኔራል መንግሥቱን ሲቀርቧቸው ያሳዩት የነበረው ሁኔታ ሰው ሁሉ እንቅስቃሴውን ተረድቶ እንደመጣ ዓይነት ነገር ሲሆን፤ ጄኔራሉም አቀባበላቸው እንኳን ደህና መጣችሁ ዓይነት ነበር። ስለዚህ ምስጢሩን ለማወቅ የጓጓ ሁሉ በቅጡ የተረዳ መሆኑን ለመናገር ይቸገር ነበር። አብዛኛው ድርጊቶችን ጎን ለጎን በሹክሹክታ ከመጠያየቅና የራስን ግምት ከመውሰድ ያለፈ ነገር ማድረግ አልቻለም። ሌሎች ደግሞ "የመንግሥት ግልበጣ ነው" ብለው ሁኔታውን የተቀበሉና ለመተባበር የተሰለፉ ይመስሉ ነበር።

ጄኔራል ጽጌ ዲቡ ከትእዛዝ መስጫው ቢሮ ራቅ ባለ ክፍል ውስጥ ከወርቅነህ ጠበቅ ባለ ሁኔታ ይጠበቁ ነበር። ፖሊስን ለማንቀሳቀስና ልዩ ልዩ

[25] ሻለቃ ተፈራ ወልደ ትንሳኤ

ሥራ ለማስፈጸም በሚያስፈልግበት ጊዜ፣ ጄኔራል መንግሥቱ ሔደው፣ "የፖሊስ አዛዦች ይመጣሉና ይህን ትእዛዝ ስጥልን" ብለው ከነገሯቸው በኋላ የተባሉት መኮንኖች ተጠርተው ሲመጡ፣ ጄኔራል ጽጌ ትእዛዝ መንገራቸውን ከሚያረጋግጥ ሰው ጋር የተጠሩት ሰዎች ቀርበው መመሪያ ይቀበላሉ። ጄኔራል ጽጌ ከእንደዚህ ያለ ጉዳይ ሌላ ያሳዩት ተሳትፎ አልነበረም። ጄኔራል ጽጌ የጄኔራል መንግሥቱ ወዳጅ እንደነበሩ ይታወቃል። በጄኔራሉ ላይ የነበረው ጥበቃ የውጊያ ትእዛዝ እስከተሰጠበት እስከ ሐሙስ ድረስ ቀጥሎ ነበር። ሌሎችም፣ ለምሳሌ ሻለቃ ዮሐንስ ምስክር ለብዙ ጊዜ ለጄኔራል መንግሥቱ የቅርብ ረዳት ሆኖ ይሠራ እንደነበር ሲታወቅ፣ በንቅናቄው የመጀመሪያ ሦስት ቀናት፣ እኔ እንደተገነዘብኩት፣ በቅርብ ከመገኘት በቀር በጄኔራል መንግሥቱ በተሰጠ ትእዛዝ ወይም እራሱ ፈጥሮ የመሥራት ተሳትፎ አላሳየም። የሻምበል አሥራት ደፈረሱ ደግሞ ከጄኔራል መንግሥቱና ከገርማሜ ጋር የቅርብ ግንኙነትና ዝምድና ያለው ቢሆንም፣ በሥራ ጠባዩ በክብር ዘበኛ ራዲዮ ጣቢያ ምክንያት ከሠራው ሌላ ያደረገው ነገር የለም፣ እስከመጨረሻውም አብሮ አልቆየም።

በአጠቃላይ፣ ማክሰኞ ማታ በጄኔራል መንግሥቱ ዙሪያ የነበሩ ሰዎች ባንድ ጊዜ የተሰበሰቡ አልነበሩም። እኔ በደረስኩ ጊዜ የነበሩና በደቂቃና በሰዓታት ልዩነቶች ከታዩት ውስጥ ጥቂቶችን ብንጠቅስ፣ እነአቶ ገርማሜ ወንዳአፍራሽ፣ ገርማሜ ንዋይ፣ ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ ገበየሁ፣ ጄኔራል ጽጌ ዲቡ፣ ዐምዬ ወንድአፍራሽ፣ የሻለቃ ተሰማ ዋቅጅራ፣ የሻምበል አሥራት ደፈረሱ፣ አቶ ለማ ፍሬው፣ የሻለቃ ያሬድ ቢተው፣ የሻምበል ባዬ ጥላሁን፣ የሻምበል መሰለ መኩሪያና ሌሎችም በእማኝነት ባለሥልጣኖችን በመጠበቅ ላይ የነበሩ መኮንኖችና ባለሌላ ማዕረጎች ማስታወስ ይቻላል። በጥቂት ደቂቃዎችና በሰዓታት ልዩነት ደግሞ፣ እነ የሻለቃ ቃለ ክርስቶስ ዐባይና የሻለቃ ዮሐንስ ምስክር ዘግይተው፣ ከተማ ይፍሩና ማሞ ታደሰ፣ ረፋድ ላይ፣ አቶ ዳዊት ዕቁ እግዚ ከሕዝብ ፀጥታ፣ እነ የሻምበል ከበደ ተሰማ፣ የሻምበል ጸጋዬ ደፈርሻ፣ የሻምበል ተስፋዬ አትመውና አቶ መስፍን ወልደ ሚካኤል በሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ እየታዘዙ ይንቀሳቀሱ ነበር።


ጄኔራል መንግሥቱ ከማክሰኞ ማታ ጀምሮ መሣሪያ ታጥቀው፣ ቀንና ሌሊት ፳፬ ሰዓት ነቅተው ሰው ሲያነጋግሩና ትእዛዝ ሲሰጡ ይታዩ ነበር። ገርማሜም እንደ አጃቢና ዘብ ሆኖ ካርባይን አንግቶ የጄኔራል መንግሥቱን እንቅስቃሴ ከኋላና ከፊት እየተከተለ በትኩረት ግራ ቀኝ እየተመለከተ፣ በጥበቃ ሥራ እስከ መጨረሻው ጊዜ ድረስ ሲንቀሳቀስ ይታይ ነበር። እንግዲህ የማክሰኞ ለሊት ከላይ እንደተገለጸው የሚፈለጉ ባለሥልጣኖችን በመያዝ፣ ተባባሪዎችን በማሰባሰብ ቁልፍ ቦታዎችን እያስጠበቁ የሚቀጥለውን ሥራ ለመሥራት በማቀድና ሠራዊቱን እያሰባሰቡ በማስታጠቅ ታደረ።[26]

---

[26] ዝኒ ከማሁ

## የጦር ሠራዊት የተቃርኖ ዝግጅት

ሜጀር ጄኔራል መርዕድ መንገሻና ሜጀር ጄኔራል ከበደ ገብሬ በአንደኛ ክፍለ ጦር (በኋላ አራተኛ) "ማን ያርዳ የቀበረ ማን ይናገር የነበረ" እንደሚባለው ሁሉ፣ ጠቅላይ ኤታ ማጆር ሹሙና የምድር ጦር አዛዡ በወቅቱ እንቅስቃሴውን እንዴት እንዳወቁትና እንደደረሱበት ምን እንዳሰቡና በዕለቱ ምን እንዳደረጉ፤ ከመፈንቅለ መንግሥቱ ክሽፈት በዝርዝር የሰጡትን ቃለ ምልልስ መመልከት ለግንዛቤ ስለሚረዳ እንደሚከተለው አቅርቤዋለሁ::



*ሜጀር ጄኔራል መርዕድ መንገሻ*
*የጦር ኃይሎች ኤታ ማጆር ሹም*

> ይህ ሁከት መፈጠሩን የሰማሁት ከተኛሁ በኋላ ከምሽቱ ፫ ሰዓት ተኩል ነው:: ይኸውም ወደ ክቡር ራስ አበበ ቤት ስልክ ደውልኩ፤ ወይዘሮ ቆንጂትን (የራስ አበበ ባለቤት በኋላ እመቤት ሆይ) አገኘኋቸው:: «ራስ አበበ ግቢ ይፈለጋሉና እንዲመጡ ተብለው በክቡር ራስ አንዳርጋቸው ተጠርተው ሄደዋል:: ነገር ግን፣ ራስ አንዳርጋቸው እየደወሉ እስከሁን አልደረሱም ይሉኛል:: ከቤት ከወጡ ጀምሮ ያለው ጊዜ ሲታሰብ እንኳንስ እዚያ ሌላም ቦታ ለመድረስ ያስችላል» አሉኝ:: እኔም "ምን የተፈጠረ ነገር አለ? ግርማዊትስ ምን ሆነው ይሆን?» በማለት ብጠይቅ፣ «ኸረ እንጃ! እኔ ነገሩ ደስ አላለኝም:: በበኩልህ የምትሰማው ነገር ከተገኘ ደውልልኝ፤ በኔ በኩል ከተገኘ እደውልልሃለሁ» አሉና ስልኩን ዘጉት::[27]

እንግዲህ ይህ የወይዘሮ ቆንጅት የንግግር ቃና ነው ጄኔራል መርዕድን ያነቃና ጥርጣሬ ውስጥም የከተታቸው። ከዚያም ጄኔራል መርዕድ ሲቀጥሉ፤

---

[27] አዲስ ዘመን፣ ታኅሣሥ ፲፪ ቀን ፲፱፻፶፫ ዓ.ም.



ሜጀር ጀኔራል መርዕድ መንገሻ
የጦር ኃይሎች ኤታ ማጆር ሹም

የተገለጠ ነገር ባለማግኘቴ ነገሩ ትንሽ ግር አለኝ:: የሆነው ሆኖ ወደ ሌላ ቦታ በመደወል ነገሩን ማጣራት ያለብኝ ሆኖ አገኘሁት:: በዚህም መሠረት ወደ ጄኔራል መንግሥቱ ቤት ደወልኩ:: ያገኘሁትም መልስ "የሉም" የሚል ነበር:: "ወደየት ሄደዋል" ብዬ ብጠይቅም «አናውቅም የሚል መልስ ተሰጠኝ:: ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ ወደ ጄኔራል ከበደ ቤት ደወልኩና ለጊዜው «የለም» አሉኝ:: ወዲያውም ወደ ጄኔራል ኢሣይያስ ዘንድ ደወልኩና አገኘ ሁት:: እርሱም የሰማው ነገር እንደሌለ ነገረኝ:: ጉዳዩ በጣም ግር አለኝ:: «ምን ይሆን?» እያልኩ ሳወጣና ሳወርድ በግርማዊት ላይ ሳይሆን በመንግሥት ላይ አንድ ነገር እንደተደረገ ተሰማኝ::[28]



ወይዘሮ ቆንጂት አብነት

በዚህ መልኩ የወይዘሮ ቆንጂት ንግግር ጄኔራል መርዕድን አነቃቸው:: ለዚህ ነው ኒውስ ዊክና ታይም መጽሔት እ.ኤ.አ ታኅሣሥ ፳፮ ቀን ፲፱፻፷ ዓ.ም. ባወጡት ጽሑፍ የራስ አበበን ባለቤት «ኤ ውመንስ ክራይ ሴቭድ ዘ ክራውን» በማለት ያደነቋቸው::

ከዚህ በኋላ ያስከተለውን ሁኔታ ጄኔራል መርዕድ እንደሚከተለው ይዘረዝራሉ

> ከዚህ በኋላ ወደ ፮ ሰዓት ከ፲ ደቂቃ ገደማ ይመስለኛል ወደ ጄኔራል ጽጌ ዲቡ ዘንድ ብደውል "የለም" አሉኝ:: እንደገና ወደ ጄኔራል መንግሥቱ ቤት ብደውል የሚገኘው "ጄኔራል ጽጌ ዲቡ ቤት ነው" የሚል መልስ አገኘሁ:: ነገር ግን በዚህ መሐል ሁለቱ ጄኔራሎች በጥብቅ ፈልገውኝ ኖሮ ሊያገኙኝ ሳይችሉ ቀርተዋል:: ይኸውም ስልክ እየተያዘባቸው ኖሯል:: እስከተባለው ጊዜ ድረስ ባደረግሁት መጠያየቅ ምንም የተጨበጠ ነገር ስላላገኘሁ እንደገና ወደ ወይዘሮ ቆንጂት አብነት ዘንድ ስልክ ደወልኩ::
>
> ወዲያው «እስከአሁን የሰሙት ነገር የለም ወይ?» በማለት ብጠይቃቸው፣ «ልዕልት ተናኘ ወርቅ ይፈልጉህ ነበርና በእንዲህ ባለ ቁጥር ስልክ ደውል» የሚል መልስ ሰጡኝ:: ከዚያም ፈጥኜ ወደ ግርማዊት እቴጌ ቪላ ስልክ ደወልኩና ልዕልት ተናኘ ወርቅን አገኘኋቸው:: ልዕልትም፣ «ምንድን ነው ነገሩ? የሆነውን ሁሉ አልሰማህም እንዴ?» በማለት ጠየቁኝ:: «ኧረ የለም» የሚል መልስ ስላስከተልኩ «እነ መንግሥቱ አልጋ ወራሹንም፣ ራስ አበበንም፣ ራስ አንዳርጋቸውንም፣ አቶ መኮንን ሀብተ

[28] ዝኒ ከማሁ



*ወይዘሮ ቆንጂት አብነት*

ወልድንም የጦር ሠራዊት ስላመፀ በጉዳዩ እንመካከርበት እያሉ ወስደው አስረዋቸዋልና ልታደርግ የምትችለው ነገር እንዳለ መሞከር ነው" አሉኝ:: ይህን የልዕልትነታቸውን ቃል እንደሰማሁ በጦር ሠራዊት በኩል አንዳች ነገር እንደሌለ ዐውቅ ነበርና፤ የክብር ዘበኞች ዐምፀው ዐድማ እንዳደረጉ ገመትኩ:: ከዚህ በኋላ መሣሪያዬን አንሥቼ ባለቤቴንና ልጆቼን ይዤ ወደ ዘመድ ቤት ሔድኩና ቤተሰቦቼን ከዚያ ተውኩ:: ወዲያውም ለሁለተኛ ጊዜ ባደረግሁት የስልክ ጥሪ ጄኔራል ከበደን አገኘሁትና ልብሱን ለብሶ እንዲቆየኝ አደረግሁ:: ከዚያም ፈጥኜ ሔድኩ:: ጄኔራል ከበደ ቤት እንደደረስኩ ልብሱን ለብሶ ቆይቶኝ ነበርና ከእርሱ ቤት ሆኜ ጄኔራል ኢሳይያስን ለማስነሣት ብሞክር ስልኩን ቆርጠውት ኖሮ ለመገናኘት ሳልችል ቀረሁ:: ከዚህ በኋላ ከጄኔራል ከበደ ጋር ሆነን በቀጥታ ወደ አንደኛ ክፍለ ጦር ሔድን:: ወደዚያ ስንሔድ እግረ መንገዳችንን የመድፈኛን ክፍል አነቃን:: መድፈኞች ታጥቀው እንዲጠባበቁም ትእዛዝ ሰጠን:: ከዚያም ወደ አንደኛ ክፍለ ጦር ገባን:: ገብተንም የአዛዡን ስልክ ቆርጠውት ኖሮ ግንኙነት ለማድረግ የማይቻል ሆኖ አገኘነው:: የሆነ ሆኖ የጄኔራል ያዕቆብና የሌሎች ስታፎች ስልክ ገና አልተቆረጠም ነበርና፤ በዚህ ባልተቆረጠው ስልክ ደውዬ ጄኔራል ኢሳይያስን አገኘሁና ጠርቼው በአጭር ጊዜ ውስጥ ፈጥኖ ስለመጣ፤ እዚያው እንዳለን በመጀመሪያ ጄኔራል ዋቅጅራ ሰርዳን ቀጥሎ ጄኔራል ወልደ ሥላሴ በረካን ቀሰቀስን:: በዚህ መካከል ግን ስልኩን በመከታተል እየቆረጡት ሔዱ:: እኛ ለሕዝባዊ አገልግሎት የማይውል የራሳችን የውስጥ ስልክ ነበረንና በዚህ መሣሪያ አማካኝነት ትእዛዛችንን ለጦሩ ለማስተላለፍ ችለናል:: መኮንኖቻችንም ከያሉበት እንዲቀሰቀሱና በየጦር ክፍላቸው ተገኝተው ስፍራ እንዲይዙ ትእዛዝ የሰጠነውም በዚሁ መሣሪያ አማካይነት ነው::[29]

ከፍ ሲል እንደተመለከተው ሜጀር ጄኔራል መርዕድ መንገሻና ሜጀር ጄኔራል ከበደ ገብሬ በበኩላቸው መፈንቅለ መንግሥት በክብር ዘበኛ ጦር መጀመሩን በማወቅ፤ ጦር ሠራዊት በሚገኝባቸው በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች በክፍለ ጦሩ የሬዲዮ ቴሌፎን መገናኛ በመጠቀም መፈንቅለ መንግሥቱን ለማክሸፍ ትእዛዝ ሲያስተላልፉ ቆዩ:: በሌላ በኩል ደግሞ፣ የንጉሣዊ ቤተሰቦችና የዘውዳዊው አገዛዝ ደጋፊዎች ዘውዳዊውን አገዛዝ ከውድቀት ለማዳን የበኩላቸውን ዘዴ ለመሻት በልዑል አልጋ ወራሽ ግቢ ስብሰባ አካሔዱ:: የስብሰባው ተሳታፊዎችም ልዕልት መድፈሪያሽ ወርቅ አበበ፣ ልዑል ደጃዝማች አሥራተ ካሣ፣ ባላምባራስ ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል፣ ፊታውራሪ ወርቅነህ ወልደ አማኑኤል፣ ካፒቴን ኃይሉ ተክለ ማርያምና በጅሮንድ አባትኩን ወርቅነህ ነበሩ:: ልዕልት መድፈሪያሽ ወርቅ አበበ እንዲህ ሲሉ ስብሰባውን ከፈቱ፤ «ክብር ዘበኞች ልዑል ጌታዬን ምን እንዳደረጓቸው፣ ወዴትም እንደወሰዷቸው አይታወቅም:: ወታደሩ አድሞ ከሆነ፣ የባላገር ጦር ማዘጋጀት ያስፈልጋል» ብለው እንደተናገሩ ውይይቱ ቀጥሎ፤ በዚሁ ውሳኔ እንደተደመደመ፤ ደጃዝማች ከበደ ተሰማ መድረሳቸውን፤ ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ ልዑል ደጃዝማች አሥራተ ካሣ «እርስዎ

[29] ዝኒ ከማሁ

ወደ ደብረ ብርሃን እንዲሔዱ መክረናል» በማለት ስብሰባው ሲካሔድ ላልነበሩት፣ የወቅቱ ብሔራዊ ጦር ኤታ ማዦር ሹም ለደጃዝማች ከበደ ማስታወቃቸውን፤ ከዚያም ደጃዝማች ከበደ ተሰማ በሃሳቡ ተስማምተው፣ ከሌሊቱ ፱ ሰዓት ገደማ ከግቢው ወጥተው መሔዳቸውን እንረዳለን::

ከዚህ በኋላ ጦር ሠራዊትና ክብር ዘበኛ አንዱ በሌላው ላይ እያደባ በበነጋታው ለሚደረገው ፍጥጫ መዘጋጀቱን ቀጠለ::